የጦር መሣሪያ በገፍ ተገዝቷል፡፡ ለአዲስ ምልምል ሠራዊት … ወዘተ … እያለ ቀጥሎ ለአጠቃላይ የቀይ ኮከብ ዘመቻ ብቻ ከ5 ቢሊዮን በላይ የሚገመት ብር ወጪ ተደርጓል፡፡ ይህም ክፊሉ ለልማት ክፊሉ ለጦርነት መሆኑ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የኢትዮጵያውያን ዓይንና ጆሮ ብቻ ሳይሆን ሁሉ ነገራቸው ኤርትራ ላይ ሆነ፡፡

በታቀደው መሠረትም በጦርነት የወደሙ ፋብሪካዎች፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ት/ቤቶች፣ የጤና ተቋሞች፣ መንገዶች፣ ባንክ፣ ውሃና መብራት … የፈረሱት ተጠግነው ያልነበሩት ተሰርተው •እንቅስቃሴ ጀመሩ፡፡ ሠርቶ አደሩ፣ ላብ አደሩ ወደየስራ መስኩ እንዲመለስ ተደረገ፡፡ ተማሪው ትምህርቱን ቀጠለ፡፡ በሽተኛው ህክምና ማግኘት ጀመረ፡፡

አያሌ ገንዘብ የወጣበት ፌስቲባልና ባዛር በምፅዋ ሠሜናዊ ድንበር "ጉርጉሱም" በተባለ ሥፍራ ተዘጋጅቶ በጓድ ሊቀመንበሩ ተመርቆ ተከፈተ … በጦርነት የደቀቀችው ከተማ ነብስ ዘራች…፡፡

ጥር 17 ቀን 1974 ዓ.ም ሊቀመንበር መንግስቱ "…. የኤርትራ ህዝብ ሆይ! ልብ ብለህ ስማኝ … አባቶች፣ እናቶች፣ እህቶች፣ ወንድሞች … ስል የለበጣ አይደለም፡፡ የፖለቲካ ወይም የዲፕሎማሲ ቋንቋ አይደለም ከሐቅ ነው! ከአንጀት ነው!… የጋራ ችግራችንን፣ የጋራ ስቃያችንን ልናስወግድ፤ ወይም መፍትሄ ልንፈልግ ተሰብስበን እንደሆነ በግልፅና በሐቅ እንነጋገር …"

"…. ቀደምት አባቶቻችን ስልጣኔን ለዓለም አሻግረው የሰጡበት ድንበር፣ በጠላት ላለማስነጠቅ የከፈሉት መስዋዕትነት፣ ጠብቀው አቆይተው ያስረከቡንን አደራ፣ በጀግንነት የተዋደቁላትንም ምድር …" እያሉ ተርከው የአሉላ አባ ነጋን ጀብዱ እያስታወሱ ወደ አብዮቱ ዘመን መጥተው የቀይ ኮከብ ዘመቻን ዓላማና ግብ፤ እንዲሁም ቀጣይ ሂደቱን የሚመለከት ሰፊ ገለፃ አድርገው የዘመቻውን ጉባዔ ከፈቱ፡፡ ሊቀመንበሩን ተከትለውም የኢትዮጵያን ህዝብ የሚወክሉ የተባሉ ታላላቅ ሰዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ ባለስልጣናት … ተመሣሣይ ልብ የሚነካ ንግግር አደረጉ፡፡ የኤርትራ ህዝብም የመኖር ተስፋ ጭላንጭል በማየቱ ተደሰተ፡፡

ጉባዔው በዚህ ሁኔታ ተከፍቶ ሲሰነብትም አጠቃላይ አፈፃፀሙ በሁሉም ገጽታው ታሪካዊ እንዲሆንና የታሪክ አሻራም ትቶ እንዲያልፍ፤ ታሪኩ ለትውልድ ተከትቦ ይቆይና ይተላለፍም ዘንድ ልዩ ዝግጅቱ ተጠናቆ ጋዜጠኞች፣ የኪነጥበብ ሰዎች፣ ደራሲያን፣ የታሪክ ምሁሮች፣ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትና የአገር ሽማግሌዎች ታድመው ጉባኤውን አድምቀዋል፡፡ አንጋፋው ደራሲና ጋዜጠኛ፣ በዓሉ ግርማ አንዱ ነበር፡፡ ያያቸውን ሚስጥሮች ሁሉ በኦሮማይና በቀይ ኮከብ ዘመቻ መጽሐፉ ተርኮታል፡፡ በዓሉ ግርማ በወቅቱ አጠቃላይ ሁኔታውን አይቶ ዘገባውን እንዲያቀርብ በመንግስት ታዞ ነበር የሄደው፡፡ ይህ ታላቅ ብዕረኛ



ያያትን ሁሉ ሲፅፍ በሳንሱር እንደሚወድቅ ቢረዳም እውነታውን [illegible] ወደ ኋላ አላለም፡፡ በመጨረሻ ለፕሮፓጋንዳ ይረዳል ተብሎ የታሰበውን ዘገባ ሲያቀርብ ጽሁፉን ሳንሱር የሚያደርጉ የበላይ አለቆቹ ተቀብለው "እገሌ ይየው" እገሌ ይየው እየተባባሉ ሲዘባሩና ከተለመደው መንግስታዊ አዘጋገብ የተለዩ አይሆንም ብለው በመዘናጋታቸው ጭምር ትኩረት ስላልሰጡት በደንብ ሳይፈተሽ ሄዶ ሄዶ ለህትመት በቃ፡፡ ወይም ባልታሰበ መንገድ ታትሞ ተሰራጨ፡፡ ይህ የፀሐፊው ጥፋት አይደለም፡፡ የፃፈውን ለበላዮቹ ገምጋሚዎች ሰጥቷል፡፡ ገምግሞ መጣልም ሆነ ለህትመት እንዲበቃ መፍቀድ ያለባቸው እነሱ ነበሩ፡፡ ሳይሆን ቀርቶ አምልጦ ታተመ፡፡ "ኦሮማይ" ማለት አበቃለት ማለት ነው፡፡ ደራሲው ባለስልጣናቱን እየጠቀሰ ያየውን ሁሉ አጋለጠ፡፡ ገመናቸውን ያዩ ደነገጡ፡፡ በተለይ ደህንነቱን አፍረጥርጦታል፡፡ እናም ገደሉት….፡፡

ሁሉም ለዘላቂ ውጤት ጓጉቷል፡፡ በተቃራኒውም ዘመቻውን ለማክሸፍ የሚያስችል መረጃ ለጠላት አሳልፎ ለመስጠት ቀብድ የተቀበሉ ጉቦኛ የኢትዮጵያ ልጆች (የጦር አዛዦች) አብረው ነበሩ፡፡ የሻዕቢያ ደጋፊ የሆኑ የውጪ ኃይሎች "ኢትዮጵያ በሻዕቢያ ላይ የመርዝ ጋዝ ልትጠቀም ስለሆነ የመርዝ ጋዝ መከላከያ ጭንብል ለሻዕቢያ እንሰጣለን" እያሉ የሐሰት ወሬ ይነዙ ጀመር፡፡

በጉባኤው ላይ "የአስመራ ማኑፌስቶ" ተብሎ የተሰየመው የአቋም መግለጫ የሁሉም ክፍላተ አገር ተወካዮችና በአካባቢው የሚኖሩ የኩናማ፣ የቤኒአመር፣ የአፋርና የሌሎች ብሔረሰብ ተወካዮች በተገኙበት ይፋ ሲደረግም ሁሉንም ያስደሰተ በመሆኑ ተቀባይነቱ አላጠያየቀም፡፡ በጥቅሉ በዘመቻው ጉባዔ ላይ የተነገሩት ንግግሮችና በተግባር የተጀመሩት ስራዎች መላውን የኤርትራ ህዝብ ያጓጓ ሲሆን፤ በተቃራኒው ሻዕቢያ በድንጋጤ የራደበት ክንውን ነበር፡፡

ከጉባኤው በኋላ በሊቀመንበር መንግስቱ ሰብሳቢነት የተነደፈው የወታደራዊ ዘመቻ እቅድ ላይ የክለሳ ውይይት ተካሄደ፡፡ የውይይቱ ዓላማ የአዛዦቹ ቅድመ ዝግጅት ምን እንደሚመስል የሚገልፅ ሪፖርት ማሰማት ነበር፡፡ በጠላት ላይ ጥቃት እንዲሰነዝሩ፣ ደጀን ሆነው እንዲጠብቁና ቁልፍ ቦታዎችን ይዘው እንዲቆዩ ግዳጅ የተሰጣቸው ዕዞችና ክፍለጦሮች ዝግጅታቸውን አጠናቀው በተጠንቀቅ ላይ መሆናቸውን ገለፁ፡፡ ቀድሞ በግብረ ኃይል ተዋቅሮ የነበረው ወደ ዕዝ ተለውጦ ነበርና፤ ውቃው ዕዝ፣ ናደው ዕዝ፣ መብረቅ ዕዝ፣ መከት ዕዝ፣ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ዕዝ በውስጡ በርካታና የተለያዩ ክፍለጦሮችን ያካተተ ሆኖ የተዋቀረ ነው፡፡

በዚህ መሰረት 1. በብርጋዴል ጄኔራል አበራ አበበ የሚታዘዘው ውቃው ዕዝ በአልጌና ግንባር ከቀይ ባህር በኩል በናቅፋ ጀርባ

እንዲያጠቃ፣ 2. ብብርጋዴል ጄኔራል ውበቱ ፀጋዬ የሚታዘዘው ናደው ዕዝ ከከረን ናቅፋ በር በከርከበት ግንባር ከናቅፋ ደቡባዊ ምስራቅ በኩል እንዲያጠቃ፣ 3. በብርጋዴል ጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ የሚታዘዘው መብረቅ ዕዝ ከቃሮራ ናቅፋ በር ግንባር ማለትም ከናቅፋ ሰሜናዊ ምዕራብ በኩል እንዲያጠቃና የሻዕቢያን መውጫ እንዲዘጋ፣ 4. በብርጋዴል ጄኔራል ከበደ ጋሼ የሚታዘዘው መከት ዕዝ የአስመራን ዙሪያ እንዲይጥር፣ 5. የሰሜን ዕዝ ልዩ ልዩ ክፍል የአስመራ ከተማን የውስጥ ጥበቃ እንዲያከናውን የሚል የዘመቻ ትዕዛዝ ተቀብለው ተዘጋጅተዋል፡፡ ከአንድ እስከ ሦስት ያሉት የዘመቻ እቅዶች ግባቸው የናቅፋ ከተማ ናት፡፡

አዛዦቹ ሪፖርታቸውን ሲያሰሙ "ጓድ ሊቀመንበር ዘመቻው ሙሉ በሙሉ ይሳካል፤ ሁሉንም ነገር ለእኛ ይተውት፤ አያስቡ" የሚሉት ቢበረክቱም፣ ጄኔራል አበራ አበበ ግን በተለይ በመብረቅ ዕዝ ስር ያለውን 21ኛ ተራራ ክፍለ ጦር በሚመለከት፤ "ከተቋቋመ አንድ ዓመት ያልሞላው፣ ምንም የውጊያ ልምድ የሌለው፣ ከኦጋዴን ኤርትራ ከገባ ወር ያልሆነው፣ ከኤርትራ መሬትና ከሻዕቢያ የውጊያ ስልት ጋር ትውውቅ ያላደረገ አዲስ ጦር ነው፡፡ ተራራ ክፍለ ጦር ስለተባለ ብቻ ተዓምር ሊሰራ አይችልም፡፡ ተጨማሪ የልምምድ ጊዜ ተሰጥቶት መለማመድ አለበት፡፡ አልጌና ግንባር ያለው ጦርም ቢሆን ለኃይል ማሟያ የተሰጡን አዳዲስ ጦር ስላሉን ተጨማሪ የልምምድ ጊዜ ተሰጥቶን ከታንከኛና ከመድፈኛ ጋር የኅብረት ውጊያ መለማመድ አለብን፡፡ የጦሩ መንፈስ ዝግጁነት በቂ ስላልሆነ ውጊያ ለመጀመር ባንቸኩል ጥሩ ነው" የሚል ሀሳብ አቀረቡ፡፡ መንግስቱ የጄኔራል አበራን ሀሳብ "አልቀበልም" ብለው ዘመቻው በቀጥታ እንዲጀመር አዘዙ፡፡ የካቲት 8 ቀን 1974 ዓ.ም ሊነጋጋ ሲል በሁሉም ግንባር ወደ ናቅፋ የመጠጋት እንቅስቃሴ ተጀመረ፡፡ የናቅፋ ተራሮች በቢ..ኤም.ሮኬት፣ በመድፍ፣ በሞርታር፣ ከሰማይ በሄሊኮፕተርና በጀት በሚወነጨፉ ከባባድ ተኩሶች ተንቀጠቀጠች፡፡ አካባቢው እሳት ለበሰ፡፡

ሻዕቢያ ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሞ ተከላከለ፤ ግን አልቻለምና ናቅፋን ለቆ ሊወጣ ዝግጅት ጀመረ፡፡ ሆኖም ሁሉም መንገድ ታጠረበት፡፡ እዚያው በተከበበበት ሆኖ ማለቅ የመጨረሻው ምርጫ ሆኖበት በአለታማው ተራራ ተለጥፎ መጨፍጨፍ ዕጣው ሆነ፡፡

በሰሜን ምዕራብ በኩል የተንቀሳቀሰው መብረቅ ዕዝ ለወሣኝ ድል ተስፋ የተጣለበት ሲሆን፤ እንዲያጠቃ የተሰጠው ቀጠና ለእግረኛና ለሜካናይዝድ ጦር ውጊያ አመች በመሆኑ ግራ ቀኝ ያሉ ተራሮችን አስለቅቆ ከተቆጣጠረና በጠላት ላይ ተፅዕኖ ካደረሰ በኋላ ቀጣዩን ግዳጅ እንዲወጣ ለተመደበው የእግረኛና የሜካናይዝድ ጦር መክፈት ነበረበት፡፡



ይህ ከሆነ ብቻ ነበር ሙሉ ድል ሊገኝ የሚችለው፡፡ ለዚህም ተብሎ እዙ አስፈላጊው የሰው ኃይልና ትጥቅ በበቂ ሁኔታ ነበረው፡፡ ሆኖም ዛሬም ድረስ ባልታወቀ ምክንያት ዕዙ በተሰጠው ትክክለኛ ሰዓት መንቀሳቀስ ባለመቻሉ ጠላት ከሩቅ ያሉትን የሰው ኃይሎች አሰባስቦ እንዲጠናከር ጊዜ ሰጠው፡፡ በዚህች በተፈጠረች የጊዜ ክፍተት ሻዕቢያን ለማገዝ ከሩቅ ቦታ ተነስቶ ተጉዞ የመጣው አንድ ሙሉ የወያኔ ብርጌድ ደረሰለት፡፡የዚህ የወያኔ በርጌድ መሪ አርከበ ዕቁባይ እንደነበሩ በርካቶች ፅፈዋል፡፡በዚህም ሻዕቢያ ነብስ ዘራ፡፡

በመብረቅ ዕዝ ስር ያለውና ግንባር ቀደም የማጥቃት እርምጃ እንዲወስድ ግዳጅ የተሰጠው 21ኛው ተራራ ክፍለ ጦር እንኳን ተራሮችን አስለቅቆ ሊይዝ ቀርቶ፤ ሰብሮ ሊወጣ ባልቻለው የጠላት ቀለበት ውስጥ ገብቶ ተጨፈጨፈ፡፡ ሻዕቢያና ወያኔ በምርኮ ተንበሸበሹ፡፡ ጥቂቶች ብቻ አፈግፍገው ማምለጥ ቻሉ፡፡ ይህ የጦር ክፍል ለምን በተሰጠው ሰዓት እንዳልተንቀሳቀሰ የተለያዩ አስተያየቶች ዛሬም ድረስ ቢነሱም የብዙሃኑ የቀድሞ አዛዦች መንግስቱን ጨምሮ "ሆን ተብሎ የተደረገ ነው" የሚል ነው፡፡ ተራ ወታደሮችም ከዚያ ግንባር ተርፈው የመጡና ዛሬ ድረስ በህይወት ያሉት "መንቀሳቀስ በነበረብን ሰዓት ለመነሳት ዝግጅት እንደጀመርን ሆን ተብሎ አንዳንድ ዝግጅቶች፣ ልምምዶች እንድናደርግ ተደረገ" የሚሉ ናቸው፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ 4 ነገሮች ይጠቀሳሉ፡፡ 1. መንግስቱ ለድል ቸኩለው የተሰጠውን አስተያየት ባለመቀበላቸው፣ 2. በመንግስቱ ላይ ቂም የነበረባቸው አዝማቾች በመኖራቸው፣ 3. መብረቅ ዕዝ ሰዓት አለማክበሩ፣ 4. የወያኔ ጦር ለሻዕቢያ ገስግሶ መድረሱ የሚሉ ናቸው፡፡ ብቻ እንደማይሆን ሆነ፡፡

ከዚህ በኋላ ነገሩ ሁሉ ተበላሽቷልና ከአልጌና በኩል የተነሳው ውቃው ዕዝ በከፍተኛ መስዋዕትነት ከናቅፋ እስከ ሱዳን ጠረፍ የሚደርሰውን ካታር የተባለ ሰንሰለታማ ተራራ ጥግ ደርሶ ለመቆም ተገደደ፡፡ ከከርከበት በኩል እንዲያጠቃ የታዘዘው ናደው ዕዝ በውጤታማ ውጊያ ተጉዞ የናቅፋ ከተማን ለመያዝ 8 ኪሎ ሜትር እንደቀረው መግፋት ተስኖት ቆመ፡፡ያ ሁሉ የአገር ሐብት፣ ያ ሁሉ ጥሪት፣ ያ ሁሉ ወጣት ዜጋ ወደ ትቢያነት ተለወጠ፡፡የቀይ ኮከብ ዘመቻ ትርፉ ኪሳራ ሆነ፡፡ "ኦሮማይ" እንደማለት፡፡ ደራሲው ከውጊያው በፊት በብዕሩ ያሰፈረው ጽሁፍ በጦር ሜዳ ላይ ሲተገበር ታዬ፡፡

በወቅቱ ድልን የጠበቀ ዜጋ ሁሉ አንገቱን ደፋ፤ "እንዴት ሊሆን ቻለ?" ብሎ ያልጠየቀ ዜጋ የለም፡፡ ለውድቀት ምክንያት የሆነው ክስተት እንዲጣራና በዘመቻ ጽ/ቤቱ መምሪያ ተጠንቶ የውሣኔ ሀሳብ እንዲቀርብ ጓድ ሊቀመንበር አዘዙ፡፡ አጣሪ ቡድኑ ለውድቀት ምክንያት ያላቸውን ዘገባዎች አቀረበ፡፡ ዘገባውን ተመርኩዞ የተቋቋመው የጦር ፍርድ ቤት

ባሳለፈው ውሣኔ መሰረትም የመብረቅ ዕዝ አዛዥ ብርጋዴል ጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ላይ የእስር ቅጣት፣ የ21ኛው ተራራ ክፍለ ጦር አዛዥ ኮሎኔል ውብሸት ማሞ የሞት ቅጣት፣ የክፍለ ጦሩ 47ኛው ብርጌድ አዛዥ ሌተናል ኮሎኔል ስለሺ አስፋው ማዕረጋቸው ተገፎ እንዲታሰሩ ሲል ብይን ሰጠ፡፡ ኮሎኔል ውብሸትን በሠራዊቱ ፊት ወስደው ረሸኗቸው፡፡ በጄኔራል ቁምላቸው ላይ መንግስቱ ያሳዩት ርህራሄ ብዙዎችን አስገረመ፡፡

በዚህ ሽንፈት ሊቀመንበሩ ምን ያህል እንደተበሳጩ ማሰብ አይከብድም፡፡ ባየነው መልኩ ቀይ ኮከብ በጥቂር ደመና ተዳፍኖ እንዳለ ዕዞች ይዞታቸውን አጠናክረው ባሉበት ሆነው እንዲደራጁ ተደረገና በተከታታይ ቀይ ኮከብ ሁለት፣ ሦስት... አራት... እየተባለ በተለያዩ የዘመቻ ስያሜዎች የሻዕቢያን ጉዳይ ዳር ለማድረስ በእጅጉ ተሞከረ፡፡ በከባድ ትንቅንቅ አንዴ ሲያስለቅቁ፣ መልሰው ሲለቁ፣ ሲያጠቁ፣ ሲከላከሉ... ቆዩ፤ አልተቻለም፡፡ ለምን? የናቅፋ ተራሮች ለሻዕቢያ ምትክ የሌለው የተፈጥሮ ደጀን ስለሆኗቸው፡፡ እናም ከተጠቀሰው ቢሊዮን ገንዘብ ውስጥ ግማሹ አመድ ቢሆንም ክፊሉ ግን ለኤርትራ ህዝብ ልማት በመዋሉ እንደኪሳራ አይቆጠርም፡፡

የሰሜኑ ጦርነት ሲባል ከሻዕቢያ ጋር ብቻ እንዳልነበር ይታወቃል፡፡ ከሻዕቢያ በኋላ የተነሳው ህወሓት ሌላው የደርግ መንግስት ተቃዋሚ ሆኖ ነፍጥ ያነሳው ገና በማለዳ ነበር፡፡

በምዕራብ ትግራይ ሽሬ አውራጃ፣ ደደቢት በምትባል በረሃማ ቀበሌ የካቲት 11 ቀን 1967 ዓ.ም ጥቂት የዩንቨርስቲ ተማሪዎችና የአካባቢው መሪዎች "ሕወሓት" "ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ"ን መሠረቱ፡፡ ራሳቸውንም ዳግማዊ ወያኔ ሲሉ ሰየሙ፡፡ ህወሓት የሚለውን መጠሪያ ይፋ ከማድረጋቸው በፊትም በተለያዩ ምህፃረ ቃላቶች ይጠሩና ይታወቁ ነበር፡፡

በጃንሆይ ዘመን በተለያዩ የኢትዮጵያ ግዛቶች ላይ የገበሬዎች አመፅ ተቀጣጥሎ እንደነበር አይተናል፡፡ በወቅቱም የገበሬዎችን አመፅ በቀላሉ ማርገብ ተችሏል፡፡ ከእነዚህ ውስጥም የትግሬ ጠቅላይ ግዛት አንዱ ነበር፡፡

በአፄ ዮሐንስ 4ኛ የስልጣን ዘመን የኢትዮጵያ ማዕከል ሆና የቆየችው ትግራይና አካባቢዋ በ1882 ዓ.ም ንጉሠነገስቱ በጦርነት ላይ ከተሰውበት ጊዜ ጀምሮ፤ የትግራይ መሣፍንትና መኳንንት የሆኑት ሁሉ የቀያሞውን አይነት ክብርና ተሰሚነት ማግኘት አልቻሉም፡፡ ዳር አገር በመሆናቸውም የፖለቲካ ተሳትፏቸውና ተጠቃሚነታቸው የቀዘቀዘ ሆኖ ነበር፡፡ ያም ቢሆን ለኩርፊያና ለሽፍትነት የሚጋብዝ ባለመሆኑ ለረጅም ጊዜ በግዛቱ ላይ ሠላም ሰፍኖ ቆይቷል፡፡



ከኢጣሊያ ዳግም ወረራ በፊት ግን በመንግስትና በራያና አዘቦ ህዝብ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት፣ እሱንም ተከትሎ የደረሰው ደም መቃባት ለአካባቢው ሠላም መደፍረስ የመጀመሪያው ሆኗል፡፡ ከንግስት ዘውዲቱ የግዛት ዘመን ጀምሮ ማዕከላዊ መንግስቱን ሲፈታተንና በየጊዜውም ከሚላክበት ጦር ጋር በሽፍትነት ይፋለም የነበረው የራያና አዘቦ ህዝብ ይህን ተግባሩን በቀጠለበት ሁኔታ የኢጣሊያ ወረራ ተከሰተ፡፡ በዚህም ማዕከላዊ መንግስቱን ለመበቀል ምቹ ሁኔታ ተፈጠረላቸው፡፡ከማይጨው ጦርነት ሸሽቶ ይመጣ በነበረው የኢትዮጵያ ጦር ላይ ያደረሱት ግፍም የሚረሳ አይደለም፡፡

ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ሙሉ ለሙሉ ለቃ ከወጣች በኋላም የጃንሆይ መንግስት እስኪደላደል ድረስ በነበረው የጊዜ ክፍተትና ጣሊያኖች ትተውት የሄዱትን መሣሪያ በገፍ ማግኘት ቀላል ስለነበር በነፃነት ማግስት የመጀመሪያውን የተደራጀ አመፅ ማካሄድ ቻሉ፡፡ ይህም በነፃነት ማግስት በትግሬ ጠቅላይ ግዛት የተቀሰቀሰው የመጀመሪያው የ"ወያኔ" አመፅ ነው፡፡

የራያና አዘቦ ህዝብ አመፁን የለኮሰውም እንደመጀመሪያ ተግባሩ በአፋሮች ላይ ከፍተኛ ዝርፊያ በመፈፀም ሲሆን፤ በዚህም የማዕከላዊ መንግስቱን የበቀል እርምጃ በራሱ ላይ አስከተለ፡፡ የመንግስት ማጥቃትና የአማፅያኑ የመካላከል ተግባር እየተጋጋለ ሄዶ በመጨረሻ አማፅያኑ ከመከላከል ወደማጥቃት አመሩ፡፡ ይህ ሁኔታ ከተራ የሽፍትነት አመፅ ወደ ፖለቲካዊ አመፅ ተሸጋገረ፡፡

አማፅያኑ የመጀመሪያ ድላቸውን ያገኙት ግንቦት 14 ቀን 1935 ዓ.ም በተንቤን አውራጃ "አዲ አቡን" በተባለ ስፍራ ነው፡፡ ከዚያም በተከታታይ መቀሌ አጠገብ የሚገኙትን ቅዊሓንና እንዳ እየሱስን በቁጥጥር ስር አዋሉ፡፡ በመጨረሻም የጠቅላይ ግዛቱን ዋና ከተማ መቀሌን ሙሉ ለሙሉ ያዟት፡፡

ለዚህ ድል የረዳቸው ዋና ምክንያት የህዝቡን ቅሬታ ዘውጋዊ ወይም ጎሳዊ ርዕዮት በመስጠት ማስተባበር የቻለው የብላታ ኀይለማርያም ረዳ አመራር ነው፡፡

የአመፁ ሰፋት፣ ጥልቀትና እድገት መንግስትን ክፉኛ ስላስደነገጠው በአርበኝነቱ ዘመን በፈፀሙት ጀብድ ስመጥርነትን ያተረፉትን ራስ አበበ አረጋይን የጦር አዝማች አድርጎ ላከ፡፡ ከሁኔታው አስጊነት አንፃርም በወቅቱ በኢትዮጵያ ከነበሩ የእንግሊዝ ጦር ባለስልጣኖችን እርዳታ መጠየቅ አስፈልጎ ነበር፡፡ በእንግሊዝ ይሁንታም የጦር አውሮፕላኖች ማግኘት ተችሎ ቀዳማዊ ወያኔን በምድርና በአየር ውጊያ ማሸነፍ ተቻለ፡፡ መስከረም 25 ቀን 1936 ዓ.ም ሙሉ ለሙሉ ድል የሆነው የአማፅያኑ ጦር ተበታተነ፡፡

ቀዳማዊ ወያኔ ትግሉን የጀመረው ምስራቃዊ ትግራይን መነሻ በማድረግ ነበር፡፡ ዳግማዊ ወያኔ ደግሞ ከመረብ ወንዝ በስተደቡብ በሚገኘው በምዕራብ ትግራይ መነሻውን አድርጎ ከ31 ዓመታት በኋላ የአርነት ንቅናቄውን እንደዋዛ ጀምሮ እየተጠናከረ ቀጥሏል፡፡

የመጀመሪያው ወያኔ ርዕዮቱን ዘውጋዊ አድርጎ የተነሳ ሲሆን፤ ሁለተኛው ወያኔ ደግሞ ከኢትዮጵያ የተማሪዎች ንቅናቄ በወረሰውና "የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል" በሚለው መርህ የሚመራ ነበር፡፡ቀዳማዊ ወያኔናዳግማዊ ወያኔ የሚመሳሰሉበት ሁኔታ ኖሮ ሳይሆን፤ህወሓት ለራሱ ፕሮፖጋንዳ ታሪካዊ መሰረት ለመስጠት የፈጠረው ነው፡፡

አካባቢው ዳር አገር በመሆኑ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ለማድረግ ምቹ ቢሆንም፤ በአካባቢው ኅብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት የግድ ነበርና፤ ለዚህ የሚረዳ በቂ ምክንያት በጠቅላይ ግዛቱ ውስጥ መኖሩ ለዳግማዊ ወያኔ የበለጠ ምቹ ሁኔታ ፈጠረለት፡፡ ይህም ከ1950ዎቹ አጋማሽ አመታት ጀምሮ በግዛቱ ውስጥ የተከሰተው ተደጋጋሚ ድርቅና የኢኮኖሚ ችግር ነው፡፡ ከዚህም በላይ የቀድሞ ባለባት ሹማምንት የፖለቲካ ማዕከላዊነት በማጣታቸው ምክንያት ሲሰማቸው የቆየው ቁጭት ስለነበር፤ በጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦች የመሰረቱትን የነፃነት ንቅናቄ በግዛቱ የሚኖረው ሁሉም ወገን የየራሱን መነሻ ምክንያት መሰረት በማድረግ ለመደገፍና ለማበረታታት ዝግጁ ነበር፡፡ ለዚህም ነው በተመሠረተ በአጭር ጊዜ ውስጥ በቂ የሚባል የሰው ኃይል፣ የስንቅና የትጥቅ አቅርቦቱ ሳይቸግረው ባለበት ፈጥኖ ተደራጅቶ የደርግ መንግስትን መፈታተን የቻለው፡፡

ህወሓት ይዞት የተነሳውን "የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል" የሚለውን የሌኒን መርህ ግን ለትግራይ ህዝብ ከማስረዳት ይልቅ ከእሱ ቀድሞ የመገንጠል ዓላማ ይዞ ለተነሳው ለሻዕቢያ መግለፅ ይቀለው ነበር፡፡ ያደረገውም ያንን ነው፡፡ሆኖም ሻዕቢያ የትግራይን የመገንጠል ትግል የኔን ትግል ያዳክምብኛል በሚል የወያኔን የመገንጠል ዓላማ ማኑፌስቶ እንዲያሰወግድ አስገድዶታል፡፡

ለወያኔ የአካባቢውን ህዝብ ድጋፍ ለማግኘት የኢኮኖሚ ችግር ሰለባ መሆኑን መግለፅ ብቻውን በቂ ስለነበር የርዕዮት ትንተና ውስጥ መግባት አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ለሻዕቢያ ግን ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ስለዚህ የ"ገንጣይ" እና "አስገንጣይ" ጥምረት መስርቶ መደጋገፉ ለሁለቱ ቡድኖች ወሣኝ በመሆኑ፤ ከልዩነታቸው ይልቅ አንድነታቸው ጠንክሮ በመቀጠሉ በመጨረሻ የየግል ግቦቻቸውን ዳር ማድረስ ችለዋል፡፡



ደርግ ጊዜያዊ መንግስት በሆነ ማግስት የወሰዳቸው እርምጃዎች፤በተለይም የ60ዎቹ ግድያና ሌሎች በፍርደ ገምድልነት የተደረጉ ነገሮች መደራረባቸውም ለሸመቁ ተቃዋሚዎች ድጋፍና ትኩረት አስገኝቶላቸዋል፡፡የአገር ውስጥ ብቻም ሳይሆን የውጭ አገራት ድጋፍን በተከታታይ አመታት ሊያገኙ የቻሉት የደርግ አምባገነንነት በየጊዜው እየጎላ በመሄዱ ነው፡፡

ደርግ ለአብዮቱ ሲል የሚወስዳቸው ጥንቃቄ አልባ እርምጃዎች በአብዮቱ ደጋፊዎች ዘንድ ተወዳጅ ያደርገኛል ብሎ ሲያስብ ራሱን ለጠላት ፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ አድርጎ ማቅረቡን ለደቂቃ አስቦት አያውቅም፡፡

ህወሓት "ወያኔ" የሚለውን ወኔ ቀስቃሽ ስያሜ ይዞ የትጥቅ ትግል ሲጀምር ልክ እንደሻዕቢያ የመጀመሪያ ስራው ያደረገው በግዛቱ ውስጥ የበላይነቱን ማረጋገጥ ነበር፡፡ ስለዚህም በቅድሚያ ከሦስት ተቀናቃኝ ድረጅቶች ጋር መፋለም ነበረበት፡፡ በመጀመሪያ ከእሱ ቀድሞ የተደራጀውን "የትግራይ አርነት ግንባር"ን ማስወገድ ቻለ፡፡ ይህን ግንባር ለማስወገድ ብዙ ድካም አልነበረውም፡፡ ሁለተኛውን "የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት" በእንግሊዝኛ ምህፃረ ቃሉ "ኢዲዩ"ን ግን ብርቱ የሆነ ውጊያና ከፍተኛ የህይወት መስዋዕትነት በመክፈል ነው መደምሰስ የቻለው፡፡

ኢዲዩን ከምዕራብ ትግራይ ጠራርጎ ካስወጣ በኋላ ቀጣዩን ፍልሚያ ያደረገው በሰሜን ምስራቅ ትግራይ አሲምባ በምትባለው ተራራማ ቦታ ከመሸገው ከኢ.ህአፓ ሠራዊት ጋር ነበር፡፡ ኢ.ህአፓ በከተማው ትግል ስኬታማ መሆን ሳይችል ሲቀር ወደ ገጠር አምርቶ አሲምባ ላይ ቢመሽግም ለአካባቢው እንግዳ ነው፡፡ ኢ.ህአፓ አሲምባን የመረጠው በሁለት ምክንያቶች ሲሆን፤ አንዱ ከመንግስት ጥቃት ለመሸሽ፣ ሌላው በትግራይ ያለው ሽማቂ ቡድን የኅብረብሔራዊነት ዓላማ ካለው አብሮ ለመቀናጀትና ለመታገል ነው፡፡

ህወኀትም ኢ.ህአፓም ግራ ዘመም ከሆነው ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ አብራክ የወጡ ድርጅቶች ይሁኑ እንጂ፤ ዓላማና ግባቸው እጅግ የተራራቀ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ገሃድ በሆነው ትግላቸው ውስጥ ስውር የሆነ የየግል ዓላማ ነበራቸው፡፡

የትግሉን ይዘት በሚመለከት ኢ.ህአፓ "በኅብረብሔራዊ ድርጅት የሚመራ የመደብ ትግል"ን በቀዳሚነትና በአፅንኦት ሲያስቀምጥ፤ ሕውሓት ግን "ትግሉ ሊሰምር የሚችለው የተለያዩ ጭቁን ብሔር ብሔረሰቦች በራሳቸው ድርጅት አማካኝነት ትግላቸውን ጀምረው ከዚያ በኋላ የኅብረት ግንባር ሲፈጥሩ ነው" የሚል አቋም ያዘ፡፡ ከዚህ ልዩነት በተጨማሪም ሕወሓት ሙሉ እምነቱን በገጠር የትጥቅ ትግል ላይ

ሲያሳርፍ፤ ኢህአፓ ደግሞ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረው በከተማ ነው ብሎ ስላሰበ በከተማ የትጥቅ ትግል ላይ እምነቱን አሳድሯል፡፡በተጨማሪም ኢህአፓ እንደ ነጭ ማርክሲስትነቱ አርሶአደሩ አብዮታዊ ሀይል አይደለም ላብ አደሩ እንጅ ብሎ በማመኑ ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ ግን (የሻዕቢያን ከጀርባ ሆኖ በሰርጎ ገቦቹ አማካኝነት ኢህአፓን መጠቀሚያ ማድረጉን ሳንዘነጋ) ዋናው ልዩነታቸው በህወሓት ውስጥ የነበረው የመገንጠል መሻትና "በኢህአፓ ውስጥ የነበረው መገንጠልን ያለመሻት የፀባቸው መንስዔ ነው፡፡

በዚህ ልዩነት ሕወሓት የኢህአፓን አባላት ቢቻል በእሱ አቋም እንዲስማሙ አድርጎ ማሳመንና መቀላቀል፣ ካልተቻለ ያመኑለትን መርጦ ወስዶ የቀሩትን መደምሰስ፣ ካልሆነም ከአካባቢው ማባረር ነበረበት፡፡ ያደረገውም ይሄንኑ ነው፡፡

በዚህ መሠረት ግሚሱ የኢህአፓ አባላት ተደመሰሰ፡፡ጥቂቶቹ ተባባሪ ሆነው ተቀላቀሉ፡፡ የቀሩት ጓዛቸውን ጠቅልለው ወደ ጎንደርና ወደ ወሎ አፈገፈጉ፡፡ አንዳንዶቹም የከተማ ሽብራቸውን ቀጠሉ፤ሌሎችም ለደርግ እጃቸውን ሰጥተው ከደርግ ጋር መስራት ጀመሩ፡፡ደርግም ምልስ የኢህአፓ አባላትን እጁን ዘርግቶ ተቀበላቸው፤የድርጅታቸውን ሚስጥር አወጡ፤በደርግ ተይዘው የሚታሰሩ አባላትን መርማሪ ሆነው እስኪሰሩ ድረስ ለደርግ ታማኝ ሆነው ዘለቁ፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለም የየራሳቸውን ብሔር እንዲያደራጁ ወደየክልላቸው ቀድመው የተላኩ ምልምሎች የተገኙት በዚህ አጋጣሚ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡

በዚህ ዓይነት በትግራይ ግዛት ውስጥ ብቸኛው የትጥቅ ትግል አራማጅ ህወሃት ሆነ፡፡ እነዚህ ጅምር የነፃነት ንቅናቄዎችና የውስጥ ፍጭቶች ለሻዕቢያ ሠርግና ምላሹ ነበሩ፡፡ ኅብረብሔራዊነት፣ ብሔረተኝነት ወዘተ ... ለሻዕቢያ ምኑም አይደሉም፡፡ ብቻ ኢትዮጵያ ውስጥ ሽብሩም፣ ተቃውሞውም፣ ፍጅቱም ይፋፋምለት እንጂ ሌላው ሁሉ ነገር አያገባውምም፣ አይገባውምም፡፡ የእሱ ስራ በኢትዮጵያውያን የግራ ኃይሎች ውስጥ የራሱን ዓላማ ማስፈፀም የሚችልበት፣ የመገንጠል ግቡን የሚያፋጥኑለትን ልዑካን ማሰማራት ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ምቹ ሆኖ ያገኘው ከሕወሓት ይልቅ ኢህአፓን ነበር፡፡

መጀመሪያ ላይ ደርግ ሕወሓትን ከመጤፍ አልቆጠረውም ነበር፡፡ ለድርጅቱ መፈጠር ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎችን ትኩረት በመንፈግ አንድ የሻዕቢያ ተቀፅላ ቡድን አድርጎ ነበር የወሰደው፡፡ ስለዚህም ደርግ ሙሉ ኃይሉን ያዘመተበት ሻዕቢያ ከተመታ ሕወሓትም አብሮ ይከስማል ብሎ ጥርጣሬ አልባ ግምት ውስጥ ገባ፡፡

ነገር ግን ሕውሓትና ሻዕቢያ አንድ አልነበሩም፡፡ አንድነታቸው ሰፊ፣ ልዩነታቸው ጠባብ የሆኑ የተነጣጠሉ ቡድኖች ናቸው፡፡ ይልቁንም



ሻዕቢያ መጀመሪያ ላይ ከሕወሓት ይልቅ ቀድሞ ወደጎለበተው ወደ ኢህአፓ ነበር ያተኮረውና በኅብረት ለማመፅ ሁኔታዎችን ያመቻቸው፡፡ ሆኖም ኢህአፓ ከትግራይ ተጠራርጎ ሲወጣ ፊቱን ወደ ሕወሓት አዞረ፡፡

ሕውሓት በመላ ትግራይ የበላይነቱን ካሰፈነ በኋላ የተመሠረተው ግንኙነትም የፍቅር ሣይሆን የጥቅም ብቻ ነበር፡፡ የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ አንድ ህዝቦችን ለመከፋፈል ሲል ተክሎት በሄደው መርዛማ ችግኝ ምክንያት በሁለቱ የመረብ ወንዝ ተዋሳኝ ወንድማማች ህዝቦች መካከል ከመቃቃርም አልፎ በጣም በጥቂቱ መናናቅም ይታይ ነበር፡፡ ሆኖም ከጃንሆይ ዘመን ጀምሮ የተፈጠረው ውህደት ተለያይተውና ተቃቅረው የነበሩ ህዝቦችን አንድ አድርጎ ወደ ቀድሞው ፍቅራቸው መልሷቸው ነበር፡፡ በዚህ መሠረት በሁለቱ ህዝቦች መካከል አንዳች ልዩነት አለመኖሩን ስንረዳ፤ የሁለቱ ህዝቦች ተቆርቋሪ ሆነው የትጥቅ ትግል በጀመሩ የስልጣን ተፋላሚዎች ዘንድ ግን የተካረሩም ባይሆኑ ልዩነቶች አልጠፉም፡፡

ሕወሓት "ብሔር ብሔረሰቦች" ሲል ሻዕቢያ ግን በኤርትራ ትግል ውስጥ ብሔር ብሔረሰብ የሚባል አጀንዳ ፈፅሞ የለም ባይ ነበር፡፡ ሕወሓት ሶቭየት ኅብረት ለደርግ በምታደርገው እገዛ ምክንያት ጠንካራ ፀረ ሶቭየት አቋም ሲወስድ፤ ሻዕቢያ ግን ፀረ ሶቭየት አቋም አልያዘም፡፡

የሕወሓት የጦር ስልት በደፈጣ ውጊያ ላይ ሲያተኩር፤ ሻዕቢያ ግን መደበኛ ውጊያን መርጧል፡፡ በዚህም ሕወሓት ሻዕቢያን ተቻኩሎ ወደ መደበኛ ጦርነት በመግባቱ ክፉኛ ይተቸው ነበር፡፡ "ሳንደራጅ አታስጨርሰን፤ ተረጋጋ" መሆኑ ነው፡፡

እነዚህን በመሳሰሉ የሀሳብና የዘዴ ልዩነቶች ሲተቻቹ ከቆዩ በኋላ፣ የደርግ የማጥቃት እርምጃ እየጠነከረ ሲሄድና በተለይም ከቀይ ኮከብ ዘመቻው ከ1974 ጀምሮ በነበሩት ተከታታይ አመታት፤ የነበራቸውን ጥቃቅን ልዩነቶች ሁሉ እርግፍ አድርገው ትተው በጋራ ርብርብ፣ በጋራ ጠላታቸው በደርግ መንግስት ላይ ተነሱ፡፡ ውድቀቱን ለማፋጠንም በቁርጠኝነት ተፋለሙ፡፡

እነሱን ለማጥፋት ደርግ የወሰዳቸው ተደጋጋሚ እርምጃዎች ከሸፉበት፡፡ ቢቸግረው ለኤርትራና ለትግራይ የራስ ገዝ አስተዳደር ስልጣን ሊሰጥ ሞከረ፡፡ ይህን ግን የኃይል ሚዛኑ ወደነሱ ማዘንበሉን የተረዱት ሁለቱ ቡድኖች ሊቀበሉት አልፈቀዱም፡፡

ሻዕቢያና ሕወሓት ሲመች በጥምረት ሳይመች በተናጠል ደርግን በፅኑ ሲፋለሙ እነሱ ተሳዳጅ ደርግ አሳዳጅ ሆኖ የዘለቀው ለጥቂት ዓመታት ነው፤ እያደር ግን ደርግ ተሳዳጅ እነሱ አሳዳጅ ሆነው ተገኙ፡፡

ግራ የተጋባው ደርግ አብዮታዊ ሠራዊቱን እንደገና በአዲስ መልክ አደራጅቶ በአራት ዕዞችና በውስጡም የተለያዩ ኮሮችን አቅፎ የሚይዝ

ከማድረጉም በላይ "የሦስት ማዕዘን ዕዝ" በሚል 1ኛ አዛዥ፣ 2ኛ የፖለቲካ ኃላፊ፣ 3ኛ የወታደራዊ ደህንነት ኃላፊ የሚባሉ ባለሥልጣኖችን በጦሩ ላይ ሹሞ ዝብርቅርቁን አወጣው፡፡

የዕዙ ማዕከል ዋና አዛዡ ቢሆንም የፖለቲካና የወታደራዊ ደህንነት ኃላፊዎች በዋና አዛዡ ስራ ላይ በቀጥታ ጣልቃ መግባት ይችላሉ፡፡ በተለይ የፖለቲካ ኃላፊው በአዛዡ ላይ ጣልቃ መግባት ብቻ ሳይሆን ትዕዛዙንም መሻር ይችላል፡፡ ይህ ያልተለመደ አደረጃጀት ሙያና ችሎታው ያለውን አዛዥ ሙያው የሌላቸው ኃለፊዎች ሊገድቡት እንዲችሉ ከማድረጉም በላይ፤ የእኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ፉክክሩን ዋና ስራቸው አድርገው እንዲቀጥሉ በር ከፈተ፡፡ ሽንፈት ሲደርስም የሱ ችግር ነው፣ የእኔ አይደለም ተብሎ መጠቋቆም ሆነ፡፡ ሠራዊቱ ዋና አዛዡን ለይቶ ማወቅ ተሳነው፡፡

ይህ አይነቱ ከሶቭየት የተኮረጀ የቀዩ ጦር ስልት ዓላማው አፈንጋጭነት እንዳይፈጠርና በአንድ አዛዥ ክህደት ችግር እንዳይደርስ አጥብቆ ለመያዝ ነበር፡፡ ሆኖም በእኛ አገር ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ ቅድመ ዝግድቶች ይቀሩ ነበር፡፡ የታሰበው ሳይሆን ቀርቶ አደረጃጀቱ የጣት መቀሳሰሪያና የአጥፊና ጠፊ መድረክ ሆኖ ቁጭ አለ፡፡

ሻዕቢያን ከኤርትራ፣ ሕወሓትን ከትግራይ ለመደምሰስና ሙሉውን የኢትዮጵያ ድንበር ለማስከበር ይቻል ዘንድ ሠራዊቱ በሰው ኃይል ጠንክሮና በዕዝ ደረጃ ራሱን ችሎ እንዲደራጅ፣ ግዳጁን የመወጣት ብቃትም እንዲኖረው ታስቦ የተደራጀው አብዮታዊ ሠራዊት፤ 1. አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት በሜጀር ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ አዛዥነት፣ የዕዝ ቀጠናው ምስራቅ ኢትዮጵያ ሆኖ የሰው ኃይሉ 30,498፣ 2. ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት በሜጀር ጄኔራል ረጋሳ ጅማ አዛዥነት የዕዝ ቀጠናው ኤርትራ ራስ ገዝ ሆኖ የሰው ኃይሉ 124,024፣ 3. ሦስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት በሜጀር ጄኔራል ሙላቱ ነጋሽ አዛዥነት የዕዝ ቀጠናው ትግራይ፣ ጎንደርና ወሎ ሆኖ የሰው ኃይሉ 107,407፣ 4. አራተኛው አብዮታዊ ሠራዊት በሜጀር ጄኔራል ጌታቸው ሽበሺ አዛዥነት የዕዝ ቀጠናው ምዕራብና መሀል ኢትዮጵያ ሆኖ የሰው ኃይሉ 20,700 ተደርጎ፣ በስራቸው ልዩ ልዩ ኮሮችና ክፍለ ጦሮች አቅፈው ተደራጁ፡፡

ሦስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት በጄኔራል ሙላቱ ነጋሽ ዋና አዛዥነት ከተቋቋመ በኋላ በትግራይ ላይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታወጀ፡፡ ሻምበል ለገሰ አስፋው የትግራይ ራስ ገዝ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አስተዳደር የበላይ አስተዳዳሪ ሆኖ ተሾመ፡፡ በአዋጁ አማካኝነት በቀጥታ የሠራዊቱ የበላይ አዛዥ ሆነ ማለት ነው፡፡

ለገሠ አስፋው ተሹሞ ሄዶ መቀሌ እንደደረሰ በፍጥነት ሦስተኛውን አብዮታዊ ሠራዊት "በቁልፍ ወታደራዊ ቦታዎች ላይ ጠላት



ሠፍሯል፣ ሠራዊታችን፣ በሚገባ ተደራጅቷል፣ ስለዚህ ከየአቅጣጫው ተወርውሮ ይምታው!" ሲል አዘዘ፡፡

ሕወሓትም በበኩሉ፤ "ጦሩ ሲወረወር ተሰወር" የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶ ስልታዊ ማፈገፈግ አደረገ፡፡ በዚህ አይነት የሚለቀቁ ቦታዎችን በተነጣይ ክፍል እያስጠበቁ ሲገሰግሱ የሠራዊቱ ኃይል እያነሰ ቢበታተንም ድል ያልሆነ ድል መሰል ተግባር ሆኖ ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ሽፋን ተሰጠው፡፡ ምርኮ ተብለው ጥቂት መሣሪያዎች በመገናኛ ብዙሃን ታዩ፡፡ ቀጣይነት ግን አልነበረውም፡፡ ይልቁንም በጄኔራሉና በሻምበሉ መካከል የነበረው የታዥነትና የአዛዥነት አለመጣጣም እየተካረረ ሄዶ በየጦር ግንባሩ የሚታየውን ችግር አስተውሎ የጋራ የመፍትሄ እርምጃ መውሰድ ተሳናቸው፡፡

ብዙም ሳይቆይ የቁርጡ ቀን ደረሰና በ1980 ዓ.ም ከህዳር 27 እስከ 30 ባሉት ሦስት ተከታታይ ቀናት ሻዕቢያ በሳህል አውራጃ ውስጥ በሚገኙ የናደው ዕዝ ክፍለ ጦሮች ላይ ጠንካራ በትሩን አሳረፈ፡፡ በ15ኛው ክፍለ ጦርና በ22ኛው ተራራ ክፍለ ጦር ላይ ያረፈው ምት ከቀይ ኮከብ ዘመቻ በኋላ የመጀመሪያው ከባድ ውጊያ ሆኖ "አፋቤት የተባለውን ቁልፍ ወታደራዊ ቦታ ሻዕቢያ በቁጥጥሩ ስር አደረገው፡፡

በዚህ ወቅት የናደው ዕዝ አዛዥ ብርጋደር ጄኔራል ታሪኩ ዐይኔ ለአለቆቻቸው ሳያሳውቁ ሠራዊታቸውን ትተው አስመራ ከተማ ነበሩ፡፡

እኒህ ጄኔራል ወደ ሳህል ተመድበው ከመሄዳቸው በፊት መቀሌ አካባቢ ለሰፈረው ጦር አዛዥ ሆነው በ1970ዎቹ ይሰሩ ነበር፡፡ በዚያ ወቅት ወያኔ "ዘመቻ አግአዚ" (አግአዚ ኦፕሬሽን) ብሎ በሰየመው እስረኞችን የማስለቀቅ ድንገተኛ ወረራው ሲከሰት በወህኒ ቤቱ ዙሪያ የሚገኘው የጥበቃ ኃይል ከአቅም በላይ የሆነ ወረራ እንደመጣባቸው ገልፀው፤ እርዳታቸውን ሲጠይቁ ጄኔራሉ "የወህኒ ቤት ጠባቂ አይደለሁም" የሚል መልስ ሰጥተው በመቅረታቸው የወያኔ ኃይል ያለ ችግር ወህኒውን ጥሶ ገብቶ የራሱን ሰዎች ስም እየጠራ በ15 ደቂቃ ውስጥ ይዞ ሄዷል፡፡ (ነበር ቁጥር 2)

በተጨማሪም የሊቀመንበሩንም ሆነ የሌሎች አዛዦቻቸውን ትዕዛዝ "አላመንኩበትም" እያሉ ከመፈፀም ይቆጠቡ እንደነበርና በሁሉም ዘንድ ጥርስ ውስጥ የገቡ ጄኔራል መሆናቸው ይነገርላቸዋል፡፡ አሁን ደግሞ የአፋቤት ውድቀት የመጣው በጄኔራል ታሪኩ ዐይኔ ጥፋት ነው ተባለና ያለፍርድ ተረሸኑ፡፡ እንዲሁም ብ/ር/ጄ/ል ከበደ ጋሼ ድል ከሆኑ ሁለት ክፍለ ጦሮች ውስጥ አንዱን ይመሩ ስለነበር በጥፋተኝነት ሙሉ ማዕረጋቸው እንዲገፈፍ ተደረገ፡፡ እንዲህ ያለው ተግባር በጦሩ ፊት በተግባር መፈፀሙ ደግሞ የጦሩን ስሜት የሚጎዳና ሞራሉንም የሚነካ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

በአፋቤት ጦርነት 20 ሺህ የደርግ ሠራዊት በአንድ ጊዜ ያለቀ ሲሆን፤ ስፍር ቁጥር የሌለው የጦር መሣሪያ በሻዕቢያ እጅ ገባ፡፡ ይህ ቦታ ለሻዕቢያ መጀመሪያ ወደ ምፅዋ፣ እንዲሁም ወደ አስመራ መረማመጃ ሆነው፡፡ በጦርነቱ የወደፊት አቅጣጫ ላይም ለሻዕቢያ ድል መፋጠን ትልቁን ሚና ተጫውቷል፡፡ በርካታ መኮንኖች በመማረካቸውም ሚስጥሩን ሁሉ፣ የሠራዊቱን አሠፋፈር ሳይቀር በቀላሉ ለመረዳት ለሻዕቢያ ጠቅሞታል፡፡

ሻዕቢያ እስከ መጋቢት ወር ድረስ አፋቤትን የማፅዳትና ሙሉ ለሙሉ የግሉ ለማድረግ በወሰደው ተከታታይ የማጥቃት እርምጃ ከነሙሉ የጦር ግምጃ ቤቷ ተረከባት፡፡ ዘጠኝ የሶቭየት የጦር አማካሪዎችን ጨምሮ ማረከ፣ የናደው ዕዝ በተጠቀሰው ወር ተናደ፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ኤርትራን ሊነጠቅ ምንም እንዳልቀረው እየተረዳ ነበር፡፡

በትግራይ ላይ የተሰማራው የሶስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት 604ኛ ኮር የሕወሓትን ስልታዊ ማፈግፈግ መነሻ አድርጎ ሲገሰግስና ቅጥ ባጣ ሁኔታ እየሳሳ ሲሄድ፤ በተናጠል ምት እየተደመሰሰ ራሱን መከላከል በማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡

በየካቲት ወር 1981 ዓ.ም በሻዕቢያ ሜካናይዝድ ጦር ታግዞ በምዕራብ ትግራይ የምትገኘውን ሽሬ እንዳስላሴን በከፍተኛ መስዋዕትነት መቆጣጠር ቻለ፡፡ 40 ሺ ወታደር የያዘው 604ኛ ኮር ሙሉ ለሙሉ ተደመሰሰ፡፡ ሕወሓት የምስረታውን የልደት ቀንን ጠብቆ የካቲት 11 ያደረሰው የ18 ሰዓታት ጥቃት ሽሬን መቆጣጠር ሲያስችለው፤ ብርጋዴል ጄኔራል ክንፈና ብርጋጄል ጄኔራል ገሞራውን ጨምሮ በርካታ መኮንኖችን መማረክም ችሏል፡፡ በኢትዮጵያ ጦርነት ውስጥ ጄኔራል ሲማረክ ይህ የመጀመሪያው ነበር፡፡

የአፋ ቤት ድል ለሻዕቢያ ወሣኝ የድል ምዕራፍ እንደሆነው ሁሉ ለሕወሓትም የሽሬ ድል ተመሳሳይ ገፅታ ነበረው፡፡

ቀጥሎ ተመሳሳይ ሽንፈትና ኪሳራ እዳይደርስ በሚል ከየካቲት 18 ጀምሮ የደርግ ሰራዊት ያለውጊያ ከመቀሌ መውጣት ጀመረና ግማሹ ወደ አስመራ፣ ግማሹ ወደ ሰሜን ወሎ ጓዙን ጠቅልሎ እንዲሄድ ተደረገ፡፡ በሚስጥር የተከናወነው ሽሽት በ15 ቀናት ተጠናቆ የካቲት 22 ቀን 1981 ሙሉ ለሙሉ መቀሌ ተለቀቀች፡፡

የደርግ መንግስት ያለአንዳች ውጊያ ለሕወሓት የትግራይን ግዛት አስረከበ፡፡ የሚገርመው ቦታውን ለማስከበር ሰፍሮ የነበረው ጦር "ዘመቻ ቅጣው" በሚል ስያሜ የዘመተ መሆኑ ነው፡፡ ሳይቀጣም፣ ሳይቀጣም ሹልክ አለ፡፡

ከዚህ በኋላ ሕወሓት ትግራይን ደጀን አድርጎ ዘመቻውን ወደ መሐል አገር አስፋፋ፡፡ የትግራይ ወጣትም ወደ እነሱ ከቀድሞው የበለጠ



እየተቀሳቀላቸው የሰው ኃይላቸውን አሳደጉ፡፡ ትግራይን ነፃ አወጣለሁ ብሎ የተነሳው ድርጅት አገር አቀፍ የሆነ ሌላ አጀንዳ ማውጣት ግድ ሆነበት፡፡

ከ"ኢሠፓአኮ" ወደ "ኢሠፓ"

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግስት ደርግ ከምስራቁና ከሰሜኑ ጦርነት ጎን ለጎን ስልጣኑ ሕጋዊ ከለላ ያለውና፤ በህዝብ ተሹሞ የተሰየመ መንግስት ሊያስመስለው የሚችል ተግባር ለመፈፀም ደፋ ቀና ይል ነበር፡፡

ይህም በየካቲት ወር 1972 ዓ.ም ተጀምሮ በ6 ወራት ውስጥ እንዲዋቀር የተደረገውን "የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን" (ኢሠፓአኮ)ን መመስረት ሲሆን፤ አደራጅ ኮሚሽኑ ከተዋቀረ በኋላ ደግሞ አምጦ የሚወልደው "የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ፓርቲ" (ኢሠፓ) የመጨረሻው አውራ ፓርቲ ይሆንና፤ የደርጉን ሊቀመንበር ሌተናል ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምን ብቸኛ መሪ አድርጎ እስከፍፃሜው እንዲዘልቁ ማድረግ ዓላማና ግቡ ነው፡፡

ዓላማው ከግቡ ይደርስ ዘንድም ገና ከጅምሩ በጽኑ መሠረት ላይ መገንባት ነበረበትና የኮሚሽኑ ምስረታ አዋጅ ይፋ ከመደረጉ በፊት በክፍላተ አገራት፣ በአውራጃና በወረዳዎች ላይ ታማኝ ታማኝ የመንግስቱ ተጠሪዎች ከታህሳስ ወር ጀምሮ ቅድመ ስራቸውን እንዲያከናውኑ ተመደቡ፡፡

በየቦታው ቢሮዎችን ማዘጋጀት፣ ተገቢ ሰዎችን መመልመል፣ መሰናክል ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉትን ማጥራት፣ የመንግስቱን መልካም ስብዕና ማንፀባረቅ... የሚሉት ከቅድመ ስራዎች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በኋላ በ"ኢማሌድኅ" ጥላ ስር ተሰባስበው ከነበሩ ድርጅቶች ውስጥ በአባልነት ይሳተፉ ከነበሩ ግለሰቦች ጀምሮ፤ የፖለቲካ ተሳትፎ እስከሌላቸው ግለሰቦች ድረስ፣ ምሁራን፣ የኪነጥበብ ሰዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የፈጠራ ባለቤቶች፣ አምባሳደሮች፣ ሚኒስትሮች፣ ከጦር ኃይሉም፣ ከፖሊስ ሠራዊትም ፣ጡረተኛ አርበኞችም ... ሳይቀሩ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በ ኢሠፓአኮ መስራች ጉባዔ ላይ እንዲሳተፉ ተደረገ፡፡

እነዚህ ከድፍን ኢትዮጵያ ተመርጠው በጉባዔው ለመገኘት የተጋበዙ ዜጎች ቁጥራቸው 2ሺ ሲሆን፤ በታላቁ ቤተመንግስት ጊቢ ውስጥ ባለው የምኒልክ አዳራሽ ጳጉሜ 1 ቀን 1972 ዓ.ም ከጠዋት ጀምረው በመስራች ጉባኤው ላይ በጋራ ተገኝተው ያዳራሹን ግድግዳና ኮርኒስ በጋለ ጭብጨባ ሲያናጉት ዋሉ፡፡

ጉባዔው በማግስቱም ቀጠለና 93 ቋሚ፣ 30 ተለዋጭ አባላት ያሉት ማዕከላዊ ኮሚቴውን ሰየመ፡፡ ከቋሚ የማዕከላዊ አባላት ውስጥ 60ዎቹ መለዮ ለባሾች (ፖሊስን ጨምሮ) እንዲሆኑ ሲደረግ፣ 33ቱ

ሲቪሎች ነበሩ፡፡በዚህም የአማን አንዶምን የመጀመሪያ ዕቅድ ደርግ በመጨረሻ በከፊል መተግበሩን እንረዳለን፡፡

ከተለዋጭ አባላቱ ውስጥ ደግሞ 21ዱ መለዮ ለባሽ፣ 9ኙ ሲቪሎች ናቸው፡፡ በተለዋጮቹ ውስጥ 2ቱ፣ በቋሚዎቹ ውስጥ 26ቱ የደርግ አባላት እንዲሆኑ ተደረገ፡፡ ሁሉንም አባላት በዕጩነት ያቀረቡት ሊቀመንበር መንግስቱ የነበሩ ሲሆን፤ ያለአንዳች ተቃውሞ ይሁንታ ማግኘቱን ቆመው በጋራ ጭብጨባ ያረጋገጡት ደግሞ ሁሉም ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡

ኢሠፓአኮ ከተመሠረተ በኋላ ባደረገው የመጀመሪያ ስብሰባም የአደራጅ ኮሚሽኑ ሊቀመንበር አድርጎ መንግስቱን መምረጡን ለጠቅላላ ጉባዔው ሲያበስር ያ ከፍተኛ ድምፅ ያለው የጋለ ጭብጨባ ያለማቋረጥ ተስተጋባ፡፡

ኮሎኔል መንግስቱ በደርግ ሊቀመንበርነታቸው ላይ የኢሠፓን ሊቀመንበርነት ደርበው ያዙ፡፡ ከዚህ በኋላ ሊቀመንበሩና የመስራች ጉባዔ አባላቱ በሲቪልና በወታደራዊ ሰልፍ የደመቀውን የአብዮቱን 5ኛ ዓመት በዓል በአብዮት አደባባይ አክብረው ወደየመጡበት ተመለሱ፡፡ ወደየመጡበት የተመለሱት የመስራች ጉባዔ አባላት በየክልላቸው ኢሠፓአኮን አቀነቀኑ፡፡ ሊቀመንበር መንግስቱም በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የማዕከላዊ ኮሚቴውን ስራ አስፈፃሚዎች (የፖሊት ቢሮ አባላትን) መርጠው በየዘርፉ መደቡ፡፡

1. ሻምበል ለገሠ አስፋው - የድርጅት ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
2. ሻምበል ፍቅረስላሴ ወግደረስ - የርዕዮተዓለም ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
3. ኮሎኔል ተካ ቱሉ - የዲሲፒሊንና ቁጥጥር ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
4. አቶ ታዬ ጉርሙ - የኅብረት ስራ ማኅበራት ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ
5. ኮሎኔል ብርሃኑ ባይህ - የውጭ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
6. ኮሎኔል ውብሸት ደሴ - የአስተዳደርና ፋይናንስ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
7. ኮሎኔል ገብረየስ ወልደሃና - የአብዮታዊ ጦር ዋና ፖለቲካ አስተዳደር ኃላፊ
8. ሻለቃ ተካልኝ ባልቻ - የማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ኃላፊ ሆነው ተመድበው ስራቸውን ቀጠሉ፡፡

ኢሠፓአኮ በዚህ መልኩ ተዋቅሮ ሲያበቃ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሁሉ በስሩ ሆኑ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ወሬ ስለ ኢሠፓአኮ እንዲሆን ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ስራ ተሰራ፡፡ ሲቪልና ወታደሩ እየተናናቀ፣ እንዲሁም ሌሎች የውስጥ ችግሮችን ይዞ ለመቀጠል



ከመገደዱም ባለፈ፤ አደራጅ ኮሚሽኑ የፀነሰው ፓርቲ ነውና አብሮ ለመወለድ ሲባል የሚደረገው ሹክቻ የበረታ ነበር፡፡ በዚህም ላይ የሰሜንና የምስራቁ ጦርነት አለ፣ የኢህአፓ ሠርጎ ገቦችን መከላከልም ሌላ ፈተና ነበር፡፡ የክፍለሃገራት ኮሚቴዎችን ፀብ ማርገብና መሸምገልም ተጨማሪ ስራ ሆኗል፡፡ ምንም ቢሆን ግን ኮሚሽኑን ተንከባክቦ ዳር ማድረስ አላዳገተም፡፡

ኢሠፓአኮ ከፍተኛ በጀት ተመድቦለትና የህዝብ ድጋፍም አግኝቶ ጠቅላላ ጉባዔ፣ ማዕከላዊ ኮሚቴ፣ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ የክፍላተሃገር ኮሚቴ እና በየቀበሌው ማኅበራትና መስሪያ ቤቶች የተዋቀሩ መሠረታዊ ድርጅቶች እንዲኖሩት ተደርጎና ራሱን የቻለ የአሠራር መዋቅር ተዘርግቶለት፣ ከቀበሌ እስከ አጠቃላይ ምክር ቤት ባለው የአመራር ቦታ ላይ ይመጥናል የተባለ እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ዜጋ ከየአቅጣጫው ተሰብስቦ በዕጩነት ተመዘገበ፡፡ ከሞላ ጎደል የዕጩዎች መመዘኛ አጭር የህይወት ታሪክና ለአብዮቱ ያደረጉት አስተዋፅኦ የሚል ነበር፡፡

ዕጩዎችን ለማበጠር የተሰየሙት ኮሚቴዎችም "የአብዮታዊ ሠደድ" አባላት የበረከቱበት ነው፡፡ በደርግ የበላይነት እየተዳፈኑ የነበሩ የዘመኑ ፓርቲዎችም በዚያ ወቅት ገና ተደመሰሰው አልከሰሙም ነበርና በተቻላቸው መጠን ዕጩዎቻቸውን አቅርበዋል፡፡ የዕጩዎች ዝርዝር ከተጠናቀቀ በኋላም ምርጫው በቀበሌ፣ ቀጥሎ በከፍተኛ፣ በመጨረሻም በአጠቃላይ ምክር ቤት ተካሂዶ በሁሉም ከተሞች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተጠናቀቀ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የሠራተኛና የገበሬ ማኅበራት ተደራጁ፡፡

በዚህ መሠረት ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን በአንድ በኢሠፓአኮ አመራር መዳፍ ስር ማድረግ ተቻለ፡፡ "የኢሠፓአኮ ተልዕኮ በሰፊው ህዝብ የጋራ ርብርቦሽ ይሳካል" የሚል መፈክር ያላሰማ ዜጋ ፀረ አብዮተኛ ተብሎ ይፈረጃል፡፡ የኮሚሽኑ ልሳን "ሠርቶ አደር" ጋዜጣ ሙሉ ገፁ ስለኢሠፓአኮ የሚያትት ሆነ፡፡

እንዲህ ሆኖ የፓርቲው መወለጃ ጊዜ እስኪቃረብ የተጀመሩ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች እንዲፋጠኑ፣ አስፈላጊ ዝግጅቶች እንዲደረጉ፣ የሌኒንና የትግላችን ሐውልቶች ግንባታቸው አልቆ በጌጣጌጥ እንዲንቆጠቆጡ ተደረገ፡፡

ኢሠፓአኮ በተመሠረተ በ4ኛ ዓመቱ በ1977 "የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር" ፓርቲን (ኢሠፓ)ን ሲወልድ በጥቂቱ በዓሉን የወሎው ድርቅ አደበዘዘው እንጂ፤ አጠቃላይ የከተማዋ በመብራትና በባንዲራ ማሸብረቅና ሌላው ሁሉ ዝግጅት የቀድሞውን የእነጃንሆይን የንግስ በዓል

የሚያስታውስ ሆኖ ነው የታየው፡፡ እንዲህ ያማረችው ከተማ የመላ አገሪቱን የፓርቲ ተወካዮችና የውጭ አገር እንግዶችን በክብር ተቀበለች፡፡

ይህ የንግስ በዓል በአብዮቱ 10ኛ ዓመት የድል በዓል ወቅት በደማቅ ስነስርዓት ከመከበሩ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ጳጉሜ 1 ቀን 1976 ዓ.ም የፓርቲው መስራች ጉባዔ ተሰብስበው ለኢሠፓ ምስረታ እውቅና ሰጥተዋል፡፡ በጉባዔው ላይ ከ2ሺ በላይ የኢሠፓአኮ አባላትና ከ350 በላይ ታዛቢዎች ተገኝተዋል፡፡ የኢሠፓአኮ ተመራጭ አባላት ከሠራተኛው፣ ከገበሬውና ከወታደሩ የተወጣጡ ይሁኑ እንጂ 60 በመቶው አባላት ከመለዮ ለባሹ የተውጣጡ ናቸው፡፡ ... ያው እንደተለመደው ስለሆነ ዝርዝር ውስጥ መግባት ሳያስፈልግ በእለቱ የዕጩዎች ስም ዝርዝር ለቋሚ ማዕከላዊ ኮሚቴና ለተለዋጭ አባላት የታሰቡ ሰዎች ቀረቡ፡፡ ምርጫውም ለብዙሃን መገናኛ የሚሆኑ ቀረፃዎች እስኪከናወኑ ድረስ እውነተኛነቱን ተላብሶ ሲካሄድ ቆየና የድምፅ መስጫ ሳጥኖች የምርጫ አስፈፃሚ ሆነው ለተመደቡት ለኮሎኔል ብርሃኑ ባይህ ተሰጡ፡፡ ከ3 ሰዓት በኋላ የቆጠራ ውጤቱ ተነበበ፡፡በዚህ መሠረት ኮሎኔል መንግስቱ ቁልፍ የሆነውን የፓርቲ ዋና ፀሐፊነት ከመያዛቸውም በላይ፤ ሁለት መቶ አባላት ያሉት የማዕከላዊ ኮሚቴና አስራ ስምንት አባላት ያሉት የፖሊት ቢሮ ሊቀመንበር ሆነው ቁጭ ማለታቸው ተረጋገጠ፡፡

ከኢሠፓአኮው ምስረታ ጋር ተመሣሣይ በሆነ መልኩም የፖሊት ቢሮው አባላት ለመንግስቱ ታማኝነታቸውን ያረጋገጡና በመንግስቱ አቅራቢነት የተመረጡ የደርግ አባላት፣ ቴክኖክራቶችና የማርክሲዝም ሌኒኒዝም አቀንቃኞች ነበሩ፡፡

በዚህ መልኩ ኢሠፓአኮ ኢሠፓን ወለደ፡፡ ፓርቲው ሶሻሊስታዊ ሠነዶችን አፅድቆ ስራውን ቀጠለ፡፡ መንግስቱም እቅዳቸው እየሰመረ በመቀጠሉ ደስ ተሰኙ፡፡ ሆኖም ከአባላቱ በኩል ሁለት ተቃውሞ ነበር፡፡ አንዱ በምርጫው ድራማዊ ክንውን ካኮረፉት በኩል የተደመጠ ማጉረምረም ሲሆን፤ ሌላው የአገሪቱ ዜጎች በረሃብ እየተቀጠፉ ይህን ያህል ከፍተኛ ገንዘብ ለፓርቲ ምስረታ ተብሎ በመመደቡ ነው፡፡

በእርግጥም መንግስቱ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ትኩረታቸው ፓርቲው ላይ ነበርና ይህንኑ ዳር ካደረሱ በኋላ ነው በፍጥነት ወደ ድርቁ ጉዳይ ፊታቸውን ያዞሩትና ቀደም ሲል "የአብዮቱ ፍሬዎች" በሚል ርዕስ ስር ተካትቶ ያየነውን የመፍትሄ እርምጃ መውሰድ የጀመሩት፡፡

በተረፈ በምርጫው ፍትሐዊ አለመሆን የተደመጠውን ጉርምርምታ ከመጤፍ አልቆጠሩትም፡፡ እናም ከዚህ ጊዜ በኋላ "ከጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያም አብዮታዊ አመራር ጋር ወደፊት!" ተባለ፡፡ ሊቀመንበር መንግስቱ አሁን የቀራቸው ሁለት ያህል ቀላል ስራዎች ናቸው፡፡



ሕገ-መንግስቱን ማስረቀቅና ማፅደቅ፣ ሪፐብሊኩን አውጆ ህዝባዊ ምርጫ ማከናወን፡፡ ምርጫውንም አሸንፈው ፕሬዝዳንት መሆንና እስከመጨረሻው መንገስ፡፡ እነዚህን ተግባራት ከማከናወናቸው በፊት ግን በፓርቲው ምስረታ ማግስት የተከሰተው ከባድ የኢኮኖሚ ቀውስ ኢሠፓን አላራምድ ስላለ አንዳንድ እርምጃዎችን መውሰድ ቀዳሚ ተግባር መሆኑ የግድ ሆኖ ተገኘ፡፡ ሰማያዊ ካኪ መልበስም የመጣው የኢኮኖሚ ቀውሱን ተከትሎ ነውና እሱኑ ወደማየት እንለፍ፡፡

የኢኮኖሚ ተሐድሶ

ወቅቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ለድርቅ አደጋ የተጋለጡበትና፤ ድርቁን ተከትሎ በተከሰተው ረሃብም በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ለአሠቃቂ ሞት የተዳረጉበት ወቅት ነው፡፡ ይህንን ዛሬም ድረስ አልለቅ ያለ የጎን ውጋት ለማስወገድ ኢትዮጵያ አቅም አልነበራትም፣ አሁንም ያላትም፣ (ወደፊት ይኖራት ይሆናል እንጂ፤) ስለዚህ ወደለጋሽ አገራት አኮፋዳ ይዞ መዞር የግድ ነበርና መንግስቱ ይህን አድርገው የነብስ አድን ስራ ሠርተዋል፡፡ ነገር ግን በወቅቱ ብዙ አገሮች በርዕዮት መለያየት ምክንያት ፊታቸውን አዞሩ፡፡

በዚህም ላይ በርሃ ያሉ ተቃዋሚዎች ደርግ ጃንሆይን ሲጥል እንዳደረገው ሁሉ ረሃቡንና የፓርቲ ምስረታ ግብዣውን እያቀናጁ ለፕሮፓጋንዳ ስለተጠቀሙበት የተፈለገው እርዳታ በተፈለገው መጠን ሊገኝ አልቻለም፡፡ የተፈጠረውን ክፍተት በራስ ጥረት ለመሙላት ሲባልም እቅድ ነድፎ የነብስ አድን ስራውን ለመስራት የሚያስችል "የተፈጥሮ ችግር መቋቋሚያ ኮሚቴ" ተቋቁሞ እርዳታውን ለተጎጂዎች ማስራጨትና፣ ተጎጂዎችን ወደ ሌላ ሠፈራ ማጓጓዝ ተጀመረ፡፡ ለዚህም ኮሎኔል ብርሃኑ ባይህ የእርዳታ ገንዘብና ቁሳቁስ አሰባሳቢ፣ ሻምበል ለገሠ አስፋው የሠፈራ መርሐ ግብር አስፈፃሚ ዘርፎች ኃላፊ ሆነው ተመድበው በየክፍላተአገሩ እስከቀበሌ ድረስ በተዋረድ የሚሰሩ ሰዎች ተመድበው በህዳር ወር 1977 ዓ.ም ስራቸውን ጀምረዋል፡፡ ሂደቱን አጠናክሮ በመቀጠልም ከትንሹ ስንዴ እደላ እስከ ትልቁ የጣና በለስ ግድብ የዘለቀ የመፍትሄ እርምጃ ተወሰዷል፡፡

ድርቁ ያስከተለው ችግር ወደ ከተማም ተዛምቶ በአዲስ አበባ ሳይቀር ከፍተኛ የእህል እጥረት ተከሰተ፡፡ በሚያስደነግጥ ሁኔታ አንድ ኩንታል ጤፍ 400 ብር (አራት መቶ ብር) ተሸጠ፡፡ ዳቦ ጠፋ፣ አትክልት የለም፡፡ የውሃ እጥረትም ተፈጠረ፡፡ በዚህ ምክንያት በየካቲት ወር 1977 የኮሌራ ወረርሽኝ የከተማውን ህዝብ አጠቃ፡፡

ወረርሽኙ የፖለቲካ ኪሣራ እንዳያስከትል "አጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት" የሚል መጠሪያውን መንግስት "አተት" በሚል ምህፃረቃል ሸፈነው፡፡ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር በወሰደው ፈጣን የመከላከል ርምጃ 700

ሠዎች ብቻ ገድሎ በሽታውን መግታት ተቻለ:: እንዲህ እያለ የአገሪቱ ኢኮኖሚ በፍጥነት እያሽቆለቆለ ሲሄድ መንግስት ለህዝቡ የተለያዩ ምክሮችንና የተመጠነ ኑሮ መልመድ እንደሚገባ ማስተማር ጀመረ:: "ቁጠባን ልመዱ" ሲል አስጠነቀቀ::

ጓድ ሊቀመንበር ራሳቸውን አርአያ አድርገው ማሳየት ነበረባቸውና ... ያው የወታደር ልብሳቸውን ካወለቁ ቆይተው ነበርና በምትኩ ሱፍና ክረባት አድርገው ይታዩ ስለነበር አሁን ደግሞ የአገር ውስጥ ምርት የሆነውን ሠማያዊ ካኪ ኮምፕሌቱን ገጥመው መጡ::

"አለው አለውና

በካኪው ላይ ጠና ..." የሚል ስንኝ ተቋጠረ:: ከካኪ ወደ ሱፍ፣ ከሱፍ ወደ ካኪ ማለት ነው:: ወዲያው የፓርቲው አባላትና ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ይህንኑ ጥቁር ሠማያዊ ካኪ እንዲለብስ የሚያስገድድ ደንብ ወጣ:: ተግባራዊም ሆነ:: ያጉረመረሙት ብዙ ቢሆኑም ግን፣ "አሁን ካኪ ተለብሶ ምን ለውጥ ሊመጣ ነው?" ቢሉም ተግባራዊ ከመሆን አልዳኑም::የሀ ልብስ ሶስት አይነት ደረጃዎችና ቀለማት ነበሩት:: ቀጥሎ ለመንግስት ስራም ሆነ ለግል ማንኛውም አውቶሞቢልና ሌሎች የቅንጦት እቃዎች ከውጭ እንዳይገቡ ታገደ::

የመንግስት ተሽከርካሪዎች በባለሥልጣናቱ በግል መያዛቸው ቀርቶ በጣም አስፈላጊ ሲሆን በሹፌር እንዲጓጓዙ፣ የግል አውቶሞቢል እሁድ ቀን እንዳይሽከረከር፣ ነዳጅ በኩፖን እጅግ አስፈላጊ ለሆነ ጉዳይ ሲፈለግ ብቻ እንዲሸጥ፣ ውድ ዋጋ ያላቸው ጨርቃጨርቆች ተገዝተው ከውጪ እንዳይመጡ፣ነዳጅ፣የሞተር ዘይትና ቅባት ለምርት፣ ለወታደራዊ አገልግሎት፤ እንዲሁም ለህዝብ መጓጓዣ ተግባር ብቻ በእቅድና በቁጠባ እንዲውል፣ የተጋነነ የመኖሪያ ቤት አሠራር ስርዓት እንዲይዝ፣እያንዳንዱ ዜጋ በድርቅ ለተጎዱ ወገኖቹ መልሶ ማቋቋሚያ የሚሆን ቋሚ የገንዘብ መዋጮ እንዲያደርግ፣በመጠለያ ጣቢያ የሚገኙትን ተጎጂዎች ለመርዳት ጥያቄ የሚቀርብለት ዜጋ በማንኛውም የስራ ዓይነት በፈረቃ መሳተፍ ግዴታው እንደሆነ የሚደነግግ ደንብ ወጥቶ በስራ ላይ እንዲውል ተደረገ::

እነዚህን የመሰሉ ሕጎች አውጥቶ በመንግስት ብቻ ጉዳዩ ሳይያዝና በብሔራዊ ደረጃ ችግሩን ለህዝብ ገልጾ፣ አቅምን አገናዝቦ የተመጠነ ኑሮ መኖር ግዴታ መሆኑን አውጆ፤ በተለይም በገቢና ወጪ ንግድ ላይ የተከሰተውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ችግር ለመቅረፍ የሞከረ መንግስት "ረሃብ ደብቋል" እየተባለ መታማቱ ተገቢ አይመስልም:: ከዚህ ይልቅ "ትኩረት የሰጠው ዘግይቶ ነው" በሚለው ማማቱ የተሻለ ይሆናል::

ፓርቲው በአዋጅ የያዘውን አገር የመምራት ስልጣን መሠረት አድርጎ የመንግስትነት ኃላፊነቱን በውጊያም፣ በኢኮኖሚ ግንባታም በሌሎችም ዘርፎች ሁሉ ከመዋከቡ ጎን ለጎን የተቻለውን ጥሯል::



የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ያሽቆለቆለው በድርቅ ምክንያት ብቻ አልነበረም:: በዋናነት በጦርነት ነው:: የራስ ወዳድ ግለሰቦች ንቅዘትም አብሮ ይጠቀሳል:: በጦርነት የፈሰሰው ገንዘብ ግን እጅግ ከፍተኛ የሆነውን ድርሻ ይይዛል:: ይህም የአገር ዳር ድንበር ጉዳይ እስከሆነ ድረስ ደርግ ከጃንሆይ የተረከባትን ድፍን ኢትዮጵያን ጠብቆ የመቆየት ኃላፊነት አለበትና እንደመንግስት በዘርፉ ፈሰስ ማድረግ ነበረበት:: "አገሪቱን በጦርነት ዘፍቆ ህዝቡን ለረሃብ አጋለጠ" ይባላል:: ማነው ጦርነት የፈለገው? ደርግ? ይሄ አባባል መመርመር ያለበት ነው:: ምክንያቱም ጤናማ አስተሳሰብ አይመስልም:: በጥቂቱ ከላይ የተጠቃቀሱትን አይነት የኢኮኖሚ ተሐድሶ በማድረግ በወቅቱ የነበረውን ችግር በመጠኑ ማሻሻል ተችሏል::

ሁኔታው በዚህ በቀጠለበት ወቅት በፓርቲው የማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ውስጥ በተለይ የወታደርና የሲቪሉ ፍጥጫና መናናቅ እየተካረረ ሄደ:: በነብስ አድን ስራው ላይ ይታይ የነበረው የጋራ ርብርብ ፓርቲው የወታደርና የሲቪል እየተባለ በሽኩቻ ውስጥ መሆኑ ቀርቶ ውህደት እየተፈጠረ ነው ወደሚል እሳቤ አምርቶ የነበረ ቢሆንም፤ ብዙም ሳይቆይ የስልጣን ትግል ተጀመረ::

አንዱ ቡድን ኃያሉ የወታደር ቡድን ሆነና፤ ሌላው ቡድን ስልጣን ከወታደሩ ለመንጠቅ ይገዳደራል የተባለው አራት ሲቪል ግለሰቦችን ያቀፈ ቡድን ሆኖ ቁርቁሱ ቀጠለ:: "ጋንግስ አፍ ፎር" (አራቱ ነውጠኞች) ተብለው የተፈረጁት በቁጥር እንጂ በስም ተለይተው አይታወቁም:: ብቻ ግን ጓድ ሊቀመንበር መፍጠን ነበረባቸው:: ፓርቲው (ኢሠፓ) ከተመሠረተ ከሦስት ዓመት በኋላ የሊቀመንበሩ የመጨረሻ ዓላማ ግቡን ሲመታ እናያለን::

ሕገ መንግስትና ምርጫ

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በአብዮቱ ወቅት በገባው ቃል መሠረት ስልጣኑን ለህዝብ ለማስረከብ በዝግጅት ላይ መሆኑን በአብዮቱ 11ኛ ዓመት የልደት በዓል ላይ መስከረም 2 ቀን 1978 ዓ.ም በአብዮት አደባባይ ለተሰበሰበው ህዝብ ጠቁሞ ነበር::

ይህን ለማድረግ የመጀመሪያው ስራ ሕገመንግስት ማርቀቅ ነበርና የአርቃቂ ኮሚሽኑ አባል ሊሆኑ የሚችሉ ዕጩዎችን መመልመል ተጀመረ:: ለዚህና ለቀጣዩ ሂደት ሲባልም "የብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲቲዩት" የተባለ የአገሪቱ ምርጥ ምርጥ ምሁራን የተሰባሰቡበት ተቋም እንዲመሰረት ተደርጎ ነበርና፤ ተቋሙ ያካሄደውን ጥናትና የጥናቱንም ውጤት በመመርኮዝ ሂደቱ እንዲቀጥልና ውጤታማ ግብ ላይ እንዲደረስ ትልቅ ሚና ተጫውቷል::

በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑና አብዮቱን የሚደግፉ ዜጎች ተሳታፊ እንዲሆኑ የተደረገበት ምልመላም ከህዝባዊ ማኅበራት፣ ከሙያ ማኅበራት፣ በአካባቢያቸው ከታወቁ ሰዎች፣ ከፓርቲ አባላት፣ ከሃይማኖት መሪዎች፣ ከጦር ሠራዊት፣ ከፖሊስ፣ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች፣ እንዲሁም ከሕግ ባለሙያዎች የተውጣጡ 344 አባላት ያሉት የሕገመንግስት አርቃቂ ኮሚሽን ማቋቋም ተቻለ፡፡ ስራውንም በዚያው ዓመት የካቲት 7 ቀን ጀመረ፡፡ ህዝቡ እንዲወያይበት ስለታቀደም አራት ወራት የፈጀ የአወያዮች ስልጠናና የመወያያ መድረኮችን የማመቻቸት ስራ ተሠራ፡፡

ረቂቁ በአማርኛ ከተዘጋጀ በኋላ ሁሉም ብሔረሰብ በቋንቋው እንዲወያይበት በሚል በኦሮምኛ፣ በትግርኛ፣ በሲዳምኛ፣ በወላይትኛ፣ በሶማልኛ፣ በአፋር፣ ሐድያ፣ ከንባታ፣ ጌዲኦ፣ ኩናማ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ሳሆ እና በስልጥኛ ተተርጉሞ ለወይይት ተሰራጨ፡፡

ምሽግ ውስጥ ካሉት ወታደሮች ጀምሮ ውጪ አገር ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሳይቀር ለሁሉም ዜጎች እንዲደርስና አስተያየት እንዲሰጥበት ከተደረገ በኋላ ከአወያዮች ዘገባ ጋር ወደ አርቃቂ ኮሚሽኑ ተመለሰ፡፡

ኮሚሽኑ "አስተያየቶችንና የማሻሻያ ሀሳቦችን ተቀብዬ አስተካክዬ ጨርሻለሁ" በሚል ጳጉሜ 1 ቀን 1978 ዓ.ም ለጓድ ሊቀመንበሩ አስረከበ፡፡

በ17 ምዕራፎች የተከፈለውና 119 አንቀጾች ያሉት ሕገ-መንግስት ጥር 24 ቀን 1979 ዓ.ም የህዝብ ውሣኔ ያገኘ ሲሆን፤ እንደ ኮሚሽኑ ዘገባ ከተመዘገበው ህዝብ 81 በመቶው "ተቀብለናል" የሚል ነበርና ሕገመንግስቱ በሪፈረንደም ፀደቀ፡፡

ሕገመንግስቱ በሚደነግገው መሠረትም የመንግስት ከፍተኛ አካል ነው ለተባለው ለብሔራዊ ሸንጎ አባልነት ምርጫ መካሄድ ነበረበት፡፡ ለዚህም "የምርጫ ኮሚሽን" ሚያዚያ 14 ቀን 1979 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡ የዚህ ብሔራዊ ሸንጎ (የእንደራሴዎች ሸንጎ) አባል ሆኖ ለመመረጥ የፓርቲው ዝቅተኛ አባላት መብት አላቸው፡፡ በዚህም በፓርቲው የተደገፉ ዕጩዎች አሸናፊ እንዲሆኑና የብሔራዊ ሸንጎው አባል እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡የአውራጃ ፓርቲ ኮሚቴዎች ለህዝብ እንደራሴነት ይመጥናሉ ያሏቸውን ግለሰቦች ስም ዝርዝር በመመዘኛው መሠረት አጣርተው ለክፍለሀገር ኮሚቴዎች ሲያሳልፉ፤እዚያም አስፈላጊው ማጣራት ተደርጎና "እገሌን በእገሌ ለውጥ" በሚል ወደ አውራጃ ስም ዝርዝሩ ተመልሶ፤ የተለወጡትም "ለምን ተለወጥን?" የሚል ክርክራቸው ውድቅ ተደርጎ፣ የተጣራው ዝርዝር ለማዕከላዊ ኮሚቴ ድርጅት ጉዳይ መምሪያ ተላከ፡፡ ማዕከላዊ ኮሚቴውም የደረሰውን ስም ዝርዝር አይቶ፣የሚሰርዘውን ሠርዞና



በሌሎች ዕጩዎች ተክቶ ለመጨረሻ ስራ ወደ አውራጃ ኮሚቴዎች መለሰው፡፡ በዚህ ጊዜ ነው የበታች የሆኑ የአውራጃ የፓርቲ አባላቱና፤ የፓርቲው የበላይ አካላት ጥምረታዊ የፓርቲ ስራ እየሰሩ እንዳልሆነና፤ፓርቲው የይምሰል መሆኑ ለብዙዎች ግልፅ የሆነው፡፡የበታች የሆኑ የፓርቲው አባላት በዕጩነት የመዘገቧቸውን ተራ የፓርቲ አባላት የላይኛው ክፍል እየሰረዘ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን ተካበት፡፡

ከዚህም በላይ በህዝብ ዘንድ ተደማጭነትን ያስተርፉሉ ተብሎ የታመነባቸው ግለሰቦች ባይፈልጉትም በዕጩነት እንዲቀርቡ ግፊት ተደርጎባቸዋል፡፡ ለአብነትም ብፁዕ አቡነ ተክለሃይማኖት ይጠቀሳሉ፡፡ "አልፈልግም" ብለው ቢከራከሩም በብዙ ማግባባት እሺ አሰኝተው ቅፅ እንዲሞሉ ሲደረግ "ብሔር" የሚል ነገር ሲያዩ "እኔ ብሔር ብሎ ነገር አላውቅም እምቢ ያልኩትም ለዚህ ነው፤ እኔ የምወክለው ምዕመኑን ብቻ ነው" ብለው ጥለው ሊወጡ ሲሉ፤ "ግድ የለም እሱን ይተውትና ሌላውን ይሙሉ" ተብለው የሚያምኑበትን ብቻ ሞልተው እንደሄዱ በ"ነበር" ቁጥር 2 ላይ ተጠቅሷል፡፡

በዚህ ዓይነት የዕጩ እንደራሴዎች ቅድመ ዝግጅት ከተጠናቀቀ በኋላ 150 ሺ አባላት ያሏቸው ከ ክፍለሀገር እስከ ቀበሌ የምርጫ ጣቢያ ድረስ ምርጫውን የሚያስተባብሩ "የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች" በድፍን ኢትዮጵያ ተቋቋሙ፡፡

የምርጫ ኮሚሽኑ ዝግጅቱን አጠናቆ የዕጩ እንደራሴዎችን ዝርዝር ተቀብሎ ካፀደቀና የምርጫ አፈፃፀምና የዕጩዎች ማስታወቂያ መመሪያዎችን ካዘጋጀ በኋላ ለእያንዳንዱ ዕጩ የምርጫ ምልክት ብሎ ራሱ የሰየመላቸውን "ዝሆን፣ እንበሳና ጎሽ" ሰጣቸው፡፡ በተለመደው አሠራር መሠረት አንድ ዕጩ መወዳደር ያለበት በሚኖርበት ወረዳ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን በአዲስ አበባ የፓርቲ አባላትና የመንግስት ባለሥልጣናት በጣም ብዙዎቹ ቦሌ አካባቢ ይኖሩ ስለነበር ችግር ተፈጠረ፡፡

መቼም ቀድሞ ያለቀለት ምርጫ ቢሆንም (እንደማንኛውም የአፍሪካ አገራት ምርጫ) ለደንቡ ያህል ነውና የቦሌዎቹን ባለሥልጣናት ወደ ሌሎች ወረዳዎች መበተን የግድ ሆነ፡፡ በማይኖሩበት ቀበሌ ሄደው ተመረጡ ማለት ነው፡፡

የዝሆን ምልክት የያዘ ዕጩ ማሸነፍ እንዳለበት ቀድሞ ተወስኗል፡፡ ግን አንበሳና ጎሹ እንዲያው በስህተት ሊያሸንፉ ቢችሉስ? በሚል መነሻና በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች ሊመረጡ ይችላሉ ተብለው የተፈሩ ዕጩዎች ስለነበሩ፤ ከዕጩ እንደራሴነት ራሳቸውን እንዲያገሉ ተደረገ፡፡

በከፍተኛ (ወረዳ) 14 ቀበሌ 18 በነበረው የምርጫ ጣቢያ ላይ ዕጩ ሆነው ከቀረቡ 3 ሰዎች ውስጥ አንዱ ጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ

ኃይለማርያም ናቸው፡፡ የፕሬዝዳንትነት ወንበሩ የትም እንደማይሄድ ቢያውቁትም ግን፤ ከዚያ በፊት ከዚህ ቀበሌ በእንደራሴነት ምርጫ ማለፍ አለባቸው፡፡

እንደማንኛውም ዕጩ እንደራሴም በቀበሌው ህዝብ ፊት ቀርበው ራሳቸውን አስተዋውቀዋል፡፡ እናም አንዳች አስገ ነገር እንዳይከሰት የጎሽና የአንበሳ ምልክት ባለቤቶች በደረሰባቸው ተፅዕኖ ምክንያት "ከእሳቸው ጋር በዕጩነት በመቅረቤ ብቻ ታሪካዊ ኩራት ይሰማኛል፣ ልወዳደራቸውና ልመጥናቸው ስለማልችል ብቻ ግን ራሴን በፈቃዴ ከምርጫው አግልያለሁ" እያሉ ወጡ፡፡ የቀበሌው ብቸኛ ዕጩ እንደራሴ ሆነው ጓድ መንግስቱ ብቻቸውን ተወዳድረው ብቻቸውን ተመርጠው አለፉ፡፡

የምርጫውን አጠቃላይ ድባብ በሚመለከት የ"ነበር" ፀሐፊ ዘነበ ፈለቀ በቁጥር 2 መጽሐፋቸው በገፅ 109 ያሰፈሩትን ብናይ ሁኔታውን በአጭሩ ለመገንዘብ ይረዳናል፡፡

"... እንዲህ ሆኖ በሌሎች ምርጫ ጣቢያዎችም ተመሣሣይ እርምጃ ተወስዷል፡፡ ሆኖም አንዳንድ ጣቢያዎች ላይ ጠንካራ እንቢታ ገጥሟል፡፡ ለምሳሌ እኔ ምርጫ ባስፈፀምኩበት ቀጠና ከፍተኛ 17 ቀበሌ 17 ላይ የዝሆን ምልክት የያዙት ኮማንደር የኋላእሸት ግርማ ነበሩ፡፡ የአንበሳውን ምልክት የያዘው የትምህርት ሚኒስትር ኢሠፓ መሠረታዊ ድርጅት ፀሐፊ መብራቱ ገብረንጉስ ነበር፡፡ ከእርሳቸው ይልቅ እርሱ በቀበሌው ህዝብ የታወቀ በመሆኑ፤ "ዝሆኑን ይጥለዋል" በሚል ስጋት ከዕጩነት ራሱን እንዲያገል የምርጫ ጣቢያው አስተባባሪ ኮሚቴ ጠየቀው፡፡ መብራቱ ሆዬ "ኧረ ምን ሲደረግ? ምርጫ ብላችኋል፤ ብላችኋል! የህዝብ ድምፅ ይለየን እንጂ ራሴን አላገልም" ብሎ በፅናት ቆመ፡፡

ቢለመን፣ ቢለመን አሻፈረኝ በማለቱ ወደኔ ላኩት፡፡ "ጓድ መብራቱ ... ምን መሰለህ .... ብዬ ላግባባው ከመጀመሬ "ጓድ ዘነበ ብዙ አትድከም፡፡ እስከላይ ድረስ ሂጂ (እስከ ማዕከላዊ ኮሚቴው) ያለሁበት ፓርቲ የእኩል ፓርቲ መሆኑን ቁርጡን ማወቅ እሻለሁ" ብሎ እንቅጩን ነገረኝ፡፡ .... እላይ ደርሶ ምን እንደተባለ ባላውቅም፤ ከፍቶት ተመለሰ፡፡ ከዚያም ከምርጫው ራሱን አገለለ፡፡..." ይሉናል የዓይን እማኙ፡፡

ምናለ ግን አፍሪካ ውስጥ ቀድሞ ለታወቀ አሸናፊ ምርጫ እየተባለ ያ ሁሉ ጋጋታ፣ ለጋጋታው ሲባል ያ ሁሉ ሚሊዮን ብር ባይባክን? ያስብላል፡፡ ወይስ የአፍሪካ መሪዎች ህዝቡ ሴራችንን አያውቅም የእውነት ይመስለዋል ብለው ያስባሉ? ዘወትር ሲገርመኝ የሚኖር የግል ጥያቄዬ ነው፡፡ መልስ አልባ ጥያቄ!



እዚህ ላይ እግረመንገዴን አንድ ፈገግ ያሰኘኝን ገጠመኝ ላስፍር፡፡ በ2002 ዓ.ም ምርጫ በኢትዮጵያ ከተካሄደ በኋላ የኢትዮጵያ ፓርቲዎች (ብዛታቸው 93 ነበር) ሁሉም በየጽ/ቤታቸው የምርጫውን አጠቃላይ ሂደት የሚመለከቱ መግለጫዎች ይሰጡ ነበር፡፡ በጥምረት በተመሠረተውና መድረክ በተሰኘው ፓርቲ ውስጥ አመራር አባል የሆኑት ዶ/ር መረራ ጉዲናን ፓርቲው መግለጫ ከመስጠቱ በፊት ለሥራ ተገኝቼ ነበርና "ምርጫው እንዴት ነበር ዶ/ር?" አልኳቸው፡፡ "የምን መርጫ?" አሉኝ፡፡ "እንዴ የአሁኑ ምርጫ ነዋ፤ እናንተ ኢህአዴግን በብርቱ የተፈታተናችሁበት የትናንቱ ምርጫ" ስላቸው፤ "ታዲያ ቅርጫ በላ! ምን ምርጫ ትላለህ? ቅርጫ አይደለም እንዴ? ቅርጫ እንኳን ስርዓት አለው" ነበር መልሳቸው፡፡ ይህችን አገላለፅ ስብሰባው ከተጀመረ በኋላም ደጋግመው እያሿት የተገኘውን ጋዜጠኛ ሁሉ በሣቅ ሲያፈርሱት ቆዩ፡፡ ምርጫና ቅርጫ የዚያ ወቅት ሰሞነኛ ጥምር ቃላት ሆነው ሰነበቱ፡፡

ስንመለስ ሰኔ 7 ቀን 1979 ዓ.ም ከንጋቱ 12 ሰዓት የጀመረው ምርጫ ምሽት 12 ሰዓት አበቃ፡፡ የውጭና የአገር ውስጥ ጋዜጠኞች እየተዟዟሩ ሁኔታውን ዘገቡ፡፡ ቀድመው ያሸነፉት የዝሆን ዕጩዎች በካርድ ቆጠራ በድጋሚ አሸነፉ፡፡

ከዚያም ጳጉሜ 4 ቀን 1979 ዓ.ም የብሔራዊ ሸንጎ መስራች ጉባዔ በከፍተኛ ድምቀት ተከፈተ፡፡ 2ሺ የሚሆኑ ጉባኤውን የሚያደምቁ ከአገር ውስጥ የፓርቲ አባላት፣ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ምሁራን፣ መለዮ ለባሽ ጉባዔው ሲከፈት የተገኙ ሲሆን፤ ከውጭ አገር በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት የግብፁን ሆስኒ ሙባረክ ጨምሮ፤ የታንዛኒያ፣ የናይጄሪያ፣ የዛምቢያ፣ የቶጎ፣ የሊቢያ፣ የሳዑዲዓረቢያ፣ የኩዌትና የሌሎች አገሮች መንግስታት ተወካዮች የሆኑ የልዑካን ቡድኖች በክብር እንግድነት ተገኙ፡፡

የመታሰቢያ ስጦታቸውን ሲያበረክቱም በወቅቱ ሻዕቢያን እየረዳች ኢትዮጵያን ታሳርድ የነበረችው አገር የሳዑዲዓረቢያ ተወካይ ለመንግስቱ ያበረከቱት ስጦታ ጎራዴ ነበር፡፡ "እኛ የምንሰጥዎ ከንጉሣችን የተላከ የሳዑዲ ጎራዴ ነው!" ብለው በጩኸት ከተናገሩ በኋላ ጎራዴውን ከአፎቱ መዥረጥ አድርገው ለጓድ ሊቀመንበር ሰጧቸው አሉ፡፡ እረደው ይሁን፣ እያረድናችሁ ነው ይሁን ትርጉሙን በውል ባይረዱትም መንግስቱ ስጦታውን ተቀበሉ፡፡ ከተሰብሳቢው ጉርምርምታ ተደመጠ፡፡

በእለቱ ጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምረው እስከዚያች ታሪካዊ ያሏት ቀን ድረስ የነበረውን የኢትዮጵያ ታሪካዊ ገፅታ 4 ሰዓት በፈጀ ሐተታቸው አቀረቡ፡፡

ሲቀጥሉም፤ "... ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተደደር ደርግ ህዝባዊ አደራ በተቀበለበት በዚያ ቀውጢ ወቅት በገባው ቃል መሠረት ስልጣን

ለታሪክ ሰሪውና ከታሪክ ጋር ለሚዘልቀው ለሠርቶ አደሩ ህዝብ እነሆ ሊያስረክብ ነው፡፡ ደርግ ባለፉት የትግልና የድል አመታት ለተከናወኑት አብዮታዊ ተግባራት ከሁሉም በላይ የድርጊቶቹም ሆነ የውጤቶቹ ባለቤት ለሆነው ለሠርቶ አደሩ ህዝብ ያለውን ጥልቅና ታላቅ አክብሮት እየገለፀ፣ ለወደፊቱም ህዝቡ ለኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አመራር፣ በኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግንባታ የእድገት ትልሙን ሙሉ በሙሉ ዳር እንደሚያደርስ ከልብ ይመኛል፡፡…" አሉ፡፡

በዚህም የስልጣን ምርኩዝ ሆኖ ያገለገላቸውን "ደርግ" የተባለ ቡድን መክሰሙን አረዱ፡፡ የደርግ አባላት መክሰም የጀመሩት ከኢሠፓ ምስረታ ጀምሮ የነበረ ቢሆንም፣ ይፋ የወጣው እና በሕገመንግስቱ መሠረትም መኖር እንደሌለበት ግልፅ የሆነው በዚሁ ጊዜ ነው፣ ይህ ማለት ግን አባላቱ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ከሚገባቸው ስልጣን ጋር ይዘው ስለዘለቁ መክሰም ሊባል አይችልም፡፡ ከቡድናዊ ባለሥልጣንነት ወደተናጠላዊ ሹማምንትነት ተለወጡ የሚለው የተሻለ ይገልፃቸዋል፡፡

ከሊቀመንበሩ ንግግር በኋላ የነበረውን ጊዜም ልዩ ልዩ ሕገመንግስቱን ተንተርሰው የወጡ አዋጆችን በማፅደቅ ነበር ያለፈው፡፡ በዚህም በ813 እንደራሴዎች አማካኝነት ስልጣኑን ተግባራዊ እንደሚያደርግና፣ ዋናው የመንግስት ምክር ቤት እንደሆነ፣ የመንግስት ምክርቤቱም የጉባኤና የስራ አስፈፃሚ አካል የተሰኙ የስራ ዘርፎች እንዳሉት ተገለፀ፡፡ በሕገ መንግስቱ መሠረትም፣

- የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢሕዴሪ) ብሔረሰቦች በእኩልነት የሚኖሩበት ብሔራዊ መንግስት ነው፡፡
- ሠርቶ አደሩ ህዝብ የስልጣን ባለቤትነቱን ተግባራዊ የሚያደርገው በምርጫ በሚያቋቁመው ብሔራዊ ሸንጎና የአካባቢ ሸንጎዎች አማካይነት ይሆናል፡፡
- ብሔረሰቦች በሸንጎው መወከላቸው ይረጋገጣል፡፡
- ኢሕዴሪ በዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት፣ በሶሻሊስት ሕጋዊነትና፣ ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት መርህ የሚመራ መንግስት ነው፡፡
- የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ኢሠፓ የመንግስትና የመላው ህዝብ መሪ ኃይል ነው፡፡
- የውጭ ፖሊሲው በወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት፣ በሠላም አብሮ መኖርና በገለልተኝነት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡
- ኢህዴሪ በራስ ገዝና በአስተዳደር አካባቢዎች የሚዋቀር አሃዳዊ መንግስት ነው፡፡
- ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን አካል ብሔራዊ ሸንጎው ነው፡፡



ብሔራዊ ሸንጎው ዋና ባለሥልጣን መሆኑን ካወጀ በኋላ የራሱን ስብሰባ አድርጎ በመሪነት ላይ መሪነት፣ በመሪነት ላይ መሪነት እየተቀዳጁ እዚህ የደረሱትን ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያምን "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ፕሬዝዳንት" አድርጎ መርጦ እንደሾማቸው ይፋ አደረገ፡፡

ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም በዕለቱ ሳቃቸውን መቆጣጠር እያቃታቸው፣ "… ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ህዝብ በመረጠው ፕሬዝዳንት ተመራች!" በማለት የእንጨት መደሻዋን አንስተው ጠረጴዛዋን ኳ አደረጓት፡፡

ሸንጎው የኢህዴሪን ልዩ ልዩ የስልጣን አካላት ያዋቀረ ሲሆን፣ እነዚህም፣ የመንግስት ምክር ቤት፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ እና የቁጥጥር አካላት ናቸው፡፡

በዚህም መሠረት መንግስቱ ኃይለማርያም የምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት፣ ሻምበል ፍቅረስላሴ ወግደረስ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ አቶ አሰፋ ሊበን የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት ሆነው ሲሾሙ፣ ሌሎች የደርግ አባል የነበሩና ያልነበሩ መለዮ ለባሾችና ሲቪሎች በሚኒስትርነት፣ በምክር ቤቱ አባልነት፣ በምክትል ፕሬዝዳንትነትና በምክትል ጠቅላይ ሚንስትርነት፣ እንዲሁም በልዩ ልዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ እንዱሾሙ ሆነው በጦርነት አጣብቂኝ ውስጥ ገብታ ውጥረት የነገሰባትን ኢትዮጵያን ማስተዳደር ቀጠሉ፡፡

የሌተናል ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም የመጨረሻው የስልጣን ጣራ ላይ የመውጣት ህልም እውን ሆኖ በ1980 ዓ.ም ግቡን መምታት ቻለ፡፡ ስለዚህም 13ኛው የድል በዓል ላይ ስልጣን ህዝቡ ተረክቧልና፣ ወይም ስልጣን የህዝብ ሆኗልና … የዚያ ዓመት መስከረም ሁለት ከሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ ደምቆ ተከበረ፡፡

### መፈንቅለ መንግስቱ እና ያስከተለው መዘዝ

ግቦት 8 ቀን 1981 ዓ.ም ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም ወደሚወዷት ምስራቅ ጀርመን ለስራ ጉብኝት ብለው ሄዱ፡፡ የኢሠፓ የፖሊት ቢሮ አባላት፣ የመንግስት ምክር ቤት አባላት፣ ሚኒስትሮችና ጄኔራሎች ኤርፖርት ድረስ ሄደው በተለመደው መሽቆጥቆጥ በክብር ሸኝተዋቸው ተመለሱ፡፡

መንግስቱ ግትር ሆነዋል፣ ጦሩ እየተሸነፈ ነው፣ የጄኔራሎች የጦር እቅድ በመንግስቱ ዘንድ ብዙም ተቀባይነት አያገኝም፣ የተለየ ሀሳብ የሚያቀርብ የጦር አዛዥ በጥርጣሬ ዓይን ይታያል፣ ሊቀመንበሩ የመረጡትና ወደተግባር እንዲተረጎም የሚሹት የዘመቻ ስልት በሶቭየት ህብረት የጦር አማካሪዎች የሚቀርበውን የወረቀት ላይ የዘመቻ ንድፍን

ነው፡፡ ከፍተኛ የጦር ጄኔራሎች በበታቾቻቸው በደርግ አባላት ይታዘዛሉ፡፡ አንድ መቶ አለቃ ወይም ሻምበል አንድን ጄኔራል ያዛል፤ መንግስቱ በታማኝነት እንጂ በሙያ ብቃት ማመንና መሾም አልፈጠረባቸውም፤ የተናቁም ይመስላቸዋል፤ ከዚሁ ጋርም የደርግ አባል የሆኑ የበታች ሹማምንት ቁምነገሩ የበላይና የበታችነት ጉዳይ ሳይሆን የመንግስቱ ታማኝና ቀኝ እጅ ሆኖ መገኘቱን በመረዳታቸው በማዕረግ የሚበልጧቸውን ታላላቅ የጦር ጀግኖች ይንቋቸዋል፡፡

በእነዚህና እነዚህን በመሣሠሉ መነሻ ምክንያቶች በርከት ያሉ ጄኔራሎች የመንግስቱን አገዛዝ ጠልተውታል፡፡ ፊት ለፊት መጋፈጥ የማይሞከር በመሆኑም ያለው ምርጫ መፈንቅለ መንግስት ማድረግ ነበርና በዚህ ጉዳይ በተለያዩ ቦታዎች ተሰብስበው መመካከር ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡

የጉዳዩ ጀማሪና ጠንሳሽ ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ ነበሩ፡፡ እቅዱ ከሁለትና ሦስት ዓመት በፊት ተነድፎ ሲብላላ የቆየ ነው፡፡ በተለይ መንግስቱ በኤርትራ ያለው ጦር በተሸነፈ ቁጥር ችግሩ የጄኔራሎች ነው ብለው በማመናቸው ብዙዎችን ከነበሩበት ቦታ እያነሱና ዝቅ፣ ከፍ እያደረጉ መሾም መሻር የጀመሩት ከ1978 ጀምሮ ሲሆን፤ ለአብነት ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይን ከአየር ኃይል ዋና አዛዥነታቸው አንስተው የኢንደስትሪ ሚኒስቴር ሚንስትር እንዲሆኑ አድርገዋል፡፡ ይህ መሰሉ ሹም ሽር ለአመታት ተከታትሎ የተከናወነ እንደመሆኑ መጠንና በጄኔራሎቹም ዘንድ ስላልተወደደ ጥርስ ነክሳው ከተጠቀሰው ጊዜ የጀመረና ሲብላላ የኖረ፤ ነገር ግን በ1981 ግንቦት ወር ሊተገበር የተሞከረ ነው፡፡

የዚችን እለት የመጨረሻ የአድማ ስብሰባ ለማድረግ የተመረጠው ቦታ በመከላከያ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ጊቢ ውስጥ የሚገኝና ከሚኒስትሩ ከሜጀር ጄኔራል ኃይለጊዮርጊስ ቢሮ አጠገብ ያለው አነስተኛ የመሰብሰቢያ ክፍል ነው፡፡

በእለቱ ባልተለመደ ሁኔታ ይህ ጊቢ የጄኔራሎች መጠራቀሚያ ሆታ ታዩ፡፡ እድመኞቹም በቀጠሯቸው መሠረት አንድ በአንድ ወደዚያች ክፍል ገቡ፡፡ በስብሰባው ላይም የተገኙት፤

1. ሜ/ጄ/ል መርዕድ ንጉሴ - የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም
2. ሜ/ጄ/ል ኃይሉ ገብረሚካኤል - የምድር ጦር ዋና አዛዥ
3. ሜ/ጄ/ል አምሃ ደስታ - የአየር ኃይል ዋና አዛዥ
4. ሪረ አድሚራል ተስፋዬ ብርሃኑ- የባህር ኃይል ዋና አዛዥ
5. ሜ/ጄ/ል አለማየሁ ደስታ - የምድር ጦር ምክትል አዛዥ
6. ሜ/ጄ/ል ወርቁ ዘውዴ - የፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ



7. ሜ/ጄ/ል አብዱላሂ ዑመር - የመከላከያ ሚ/ር አስተዳደር መምሪያ ኃላፊ
8. ሜ/ጄ/ል ፋንታ በላይ - የኢንደስትሪ ሚኒስትር
9. ሜ/ጄ/ል አበራ አበበ - የጦር ኃይሎች ምክትል ኤታማዦር ሹም
10. ሜ/ጄ/ል ተስፋዬ ትርፌ - የአብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ኃላፊ
11. ብ/ጄ/ል ሰለሞን ጋሻው - የአየር ኃይል ኤታማዦር ሹም
12. ብ/ጄ/ል ደሣለኝ አበበ - የጦር ኃይሎች አካዳሚ አዛዥ
13. ብ/ጄ/ል እርቅይሁን ባይሳ - የ67ኛው ኮር ዋና አዛዥ
14. ብ/ጄ/ል ተስፋዬ ደስታ - የአየር ኃይል ዘመቻ መኮንን
15. ብ/ጄ/ል ነጋሽ ወልደየስ - የ608ኛው ኮር ዋና አዛዥ
16. ብ/ጄ/ል እንግዳ ወልደአምላክ - የ606ኛው ኮር ዋና አዛዥ
17. ብ/ጄ/ል ገናናው መንግስቱ - የ6ኛው አየር ምድር አዛዥ
18. ኮሞዶር ኃይሌ ወልደማርያም - የጦር ኃይሎች ዘመቻ መምሪያ ባልደረባ ናቸው፡፡(ነበር ቁ.2)

በስብሰባው የተገኙት እነዚህ ብቻ ይሁኑ እንጂ ከየጦር ክፍሉ የተመለመሉ አዛዦችም የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ ለመፈፀም ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ተሰብስበው የመጀመሪያ ውሣኔ ያደረጉት ሊቀመንበሩን ቀይ ባህር ሲደርሱ ፕሌኑን በሚሳኤል መምታትና ማሰናበት የሚል የነበረ ቢሆንም፤ ከመንግስቱ ውጪ የተሳፈሩ በርካታ ንፁሃን ሰቪሎች ስላሉ እነሱንም አብሮ መግደል ተገቢ አይደለም የሚል ሀሳብ ስለተነሳ ውሣኔው ተሻረና፤ ከዚህ ይልቅ በወጡበት ማስቀረት እንደሚሻል ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡

ዋና ሰብሳቢው ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ ነበሩ፤ ነገር ግን ወደ ስብሰባው የመጡት ዘግይተው ነበርና የሰብሳቢነቱን ቦታ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ንጉሴ ይዘውታል፡፡ ጄኔራል ፋንታ በላይ ወደ ስብሰባው ገብተው ሲያዩ ቦታው ተይዟል፡፡ ጄኔራል መርዕድ ዋና ሰብሳቢው ሲመጡ ቦታውን መልቀቅ ሲገባቸው ፀጥ አሉ፡፡ ቢታይ፣ ቢታይ መርዕድ ለፋንታ ሊለቁ ቀርቶ የመልቀቅ አዝማሚያም ሳያሳዩ ስብሰባውን መምራት ቀጠሉ፡፡

መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ የተሰባሰቡት ጄኔራሎች እዚያው በዚያው ሌላ መፈንቅለ መንግስት አደረጉ፡፡ ስልጣን ሠይጣን ነዋ! አስቂኙነቱም እዚህ ላይ ነው፡፡ እናም በዚያች ጠባብ ቢሮ ኩዴታ የተከናወነባቸው ጄኔራል ፋንታ በላይ በሁኔታው ተበሳጭተው ስብሰባውን ጥለው ወጡና በር ላይ እጃቸውን ኪሳቸው ከተው መንጎራደድ ጀመሩ፡፡ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ንጉሴ ቦታውን የያዙት "ይምሩት" የሚል ፈቃድ

እግኝተው አይደለም፣ በማዕረግ በመብለጣቸውም አይደለም፡፡ ሲመሩት የቆዩት ጀኔራል ስለዘገዩ ብቻ ነው፡፡

ከጅምሩ መንግስቱን ለመሸኘት መገኘት እየነበረባቸው ሳይገኙ የቀሩ ጀኔራሎች በመኖራቸው ምክንያት ጠርጣራው የደህንነት ሚኒስትር ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደሰላሴ የቀሩትን ጀኔራሎች የሚከታተል ቡድን አሰራጭተው ተጀምሮ እስኪጨረስ የነበረውን ሁኔታ ይከታተሉ ነበር፡፡ የመፈንቅለ መንግስት እድማ መሆኑን እንዳረጋገጡም የመንግስቱ ቀኝ እጅ ለሆነው ለሻምበል (በኋላ ሻለቃ) መንግስቱ ገመቹና ለሌተናል ጀኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን አሳውቀዋቸዋል፡፡

እነዚህ ሦስቱ ተመካከረው የፓርቲው ፖሊት ቢሮ አባላትና የመንግስት ምክር ቤት አባላትን፣ እንዲሁም በቅርብ የተገኙትን ሚኒስትሮች ወደ ቤተመንግስት ከጠሯቸው በኋላ በጋራ ምክክር "ሰው ልከን ፍላጎታቸውን እንወቅ" የሚል አቋም ይዘው ኮሎኔል ደበላ ዲንሳንና ኮሎኔል ሃዲስ ተድላን መርጠው ከአንድ ፖሊስ ጋር ላኳቸው፡፡

መልዕክተኞቹም "... የያዛችሁት ጉዳይ ደም መፋሰስ እንዳያስከትል በጋራ እንምከርበት ... ፍላጎታችሁስ ምንድነው?" ብለው ጥያቄያቸውን ለጀኔራል መርዕድ ንጉሴ አቀረቡ፡፡ ጀኔራሉም፤ "ጉዳያችን ከሰውየው ነው፡፡ እናንተን አይመለከትም፤ ነገሩም ያለቀለት ስለሆነ ምክክር አያስፈልግም" ብለው እንቅጩን ነገሯቸው ይሉናል፤ በቅርበት ሆነው ጉዳዩን የመከታተል እድል የነበራቸው የ"ነበር" ፀሐፊ ዘነበ ፈለቀ፡፡

ሁኔታው ቀጥሏል፤ሁለት የአየር ኃይል ጀቶች በአዲስ አበባ ሰማይ ላይ አስገምግመው አልፈዋል፡፡ጀኔራሎቹም ጉዳዩ እንደተሳካ ቆጥረው ተረጋግተው ተሰብስበዋል፡፡

በእቅዱ መሠረትም ሜጀር ጀኔራል ቁምላቸው ደጀኔና የ202ኛው አየርወለድ ክፍለ ጦር ኤታማጀገር ሹም ኮሎኔለ ካሣዬ ታደሰ አንድ አንቶኖቭ አውሮፕላን ሙሉ የአየር ወለድ ወታደሮች ይዘው ከአስመራ ተነስተው ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ደርሰዋል፡፡

ይህንንም በደህንነቱ ለጥበቃ ቦሌ የተመደበው ሰው ለደህንነቱ ለኮሎኔል ተስፋዬ ወልደሰላሴ በመስክ ሬዲዮ ገለጸ፡፡ ኮሎኔል ተስፋዬ፤ "ጀኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን በማን ትዕዛዝ መጣህ ብሎ ጠይቆሃል ብለህ ንገረው" ሲሉት ይህንኑ ለጀኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ሲገልፅ፤ ጀኔራሉ "ጀኔራል ተስፋዬ የሚባል አዛዥ አላውቅም! ለምን እንደመጣሁ ሊጠይቀኝ እንደማይችል ንገረው" ሲሉ መለሱለት፡፡

ሜጀር ጀኔራል ቁምላቸው ደጀኔ በተያዘው እቅድ መሠረት በተዘጋጀላቸው መጓጓዣ ጦራቸውን ጭነው ወደ አርሚ አቪየሽን ተጓዙ፡፡ እንደደረሱም የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያንና አርሚ አቪየሽንን ከምድር ጦር ዋና አዛዥ ከሜጀር ጀኔራል ኃይሉ ገብረሚካኤል ከስብሰባው



በፊት በተገለፀላቸው መሠረት በቁጥጥር ስር አዋሉና ከሜጀር ጀኔራል አበራ አበበ የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ መጠባበቅ ጀመሩ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ለስብሰባ በተመረጠው ጊቢ ውስጥ ያለው ሁኔታ ደግሞ ጀኔራል ፋንታ በላይ ደጃፉ ላይ መንጎራደዳቸውን እንደቀጠሉ ሲሆን፤ጀኔራል መርዕድ ንጉሤም የመሪነት ቦታውን እንደያዙ የተለያዩ ውሳኔዎችን እያሳለፉ ነበር፡፡ጥቂት የኮር አዛገሮች እየተጠሩ በስብሰባው ላይ እንዲገኙ ሲደረግ፤የመንግስቱ ታማኝ የተባሉትን የማዕከላዊ ዕዝ አዛዥ የነበሩትን ሜጀር ጀኔራል ዘለቀ በየነ የደርግ አባልም ስለነበሩ "ለስራ ጉዳይ ይፈለጋሉ" ተብለው ተጠርተው በአንድ ክፍል እንዲታሰሩና እንዲቆለፍባቸው ተደረገ፡፡

በዚህ መሀል ከመሰብሰቢያ ክፍሏ ውጪ ያለውን ሁኔታ እንዲቃኙ የተላኩት ሜጀር ጀኔራል አበራ አበበ በመከላከያ ሚኒስትር ጊቢ ውስጥ የነበሩትን ወታደሮችና ሲቪል ሠራተኞች ሰብስበው "ጨቋኙና አምባገነኑ መንግስት ወድቋል! ከዚህ በኋላ..." እያሉ የመፈንቅለ መንግስቱን ሁኔታ በንባብ እያሰሙ ሞቅ ያለ ጭብጨባ እየተቀበሉ ነበር፡፡ ምኑም ሳይያዝ፣ የሚዲያ አውታሮችን በቁጥጥር ስር ሳያውሉ፣ ገና አንድ እርምጃ እንኳ ሳይጓዙ ጊቢው ውስጥ ላሉ ሃያና ሰላሳ ሠራተኞች ይህን የመሰለ መግለጫ እየሰጡ ማስጨብጨባቸው ሌላው አስቂኝ ገጽታ ነው፡፡

እነዚህ ጀኔራሎች መንግስቱ ከዚህች ሰዓት ጀምሮ ከስልጣን መወገዱንና የመንግስት ለውጥ መደረጉን የገለፁት ለማን ነው? ብንል ለራሳቸውና ለእነዚያ ጥቂት ግለሰቦች ነው መልሱ፡፡ በተቃራኒው ግን ኤርትራ ያሉት በአስመራ ሬዲዮ ጣቢያ ለህዝብ ይፋ አድርገው ነበር፡፡

የግለሰቦችን ጭብጨባ ሰምተው ከቢሮአቸው የወጡት የመከላከያ ሚኒስትሩ ሜጀር ጀኔራል ኃይለጊዮርጊስ ፈቃዳቸውን ያልተጠየቁበት ስብሰባ በቢሯቸው አጠገብ መካሄዱ ገርሟቸው ወደ ቦታው ሊያመሩ በሚራመዱበት ጊዜ ጀኔራል አበራ አበበ ለአንድ የጥበቃ መኮንን "ጥብቅ ጥበቃ ይደረግ" የሚል ትዕዛዝ ሲሰጡ ሰሙና "እኔ በማላውቀው ጉዳይ ላይ የሚካሄድ ጥብቅ ጥበቃ ምንድነው?" በማለት ርምጃቸውን ገታ አድርገው ጠየቁ፡፡ በዚህ ጊዜ እያነበቡ ያስጨበጭቡ የነበሩት ጀኔራል አበራ አበበ፤ "አንቱ ሰውዬ ተውኝ ብልዎ አልተውኝ አሉ አይደለም?" በማለት የቆየ ቁርሾ እንደነበራቸው በሚጠቁም አነጋገር ሲቆጡ፤ ሚንስትሩ በቁጣ ሽጉጣቸውን መዘዝ ሲያደርጉ ጀኔራል አበራ አበበ ቀድመው ተኩሱና ጣሏቸው፡፡ የመከላከያ ሚንስትሩ ሜጀር ጀኔራል ኃይለጊዮርጊስ በዚችው ጥይት ህይወታቸው አለፈ፡፡

የኃይል ስምሪቱን ለማስተባበርና የስብሰባውንም ደህንነት የማስጠበቅ ኃላፊነት የተሰጣቸው ጀኔራል አበራ አበበ አንድ ነብስ

አጥፍተው፤ ሁኔታውንም ለተሰብሳቢዎች ሳይገልፁ፤ ሂጃለሁም ሳይሉ ጊቢውን ለቀው እግሬ አውጪኝ አሉ፡፡

ተሰብሳቢዎቹ ያወቁት ጉዳይ የለም፤ ስብሰባውን ቀጥለዋል፡፡ከአስመራ ይመጣል ብለው የሚጠብቁት የአየር ወለድ ጦር በምን ሁኔታ ላይ እንዳለና መድረስ አለመድረሱን አያውቁም፡፡

ጄኔራል አበራ አበበ ጥለው እንደሸሹ አያውቁም፣ ከአስመራ ያዘዋቸው የመጡትን አየርወለዶች ጄኔራል ቁምላቸው ምን እንደሚያሿቸው አያውቁም፤ ምክንያቱም የጄኔራል አበራን ትዕዛዝ በመጠባበቅ ላይ ናቸውና፡፡ ጄኔራል ቁምላቸው ቀጣይ ትዕዛዙ ለምን እንደዘገየ አያውቁም፣ አየር ወለዶችም ስላልተገለፀላቸው ለምን እንደመጡ አያውቁም፡፡ በቃ አያውቁም ባያውቁም ሆነ ነገሩ ሁሉ፡፡

የፖሊስ ጠቅላይ አዛዥ ሜጀር ጄኔራል ወርቁ ዘውዴ ነገሩ አላምር ብሏቸው ይሁን፣ ጥበቃውን ለማጠናከር ይሁን በማይታወቅ ሁኔታ ስብሰባውን ጥለው ወጡ፡፡ ከዚህ በኋላ ማንም አልወጣም፡፡ ወዲያው እሩብ ጉዳይ ለሰባት ሲሆን በሻምበል መንግስቱ ገመቹ የተመራው የቤተመንግስቱ ቅልብ ጦር የመስሪያ ቤቱን ጊቢ ዙሪያውን አጠረው፡፡ የልዩ ጥበቃ ብርጌዱ ጦር ከበባውን እንዳደረገም ማንም እንዳይወጣ፣ ማንም እንዳይገባ የሚል ትዕዛዝ ከሻምበል መንግስቱ ገመቹ ተሰጠና ይሄው ትዕዛዝ ተግባራዊ ሆነ፡፡

ሻምበል መንግስቱ ገመቹ ይህን በድል እንዳጠናቀቀውና የቀረው በምድር ጦር ውስጥ አርሚ አቭየሺን የመሸገው ኃይል እንደሆነ ለሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ገለፀ፡፡ ቀጥል ተባለ፡፡ ቀጠለ፡፡

በዚህ መሐል ሁለተኛው ዙር የአየር ወለድ ጦር ከአስመራ ተነስቶ ቦሌ ደረሰ፡፡ ይህንንም እዚያ የነበረው ጠባቂ በታዘዘው መሠረት ለደህንነቱ ለኮሎኔል ተስፋዬ ገለፀ፡፡ አለቃቸውን ጠይቆ እንደተረዳውም ከጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ብቻ ትዕዛዝ ተቀበሉ ተብለው የተላኩ መሆናቸውን ጨምሮ ነበር በመስክ ሬዲዮ መረጃ ያስተላለፈው፡፡

ይህን ገለፃ በያዘው ሬዲዮ ከደህንነቱ እኩል ያዳምጥ የነበረው ሻምበል መንግስቱ ገመቹ በደህንነት ሚኒስትሩ እና በመረጃ አቀባዩ የሬዲዮ ንግግር ጣልቃ ይገባና "አንድም ነገር አትንገራቸው፤ እንሄዳለን ወደሚሉበት ይሂዱ" ብሎ ትዕዛዝ አስተላለፈና አብሮት የነበረውን ሻለቃ ሽለማ ኤልማናን "አብዮት አደበባይ ላይ ጠብቀህ አስቁማቸውና ጄኔራል ቁምላቸው ታላቁ ቤተመንግስት እንደሚገኙ ነግረህ ወደዚያው ይዘሃቸው ሂድ" ብሎ አዘዘው፡፡ ሻምበል መንግስቱ ገመቹ እነዚህን ትዕዛዞች ከሰጠ በኋላ የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያንና አርሚ አቭየሽንን ይዘው ትዕዛዝ ይጠባበቁ የነበሩትን "ወንድሞች ጥቂት ችግር ነበር፤ አሁን ችግሩ ተወግዷል፤ ስለደከማችሁ መሣሪያችሁን አስቀምጡና ረፍት አድርጉ"



አላቸው፡፡ መሣሪያቸውን ከግምጃ ቤት እንዲያስቀምጡ ካደረገ በኋላ "የመጣችሁት ለተሳሳተ ተግባር መጠቀሚያ እንድትሆኑ ነበር፡፡ ነገሩ እስከሚጣራ በጥበቃ ስር ሆናችሁ እዚህ ትቆያላችሁ" በማለት በቁም እስር አቆያቸው፡፡ ይሄን ተግባር ፈፅሞ ሲመለስ ሻለቃ ሽለማ በታዘዙት መሠረት በሁለተኛው ዙር የመጣውን አየርወለድ ወደ ቤተመንግስት መርተው አስገብተዋቸው ነበር፡፡

በሁለት ዙር የመጡት ከታገቱ በኋላ ሦስተኛው አንቶኖቭ አዲስ አበባ ደርሶ ለማረፍ እያንዣበበ እንዳለ "ለተሳሳተ ተግባር የተላኩ ወታደሮችን መጫንህ ስለተረጋገጠ፤ ወደመጣህበት ተመለስ፡፡ እንቢ ካልክ ባለህበት እንደምትጋይ እወቅ" የሚል ማስጠንቀቂያ ለአብራሪው ሲነገረው ወደመጣበት ተመለሰ፡፡

በዚያች ዕለት አገሪቱን እየመሯት የዋሉት ሻምበል መንግስቱ ገመቹና ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴ ነበሩ ለማለት ይቻላል፡፡ የአድመኞቹን የግንኙነት መስመር በማቋረጥ ደህንነቱ ኮሎኔል ተስፋዬ፣ የአድመኞቹን አጋዥ ወታደሮችና የአዛዦችን የትብብር መረብ በመበጣጠስ ሻምበል መንግስቱ መተኪያ የሌለው ሚና ተጫውተዋል፡፡

ከስብሰባው ውጪ ሆነው ጦር እንዲያስተባብሩ የተመደቡት ጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ጥቂት ወታደሮችን ይዘው በግራ መጋባት ሲጠባበቁ ከቀኑ 10 ሰዓት በአንድ መቶ አለቃ የሚመሩ በሻምበል መንግስቱ የተላኩ የልዩ ጥበቃ ብርጌድ ወታደሮች እርሳቸው ወዳሉበት ሄዱ፡፡ እነዚህ ወታደሮች አካባቢውን እንዲቃኙ ቀድመው ተላኩ እንጂ ሌላ ትዕዛዝ ያልተሰጣቸው ነበሩና ሄደው ከጄኔራል ቁምላቸው ሠራዊት ጋር ተላተሙ፡፡ ጄኔራሉ ይህን ምንነቱን ያላወቁትን ወታደር አብረዋቸው በነበሩት ወታደሮች አስከብበው ትጥቁንም አስፈትተው ባዶ ቤት ውስጥ አዘጉባቸው፡፡ እነርሱን ተከትለው የሄዱ ሌሎች ወታደሮችም በታንክ ታግዘው ወደ ቦታው ሲያመሩ ጄኔራሉ በተመሳሳይ አስከብበው ታንካቸውንም ማርከው በግራ መጋባት መጠባበቃቸውን ቀጠሉ፡፡

ሜጀር ጄኔራል ቁምላቸው ያለውጊያ እነዚህን ወታደሮችና ታንካቸውንም ጭምር በቀላሉ መማረክ ቢችሉም ከበላዮቻቸው ጋር የነበረው ግንኙነት በመቋረጡና ቀጣይ ስራቸውንም ባለማወቃቸው ምንም ሊያደርጉ አልቻሉም፡፡

ምሽት 12 ሰዓት ላይ ሻምበል መንግስቱ ገመቹ እንደተከበበ ወደዋለው ወደ መከላከያ ጊቢ አምርቶ በድምፅ ማጉያ ጊቢው እንደተከበበና በውስጡ የሚገኝ ዘበኛ፣ ሲቪል ሠራተኛ፣ ባለሥልጣን፣ ጄኔራል ሁሉም እጁን ጭንቅላቱ ላይ አጣምሮ በሁለተኛው በር እንዲወጣ አሳሰበ፡፡ ሁሉም በአምባሳደር ቴአትር ቤት በኩል ባለው በር እጅ ወደ ላይ አድርገው ሲወጡ፤ ብርጋዴል ጄኔራል አምሃ ደስታ እዚያው

ራሳቸውን ገደሉ። ቀጥሎ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ንጉሴ ራሳቸውን በሽጉጥ ገደሉ። ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ እና ኮሞዶር ኃይሌ ወልደሚካኤል ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን እዚያው ውስጥ ተደብቀው ቀሩ። ሌላው በሠላም ወጥቶ እጅ ሰጠ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሜጀር ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ የተመራው የአስመራው አድማ እንደተጧጧፈ ቀጥሎ የነበረ ሲሆን፤ በአስመራው ሬዲዮ ጣቢያ የመንግስቱ ኃይለማርያም አንባገነናዊ አገዛዝ እንዳበቃና ለውጥ እንደተደረገ፣ ኢትዮጵያ ሠላም የሰፈነባት አገር ሆና እንደምትገነባ ወዘተ እየተገለፀ ነበር። ሻዕቢያና ወያኔም "ጉዳያችሁ ዳር እስኪደርስ ተኩስ አቁመናል" ብለዋል። በተመሳሳይም በጎንደር አዘዞ የነበሩት የ603ኛው ኮር አዛዥ ሜጀር ጄኔራል ዘውዴ ገብረየስ በአስመራ ሬዲዮ የሚሰራጨውን መልዕክት በወረቀት እያባዙ ለህዝብ ይበትኑ ነበር። በሰሜን ጎንደር የኢሠፓ ዋና ፀሐፊ የነበረው ሻምበል ገዛኸኝ ወርቁ ለስራ ጉዳይ አዲስ አበባ ወጥቶ ነበርና ወደ ጄኔራል ዘውዴ ደውሎ ሁሉም ነገር በቁጥጥር ስር መዋሉን በመግለፅ ጠሩን እንዲያረጋጉ ሲያዛቸው "ዞር በል ያንተ አዛዥነት አክትሟል" ብለው ስልኩን ዘጉበት። ሻምበል ገዛኸኝ ወርቁ ወደ ዕዙ የፖለቲካ ኮሚሳር ደውሎ "እዚህ ያለው አድመኛ ጄኔራል ሁሉ በቁጥጥር ስር ውሎ ታጉሯል። አጠገብህ ያለውን ጄኔራል ከነተከታዩ አፍስህ አስረህ ጠብቀኝ" አለው። ከሚሳሩ የታዘዘውን ፈፀመ።

አመሻሹ ላይ ግራ የተጋቡት ጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ከነበሩበት አርሚ አቪየሽን ጊቢ ወጥተው ሁኔታውን አጣርተው ለመምጣት አንድ ታንክ አስከትለው የመከላከያን ጊቢ ክርቀት ለማየት ወደሚያስችለው ወደ ጎማ ቁጠባ ዳገታማ ጎዳና ሄደው ሲያዩ የተለየ ድባብ አስተዋሉ። ጄኔራሉ ከአርሚ አቭየሽን እንደወጡ ወዲያው ነበር ጊቢው የተከበበው። ስለዚህ አየር ወለዶች እዚያው እንዳሉ በቁጥጥር ስር ዋሉ።

ጄኔራል ቁምላቸው ባቅራቢያቸው ወዳለው 5ኛ ፖሊስ ጣቢያ ሄደው የፖሊስ መምሪያ ጠቅላይ አዛዥ የሆኑትን ሜጀር ጄኔራል ወርቁ ዘውዴን በስልክ እንዲያገኟቸው ቢያዙም ቀድመው ከስብሰባው የወጡት ጄኔራል ሊገኙ አልቻሉም። የፖሊስ አዛዡ ማምለጫ መንገዱ ሁሉ ተዘግቶባቸው ቤታቸው ውስጥ መሽገው የሚመጣውን ለመቀበል ተዘጋጅተው ነበር።

ከዚህ በኋላ ጄኔራል ቁምላቸው ሁሉም ነገር ማክተሙን ተረድተው ጥለዋቸው የመጡትን ጥቂት አየርወለዶችንም "የራሳቸው ጉዳይ" ብለው ራሳቸውን የሚያድኑበትን መንገድ መፈለግ ጀመሩ።

የአዲስ አበባው የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ በሻምበል መንግስቱ ገመቹ ብርቱ ትግል በተደረገ ከበባ እኩለ ሌሊት ላይ በድል



ተደምድሟል። በሁሉም የጦር ክፍሎች የነበሩት ተባባሪዎች ሁሉ እጃቸውን ተይዘዋል።

አጠገባቸው ይገኝ የነበረውን ብሔራዊ ሚዲያ መቆጣጠር ሳይችሉ፣ ወታደሮቻቸውን በየቦታው ሳይመድቡ፣ ለህዝብ መረጃውን ሳያሰራጩ፣ እርስ በርስ ሳይስማሙ፣ ለማክሸፍ ማን ምን ሙከራ ሊያደርግ እንደሚችል ሳያውቁ፣ ሳይገምቱና ሳይዘጋጁ፣ በአንድ ጊቢ ውስጥ በምትገኝ ቢሮ ተሰብስበው መፈንቅለ መንግስት አድርገው፣ ስኬታማነቱን ለጥቂት የቢሮው ሠራተኞች እና ለራሳቸው አውጀው፣ ጊቢ ውስጥ ያሉትን አስጨብጭበው፣ እዚያው ጊቢ ውስጥ ደም ተፋሰው፣ እዚያው ጊቢ ውስጥ ተይዘው ቀሩ። የአዲስ አበባው አስቂኝ መፈንቅለ መንግስት ሳይጀመር ተጨረሰ፤ ሳይሞከር ከሸፈ።

ከሌሊቱ በ9 ሰዓት ጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያም የምስራቅ ጀርመን ጉብኝታቸውን አቋርጠው አዲስ አበባ ደርሰው የተቀባይ ጋጋታ በሌለበት በቀጥታ ወደቤታቸው ገብተው፤ እንቅልፍ ይወስዳቸዋል ብለን ባናስብም ተኙ።

ነግቶ ግንቦት 9 ቀን 1981 ዓ.ም ሆነ። ማለዳ ላይ አስመራ የሚገኘው የ202ኛ የአየር ወለድ ክፍለጦር አባላት "የፕሬዝዳንት መንግስቱን አመራር የሚቃወም ማንኛውም ድርጊት አብዮቱን የመቀልበስና ኤርትራን የማስገንጠል ሴራ ነው!" በሚል አምፀው ሬዲዮ ጣቢያውንም ተቆጣጥረው መፈንቅለ መንግስቱ የከሸፈ መሆኑን አወጁ። በዚህም አላበቁም ሌሎች የሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት ኮሮችና ክፍለጦሮች ከአየርወለድ ቡድኑ ጎን ተሰልፈው አገርን ጉድ ያሰኘ ተግባር ፈፀሙ።

የአስመራውን አድማ በዋናነት የመሩትን ሜጀር ጄኔራል ደምሴ ቡልቶን ጨምሮ ተባባሪ ያሏቸውን ጄኔራሎች ሁሉ ረሸኑ። ሬሳቸውንም በአደባባይ እየጎተቱ ተጫወቱበት። ቀጥለን ዝርዝራቸውን የምናየው ተረሻኞች ውሰጥ ግን የአድማው ተባባሪ ያልሆኑና የበታቾች አጋጣሚውን ተጠቅመው ቂማቸውን የተወጡባቸው ይገኙባቸዋል። ጦሩ "የእኛን ስንቅ ለጠላት ሽጧል፣ ጦሩን ሲመራ ሆን ብሎ ወደ ጠላት ወረዳ ከቶ አስከብቦ አስፈጅቶናል፣ እኛ የምንለብሰው አጥተን በእኛ ገንዘብ በውስኪ ይራጫል ... ወዘተ" በሚል ቂም በቀል ያሉበትንም የሌሉበትንም በጭካኔ ጨፈጨፈ። አስመራ በዚህ ሁኔታ ስትውል፤የአዲስ አበባዎችም ከጥቂቶች በስተቀር ተለቅመው ከታሰሩ በኋላ ግንቦት 10 ቀን ጓድ ሊቀመንበር በብሔራዊ ሚዲያ ጥቂት ጄኔራሎች ለስልጣን ሲሉ የሞከሩት ሴራ በእንጭጩ መቀጨቱን ከሰፊ ሐተታ ጋር ገለፁ።

የአድማው እንቅስቃሴና የህዝቡ ጉርምርምታ በአንድ ጊዜ ፀጥ ረጭ አለ፡፡ በአስመራ ራሳቸው ይመሩት በነበረው ሠራዊት የተረሸኑት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ሜ/ጀ/ል ደምሴ ቡልቶ - የሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት ዋና አዛዥ
2. ብ/ጀ/ል ወርቁ ቸርነት - የዕዙ የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊና ምክትል አዛዥ
3. ብ/ጀ/ል ታደሠ ተሰማ - የዕዙ ዘመቻ መኮንን
4. ብ/ጀ/ል ንጉሤ ዘርጋው - የሁለተኛው አየር ምድብ አዛዥ
5. ብ/ጀ/ል ከበደ ወልደፃድቅ - የሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት መምሪያ
6. ብ/ጀ/ል ሠለሞን ደሣለኝ - የ202ኛው አየር ወለድ ክፍለ ጦር አዛዥ
7. ብ/ጀ/ል ከተማ አይተንፍሱ - የ11ኛው ክፍለ ጦር አዛዥ
8. ብ/ጀ/ል ታዬ ባለኬር - የኤርትራ ሪስ ገዝ ፖሊስ አዛዥ
9. ብ/ጀ/ል ተገኔ በቀለ - ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት መምሪያ
10. ብ/ጀ/ል ከበደ መሐሪ- የዕዙ ድርጅት መኮንን
11. ብ/ጀ/ል ፈለቀ እንግዳ - ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት መምሪያ
12. ዶክተር ኮሎኔል ጌታቸው አወቀ - የዕዙ ሆስፒታል ዳይሬክተር
13. ሌ/ኮ/ል መስፍን አሠፋ - የ2ኛ ሜካናይዝድ ክፍለ ጦር አዛዥ
14. ሌ/ኮ/ል ዘርዓይ ዕቁባይ - ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት መምሪያ
15. ሌ/ኮ/ል ዮሐንስ ገብረማርያም - ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊትመምሪያ
16. ሻለቃ ካሣ ፈረደ - የዕዙ መሐንዲስ ክፍል ባልደረባ
17. ሻለቃ ሚካኤል ሚሬበ - ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት መምሪያ
18. ሻምበል ጌታሁን ግርማ - ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት መምሪያ

በዚህ እልቂት ሻዕቢያና ወያኔ በከፍተኛ የደስታ ስሜት ተጥለቀለቁ፡፡ በሣቅ እያሽካኩም አላገጡ፡፡ የአስመራው ሁኔታ ባየነው መልኩ ፈጣን ግድያ ተከናውኖ ተደመደመ፡፡ የአዲስ አበባዎቹን ጄኔራሎች ስም ዝርዝር ከአድማው አጀማመር ጋር ቀድመን ስላዩነው ደግሞ መዘርዘሩ አያስፈልግምና ቀጣይ ዕጣፋንታቸውንና ፍፃሜያቸውን በአጭሩ ወደማየት እናልፋለን፤ ከዚያ በፊት ግን ከመፈንቅለ መንግስቱ ሙከራ ጋር የተያያዙ ሁለት ያህል ነጥቦችን እናንሳ፡፡

የመጀመሪያው የመፈንቀለ መንግስቱ ዓላማ ምን ነበር? የሚለው ነው፡፡ በርካታ የዓይን እማኝ የነበሩ የቀድሞው ጄኔራሎች አሁን ላይ ሆነው ዓላማውን ለመተንተን ይዳዳሉ፡፡ ካለፈ በኋላ የሚገለፀውና በወቅቱም የተነገረው፤ "ጦርነቱ በአስቸኳይ እንዲቆምና ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ንግግር እንዲደረግ፣ ከሁሉም ተቃዋሚዎች የተውጣጣ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም፣ አዲሱ ሕገመንግሰት ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ መንገድ የፀደቀ ስለሆነ እንዲታገድ፣ የሀገር መከላከያ ከግለሰብ አገልጋይነት ነፃ ሆኖ በአዲስ መልክ እንዲደራጅ፣ ህዝቡን በመለዮ ለባሹ



ጠመንጃ አፈሙዝ መግዛት እንዲቆም፤ ለህዝቡ የጋዜጣ፣ የንግግርና የሠላማዊ ሰልፍ ነፃነት እንዲሰጠው ..." የሚል ዓላማ እንደነበር ይገለፃል፡፡ አንዳንድ የቀድሞው ጄኔራሎችማ አሁን ላይ ሆነው "ህዝባዊ መሠረት የነበረውና የተደራጀ፣ ቢሳካ ኖሮ ለኢትዮጵያ የተሻለ ..." በሚል ያብራሩታል፡፡

በመሠረቱ ህዝባዊ መሠረት ሊኖረው ቀርቶ ሠራዊታዊ መሠረት አልነበረውም፡፡ አቀናባሪ የነበሩ አባላት እንኳ በጽኑ የጋራ መሠረት ላይ የቆሙ አልነበሩም፡፡ ከዚህም በላይ ይህን መሰሉን ተንታኔ በግምታዊ ገለፃ መደምደም ቀላል የመሆኑን ያህል፤ ቢሳካ ኖሮ ዓላማው ከላይ የተገለፀውን እቅድ በተግባር መተርጎም አልነበረም ብሎ መገመትም እኩል ቀላል ይሆናል፡፡ ይልቁንም ገና ከጅምሩ የተከናወነውን የኩዴታ ተግባር ስናይ የመጀመሪያውን ገለፃ ከመቀበል ይልቅ ሁለተኛውን ግምታዊ ድምዳሜ መምረጥ የበለጠ ቀላል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሁሉም አካል ስልጣን ሲይዝ የሚለው ያንኑ ነው፡፡ አገሪቱ በዚያ አይነት የስልጣን ትግል ውስጥ በነበረችበት ወቅት፣ ለጠላት መረጃ አሳ… መሸጥ ፋሽን በሆነበት በዚያ ወቅት፣ በዚያ ላይ ኢትዮጵያዊ ባለሥልጣን ስልጣን ይዞ ለሌላ አካል አሳልፎ ለመስጠት ሲል ህይወቱን አደጋ ላይ የሚጥል፣ .... እንኳን በጦርነት ሠዓት በሠላማዊ ምርጫ አሸንፎ ስልጣን የያዘ፣ ተሸንፎ ስልጣን የለቀቀ አካል ባልታየባት አህጉር (ከሁለት የአፍሪካ አገሮች በስተቀር) ይልቁንም በኢትዮጵያ መሆኑን ስናስብ ዓላማው ምን እንደነበረ ግልፅ ይሆንልናል፡፡ ምንም እንኳ በሞካሪዎቹ አሳዛኝ ፍፃሜ ልባችን ቢነካም፤ በግለሰብ ደረጃ እንኳ ቤተሰቦቻችን፣ ዘመዶቻችን ቢሆኑ፣ በተጨማሪም በኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ በአክብሮት ብናያቸው፤ የመፈንቅለ መንግስቱ ዓላማ ምን ነበር? ለሚለው ጥያቄ አንድ ዓይነት የሆነ የብዙሃኑ የጋራ ምላሽ ከመስጠት አያግደንም፡፡ ከእውነት አብልጦ ራሱን የማይወድ እንባቢ የሚሰጠው ምላሽ "የግንቦት 8 ቀን 1981 ዓ.ም የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ አላማው ስልጣን ነው" የሚል፡፡ ... ስልጣን ... ስልጣን!

ሌላው ሁለተኛው ነጥብ ሙከራው ለምን ከሸፈ? ደጋፊና ተቃዋሚዎችስ እነማን ነበሩ? የሚለው አንድም ሁለትም የሆኑ ጥያቄዎች ሲሆኑ፤ ምላሻቸውን በጥምረት አጠቃለን ለማየት እንሞክር፡፡ የመፈንቅለ መንግስት ሞካሪዎች እቅዳቸውን ቀድመው ለጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳንና ለኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴ ገልፀውላቸዋል፡፡ ያገኙት መልስ፤ "ጥሩ ነው ቀጥሉ፤ ግን በገሃድ አብረን ልንሳተፍ አንችልም" የሚል መልስ በተናጠል ሰጥተዋል፡፡ ይህም ታስረው በነበሩ አንድ ጄኔራል የምርመራ ቃል ተረጋግጦ የነበረ ቢሆንም፤የምርመራውን ውጤት ተቀብለው ደህንነቱ ቀብረው አስቀርተውታል፡፡

የሞካሪዎቹ የቅንጅትና የዝግጅት ጉድለት ዋና የመክሸፊያ ምክንያቱ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ ነገር ግን ሙከራው የከሸፈው ለውጥ እየፈለጉ ግን ፍርሃት ያርበተበታቸው ባለሥልጣናት ቁርጠኛ አቋም ባለማሳየታቸው ነው፡፡ ለምሳሌ ቁልፉን ሚና የሚጫወቱት የደህንነት ሚኒስትሩ ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴ ከሁለት አንድ ያጣ ላለመሆን ሲሉ በአንድ በኩል እንዲሳካ የሻምበል መንግስቱ ገመቹን አካሄድ ዘገምተኛ ለማድረግ መሞከራቸውን እስር ላይ ሆነው አምነዋል፡፡ በሌላ በኩል ቢከሽፍ የሚደርስባቸውን አደጋ እያሰቡ በተለይ ወደመጨረሻው ገደማ ክሽፈቱ እየተረጋገጠ ሲሄድ ሙሉ በሙሉ ጄኔራሎችን ከደው የመንግስቱ ታማኝ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ እርምጃ ወስደዋል፡፡ ኮሎኔሉ ብቻ ሳይሆን ሚኒስትሮችና ሌሎች የፖሊት ቢሮና የመንግስት ምክር ቤት አባላት፣ ሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳንን ጨምሮ “ምን እናድርግ?” በሚል ተጠራርተው በተሰበሰቡ ጊዜ ጉዳዩን ለማጓተት የሚረዱ የተለያዩ ሀሳቦችን አንስተዋል፡፡ ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን እንኳ ሳይቀሩ የአድማው ተባባሪ ነበሩ፡፡ ግን ሁሉም ተፈራሩ፡፡ ሁሉም ከሁለት አንድ ያጣ ላለመሆን አመነቱ እንጂ ለውጡን ከጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያም በስተቀር ሁሉም ይፈልገው እንደነበር በደንብ ተረጋግጧል፡፡ ግን ማን የውስጡን ያውጣ፣ ማን ደፍሮ የውስጥ አቋሙን ይናገር፡፡ በዚያን ጊዜ አንድ ቆራጥ ሰው ድጋፍ ቢያሳይ ተሰብሳቢው በሙሉ የድጋፍ ጩኸቱን ያቀልጠው እንደነበር ግልፅ ነው፡፡ የሁሉም ማመንታትና ዝም ብሎ የሆነ ያልሆነ ነገር መቀባጠር ግራ ያጋባው ሻምበል መንግስቱ በምን እናድርግ ስብሰባው ላይ ብድግ ብሎ “ማስቆም ካለብን ፈጥነን እናስቁማቸው፤ ቤቱ እቅዳቸውን የሚደግፍ ከሆነ ደግሞ ሊወሰድ የታሰበውን እርምጃ ልቀጥልበት፡፡ በሉ እንጂ?” ሲል ጠየቀ፡፡ አሁንም ፈሩ፡፡ ሻምበል መንግስቱ ከዚህ በኋላ ነው የማክሸፍ ስራውን የጀመረው፡፡

ለአገርና ለህዝብ ሲባል ለውጥ መደረግ አለበት ብሎ የሚያምን እውነተኛና ቆራጥ ልብ ያለው ዓላማና ምኞቱ አገርና ህዝብ እንዲለወጡ፣ እንዲሻሻሉ ነውና ለአንድ ህይወቱም ሆነ ለአንድ ስልጣኑ ሲል በፍርሃት አይንቀጠቀጥም፡፡ ግን ቢከሽፍስ? በሚል መነሻ እራሴንም ስልጣኔንም ለምን አጣለሁ? የሚለው አካሄድ ከቁርጠኛ ለውጥ ፈላጊ ባይጠበቅም፤ ከአፍቃሬ ስልጣን ግን ይጠበቃል፡፡ የሆነውም ያ ነው፡፡ ዛሬ ላይ ሆነው ሁሉም ታሳሪ ባልሥልጣናት በተለይ ደህንነቱ አንባ ቀረሽ ፀፀታቸውን ደጋግመው ይገልፃሉ፡፡ “አንድም የማይደግፍ አባል አልነበረም!” ይሉናል፡፡ በዚህ መሰሉ የልቦናና የአንደበት ግጭት ሙከራው ከሸፈ፡፡

አሁንም ይህ በእንዲህ እንዳለ ብለን ስንቀጥል እንደተባለው መፈንቅለ መንግስቱን በአንደበትም፣ በልቦናም የማይደግፉት ጓድ



ሊቀመንበሩ ብቻ መሆናቸው ግልፅ የመሆኑን ያህል፤አሜሪካና ሶቭየትም በስለላ ድርጅቶቻቸው በሲ.አይ.ኤ. እና በኬ.ጂ.ቢ. አማካኝነት ሙከራው እንዲሳካ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ለዚህም ይረዳቸው ዘንድ ለሁለቱም የስለላ ድርጅቶች በሚስጥር ተቀጥረው ይሰሩ እንደነበር የሚነገርላቸው የደህንነቱ ኃላፊ ኮሎኔል ተስፋዬን ተጠቅመውባቸዋል፡፡ በተለይ የአስመራውን አድማ ሁለቱ አገሮች ፈጥነው እውቅና የሰጡት ሲሆን፤ የአዲስ አበባዎችንም “በርቱ” እያሏቸው ነበር፡፡

ኢትዮጵያና ሶቭየት መልካሙ ግንኙነታቸው በተለይ በ1970ዎቹ የመጨረሻ አመታት ከመሻከር አልፎ ተበጥሷል ማለት ይቻላል፡፡

ከፓርቲ ምስረታውና ከሕገመንግስቱ መጽደቅ በፊት በነበረው ጊዜ ሶቭየት የደርግን ሊቀመንበር ሌተናል ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምን “የዳህላክ ደሴት ግዛትን ለወዳጅዎ ለሶቭየት ያበርክቱ፣ አካባቢው ላይ የጦር ቅኝት ማድረጊያ ጣቢያ አስፈልጎናል” የሚል ጥያቄ አቅርበው ነበር፡፡ በአገር ጉዳይ ድርድር የማያውቁት መንግስቱ “እንዴ! ይሄ እንዴት ይሆናል? እኛ'ኮ በሕግ ስልጣን የተሰጠንና በህዝብ ተመርጠን መንግስት የሆንን አይደለንም፡፡ እንዲህ አይነት ጥያቄ በጭራሽ አንቀበልም፤ ስልጣንም የለንም” የሚል ምላሽ ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ሶቭየት ኢትዮጵያን አንቅራ ተፍታለች፡፡

ይልቁንም ለአማፅያኑ እርዳታ ወደማድረጉ አምርታለች፡፡ ለዚህም ነው የደርግ የስልጣን ዘመን መገባደጃ ላይ ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ወደ ኤርትራ ግዛት ዳህላክ አካባቢ ወደሚገኝ ቦታ ለስራ ሊሄዱ ሲሉ፤ “ጌታዬ ወደ ዳህላክ ለመሄድ የሶቭየት ባለሥልጣናትን ፈቃድ ማግኘት የግድ ነው” ሲባሉ በድንጋጤ አብድ የሆኑት፡፡ የአካባቢው ክፊል ግዛት በሻዕቢያ ቁጥጥር ስር ሆኖ ስለነበርም በሻዕቢያ መልካም ፈቃድ የሶቭየት ጥያቄ ያለኢትዮጵያ መንግስት ይሁንታ ተመልሷል፡፡

በዚህና በሌሎች የርዕዮት ፍርክስክሶች የጓድ መንግስቱ አገዛዝ እንዲወገድ ሶቭየት መፈለጓ ስለማይገርም ለውጡ እንዲሳካ መፈለጓም የሚደንቅ አይሆንም፡፡

የአሜሪካ አቋም ከድሮውም ግልፅ የሆነና ተጀምሮ እስኪጨረስ የታወቀ ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ የአማፅያኑ ደጋፊ፣ የመንግስቱ ተቃዋሚ የነበረች ናት፡፡ ስለዚህ ሁለቱ አገራት ሙከራው እንዲሳካ ብቻ ሳይሆን ከተሳካ በኋላም ከፈንቃዮቹ ጎን እንደሚሆኑ አረጋግጠዋል፡፡

በሠራተኞቻቸው በደህንነቱ አማካኝነትም ትብብርዎን ይቀጥሉላቸው ብለዋል፡፡ ደህንነቱም የሂደቱን ዘጠና በመቶ እቅፍ ድግፍ አድርገው በማያስነቃ መልኩ አስጉዘውታል፡፡ ከመጀመሪያው ጀምሮም ጥንቁቅ የደህንነት ጠባቂ መሆናቸውን በሚያረጋግጥ አኳኋን ያዩትን ለተስፋዬ ገብረኪዳንና ለመንግስቱ ቀኝ እጅ ለሻምበል መንግስቱ ገመቹ የገለፁት

በሙሉ ልብ እንዲከሽፍ በመፈለጋቸው ሳይሆን፤ ሂደቱ ከተጀመረ እንዲቀጥል ሁሉም መፈለጉ ስለማይቀር ችግር እንደሌለው በማመናቸው እንጂ (በእርግጥም እንደዚያ ነበር ማንም ያሰበው) ለመንግስቱ አገዛዝ ተቆርቋሪ ሆነው አልነበረም፡፡

ስለዚህ መጀመሪያ በሚስጥር አይዟችሁ ያሏቸውን በስተመጨረሻ ውድቀታቸው አይቀሬ መሆኑን ሲረዱ በሚስጥር ካዷቸው፡፡ ተጠርጣሪዎችን አሳዳጅ ሆኑ፡፡ በጉዳዩ ላይ እንደነበሩበት የሚያረጋግጡ ተጨባጭ መረጃዎችን ማጥፋት ስራቸው ሆነ፡፡ ያጋልጡኛል ያሏቸውን እና የፈሯቸውን በተለያየ ዘዴ ቦታ ቦታቸውን አስያዙና በመንግስቱ ፊት "የታባታቸው!" ብለው ሸለሉ ማለት ነው፡፡ ወደ ሞካሪዎች ፍፃሜ ስንመለስ፤ ጊቢ ውስጥ ተደብቀው የቀሩት ሁለት ብቻ ነበሩ፡፡ ኮሞዶር ኃይሌ ወልደማርያም በመከላከያ ሚኒስትር ጊቢ ውስጥ ከሚገኝ መታጠቢያ ቤት ተገኝተው ታሰሩ፡፡ ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ (የእቅዱ ጠንሳሽና ሰብሳቢ የነበሩትና መፈንቅለ መንግስት የተደረገባቸው) በጊቢው ውስጥ በሚገኝ የዕቃ ማሸጊያ ኮንቴነር ውስጥ ተደብቀው 3 ቀናት ያለ እህል ያለ ውሃ ከቆዩ በኋላ የሚያመልጡበትን ቀዳዳ በመፈለግ ላይ እንዳሉ ተያዙ፡፡

"ጌፕሲና ሚሪንዳ በከተማው ጠፍቶ፤

ፋንታ ተገኘ አሉ በኮንቴነር ሞልቶ፡፡" ተብሎ ተገጠመላቸው፡፡

በዚያ ወቅት የተቋጠሩ ስንኞችን በሚመለከት የ"ነበር" ፀሐፊ ዘነበ ፈለቀ በቁጥር 2 መጽሐፋቸው ያካተቱትን አንድ ገለፃ ላክል፡፡

ሊቀመንበሩ አዲስ አበባ ገብተው ሁሉም ነገር በቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ የአዲስ አበባን ህዝብ ለማመስገን በአብዮት አደባባይ ግንቦት 12 ቀን ተገኝተዋል፡፡ በእለቱ በርካታ ህዝብ ተገኝቶ የተለያዩ አብዮታዊ መፈክሮች ተደምጠዋል፤ቀርቶና ሽለላም ነበር፡፡ የዝግጅቱ ዓላማም "እንኳን እግዜር አዎጣዎ" ለማለት ነው፡፡

"እንጋፋው የሽለላና የቀረርቶ አቀንቃኝ ዓለማየሁ ፋንታ ጭንቅላቱን በነጭ ሻሽ በቀጭኑ ሸብ አድርጎ፤ ለምዱን ለብሶ ማሲንቆውን በቄንጥ እየገዘገዘ

"አባሮ ገዳይ ከዳመናው ስር!

ትመለሳለህ ብዬም አልነበር!" በማለት ሲያቅራራ ላዳመጠው ለዓመታት ሲያቅራራበት የነበረ ስንኝ ሳይሆን "ለምን መጣህ?" በሚል ቁጭት ለዚያች ዕለት አስቦ የቀመረው ይመስል ነበር" ይሉናል፡፡

ጄኔራል ፋንታ በላይ ተይዘው ማዕከላዊ ምርመራ ታስረው ሳለ፤ "ለማምለጥ በመሞከራቸው በጠባቂዎች ተገደሉ" ተብሎ በብዙሃን መገናኛ ተሰራጨ፡፡ ሆኖም ታሪኩ ካለፈ በኋላ እንደተባለው የደህንነቱ ኃላፊ ሚስጥር ያወጡና ተባባሪነቴን ያሳውቁብኛል ብለው የራሳቸውን ሰው



ልከው እስር ቤት ውስጥ እንዳስገደሏቸው ነው፡፡ ለዚህም የተለያዩ የአሟሟታቸውን አይነት መሠረት ያደረጉ አሳማኝ ምክንያቶች ተዘርዝረዋል፡፡ ከዚህም በላይ ሊቀመንበር መንግስቱ "ዋና ጠንሳሽ የሆኑትን ጄኔራል ፋንታን ማነጋገር ስለምፈልግ እንድታመጡልኝ" የሚል ቀጠሮ አስይዘው ስለነበር ሁለቱ ከመገናኘታቸው በፊት ነበር የተገደሉት፡፡

ከዚያም ሚኒስትሩን ገድለው ያመለጡት ጄኔራል አበራ አበበ አምልጠው እንደሄዱ ዘመዳቸው ቤት ተሸሽገው ለጥቂት ቀናት ከቆዩ በኋላ ለደህንነቱ ለኮሎኔል ተስፋዬ የሚያመልጡበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹላቸው ቢጠይቋቸውም ዳግመኛ እንዳይደውሉ አስጠንቅቀው ቻው አሏቸው፡፡

ጄኔራል አበራ የደህንነቱ እምቢታ ቢያበሳጫቸውም ምንም ሊሉት አይችሉምና ይልቁንም የት ሆኜ እንደደወልኩ አጣርቶ እንዳያስይዘኝ በሚል ስጋት የመሸሸጊያ ቦታቸውን ለውጠው ወደ ሌላ ዘመድ ቤት ሄዱ፡፡ የሴትዮዋ ባለቤት ኮሎኔል ነበርና የባለቤቱን ዘመድ መሸሸግ ለደህንነቱ ተናገረ፡፡ ወደ ራሱ ቤት እየሟራ ወስዶ አስያዛቸው፡፡ ለባለውለታነቱ 5ሺ ብር ተሰጠው፡፡ ከባለቤቱና ከዘመዶቿ ጋር ተኮራረፈ፡፡ በወቅቱ ጄኔራል አበራ አበበን ለመያዝ የሄደው ቡድን ከነህይወታቸው መማረክ እየቻለ ነገር ግን የእጅ መስጠት እድልም ሳይሰጣቸው ታዘው በሄዱ ፖሊሶች ተኩስ ተገደሉ፡፡

በዚያ ወቅት ከሚሊቴሪው አልፎ የአመፁ ተባባሪ ነበር እየተባባሉ መጠቋቆም ወደሲቪሉም ተዛምቶ ነበርና ሁሉም ስጋት ላይ ነው፡፡ የጄኔራል አበራ ወዲያው መገደልም ለደህንነቱ ሌላ እፎይታ ነበር፡፡

ሌላው ሜጀር ጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ሲሆኑ በራሳቸው አገላለፅ በእለቱ ከአዲስ አበባ ወጥተው በጎጃም አድርገው ሱዳን፣ ከዚያ አሜሪካ ገባሁ ሲሉ፤ ውስጥ አዋቂ ነን የሚሉ ወገኖች ደግሞ አድማው ሲከሽፍ አሜሪካ ኤምባሲ ውስጥ ገብተው እንደተሸሸጉና ምቹ አጋጣሚ ተጠብቆ በኤምባሲው ትብብር ከአገር ወጥተው አሜሪካ መግባታቸውን ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ አምልጠው አሜሪካን አገር ገብተዋል፡፡

የቀሩትን ጄኔራሎች በሚመለከት ፕሬዝዳንት መንግስቱ ለህዝቡ "የጥቂት ጄኔራሎች ጉዳይ በአጭር ጊዜ ውስጥ በፍርድ ታይቶ ይወሰናል" ብለው በገቡት ቃል መሠረት ከጠቅላይ ጦር ፍርድ ቤት ጀምሮ ልዩ ልዩ ደረጃ ያላቸው የጦር ፍርድ ቤቶች ተቋቁመው ስራ ለመጀመር 6 ወራት ያህል ጊዜ ወስዶ ክሱ ህዳር 27 ቀን 1982 ዓ.ም ተመስቶ ጉዳያቸው መታየት ጀመረ፡፡

20 ጄኔራሎችንና 86 ከፍተኛና መካከለኛ ማዕረግ ያላቸውን መኮንኖች ፍርድ ለመስጠት በታላቁ ቤተመንግስት ውስጥ ራሱን የቻለ ፍርድ ቤት ተቋቋመ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የ14ቱ ጄኔራሎች ክሳቸው የታየው በጠቅላይ ጦር ፍርድ ቤት አንደኛ ችሎት ሲሆን፤ ለዳኝነት የተሰየሙት

ሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን የመሀል፣ ሜጀር ጄኔራል አስራት ብሩ የግራ፣ ብርጋዴል ጄኔራል ዓለማየሁ ስዩም የቀኝ ዳኞች በመሆን ነው፡፡ ዐቃቤ ሕጉ ኮሎኔል ታጠቅ ነበሩ፡፡

የክሱ ዋና ነጥብ የሁሉም "መንግስትን በኃይል ለማስወገድ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ማድረግ" የሚል ነው፡፡ የተለያዩ አገራት መንግስታት ለሊቀመንበር መንግስቱ የከፋ እርምጃ እንዳይወስድባቸው በምክርም፣ በልመናም ሲማፀኑ ቆይተዋል፡፡ በነፃ እንዲለቋቸው የጠየቁ መንግስታትም ነበሩ፡፡ መንግስቱ አልሰሟቸውም፡፡ እናም ሂደቱ ሲጀመር አግባብ ባለው መንገድ እንዲከራከሩ፣ ጠበቃ ማቆም ከቻሉ እንዲያቆሙ፣ ካልቻሉ መንግስት እንዲያቆምላቸው ተፈቅዶላቸው ተከራክረዋል፣ ተከላክለዋል፡፡ ጠበቃ፣ ቤተሰብ፣ የውጭ ጋዜጠኛ ሳይቀር በችሎቱ ተገኝተው ነበር፡፡ ያደረሱት የከፋ አደጋ አለመኖሩን እያነሱ ተከራክረዋል፣ ጠበቆችም የቅጣት ማቅለያ ጠይቀዋል ... ወዘተ፡፡

የቀኝ ዳኛው የሕግ ምሩቅ ቢሆኑም፤ ሁለቱ ዳኞች ግን እንደማንኛውም ሚሊቴሪ ከውስን የሕግ እውቀት ውጪ ባለሙያ አልነበሩም፡፡ ያም ቢሆን ክፋት አልነበረውም፡፡

ህዳር ላይ የተጀመረው ችሎት በቀጠሮ ሂዶ ሂዶ ለውሣኔ ግንቦት 13 ቀን 1982 ዓ.ም ተቀጠረ፡፡ እስከዚህ ድረስ በአግባቡ ከሄደ በኋላ ግን የውሣኔ ቀጠሮው በ13 የነበረው ለጠበቆቹ ባልተለመደ አሰራር ስልክ ተደውሎ ወደ ግንቦት 11 መለወጡ ተነገራቸው፡፡ በተባለው ቀን ተከሳሶችም ጠበቆችም ተገኙ፡፡ ሌላ ታዳሚ አልተገኘም፡፡ ጋዜጠኛና ቤተሰብ ተባረረ፡፡ ክርክሩ ሙሉ ቀን ወስዶ ከምሽቱ 12 ሰዓት ድረስ ቆየ፡፡ ረፍት ተወጣ፡፡ ጠበቆቹ ግን ለእረፍት እንዳይወጡ ተከልክለው እዚያው ቀሩ፡፡

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ዳኞች ተሰየሙ፡፡ ያ ሁሉ ክርክርና አግባብነት የነበረው አሠራር ሁሉ በአንዴ ገደል ገብቶ ፍርድ ቤትነቱም ቀረና እስረኞች በካቴና የኋልዮሽ ታስረው ሸሎቱ ላይ እንዲቆሙ ተደረገ፡፡ (ችሎት ሲቀረብ ተከሳሽ እጆቹን አይታሰርም) ይሄም ባልከፋ ግን መዝገብ ማገላበጡ፣ ሙግት መስማቱ ቀርቶ ተፅፋ የተላከች አንዲት ብጣሽ ወረቀት ይዘው እንባ እየተናነቃቸው ሜጀር ጄኔራል አስራት ብሩ ሊያነቡ ተዘጋጁ፡፡ ያቺ ግማሽ ገጽ ወረቀት በሊቀመንበሩ ተፅፋ የተላከች ትዕዛዝ መሆኗ ነው፡፡ እስኪመሽ የተጠበቀውም ለዚሁ ነበር፡፡

ጄኔራል አስራት የሐዘን እንባቸውን እያፈሰሱ በሲቃ ድምፅ አነበቧት፡፡

እንግዲህ ቀደም ሲል በአድማው ስብሰባ ላይ የነበሩ ተብለው ከተዘረዘሩት 18 ጄኔራሎች ውስጥ ጄኔራል አበራ አበበ እና ጄኔራል ፋንታ በላይ ስለተገደሉ፤ ጄኔራል መርዕድ ንጉሴና ጄኔራል አምሃ ደስታ



ራሳቸውን ስለገደሉ፣ ሌሎቹ 14ቱ ግን በቁጥጥር ስር ሆነው ስለቆዩ ተከታዩ ፍርድ ተበየነባቸው፡፡

ሜጀር ጄኔራል አብድላሂ ዑመር በ10 ዓመት እስራት፣ ሪር አድሚራል ተስፋዬ ብርሃኔ በ15 ዓመት እስራት እንዲቀጡ ሲወሰን፤ ሌሎቹ 12ቱ ጄኔራሎች የሞት ፍርድ እንደተበየነባቸው የሚገልፀውን ወረቀት አንብበው እንባቸውን እየጠረጉ ፈጥነው ከችሎት ወጡ አንባቢው፡፡ ማለትም ዳኛው፡፡ ከተከሳሾች አንደበት የተለያዩ አሳዛኝ ቃሎች በጩኸት ተደመጡ፡፡ "ቤተሰቦቻችን ሳንሰናበት! ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ እድሜ የለውም... ቤተሰቦቻችን አደራ ..." የሚሉ ድምጾች፡፡

ተከሳሾች በወታደሮች እየተገፈተሩ ከአዳራሹ ወጡ፡፡ የዚያኑ ዕለት ምሽት ተረሸኑ፡፡

ሌላውን ሁሉ ትተን ጄኔራሎችን ብቻ ብንደምር አስመራ ላይ ከተገደሉት ጋራ 24 ጄኔራሎች ተገድለዋል፡፡ ከፍርድ በፊት የተገደሉትንና ራሳቸውን ከገደሉት 4 ጄኔራሎች ጋር 28 ሲሆኑ፣ በመከላከያ ሚኒስትር ጊቢ ውስጥ በአንድ ጥይት ከሞቱት ሚኒስትር ጋር 29፣ አንድ አምልጠው የተሰደዱ፣ አንድ 15 ዓመት የተፈረደባቸውን ስንጨምር አገሪቱ ከ6 ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ 30 የጦር ጄኔራሎቿን በቅፅበት ማጣቷን እንረዳለን፡፡ ምን ቀረ ይባላል? ኢትዮጵያ በታሪኳ ዘመናዊ ጦር ሠራዊት ያደራጀችው ከጥቂት አስርት በፊት ነበር፡፡ ዘመናዊ ጦር ሠራዊት ከተገነባ በኋላም እነዚህ ጄኔራሎች እዚህ ማዕረግ ለመድረስ አመታት ወስዶባቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር አገሪቱ በ30 ዓመት ውስጥ ያፈራቻቸውን 30 ጄኔራሎች በቅፅበት ስታጣ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ለማወቅ የጦር ሰው መሆን ሳያስፈልግ ማንኛውም ሲቪል ዜጋ በቀላሉ ይረዳዋል፡፡ ከዚህም በላይ በጦርነት ውስጥ የነበረች አገር ላይ አንድ የጦር ጄኔራል ምን ያህል አስፈላጊ ዜጋዋ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ጓድ መንግስቱ ይሄን ለማሰብ አልፈለጉም፡፡ የሶማሊያው ዚያድ ባሬ እንኳን ኢትዮጵያን ሊወሩ ሲሉ ራሳቸው ያሰሩትን ጄኔራል ራሳቸው ፈትተው የአዛዥነቱን ቦታ ሰጥተውታል፡፡ ዚያድ ባሬ ፕሬዝዳንት ከመሆናቸው በፊት ጄኔራል ስለነበሩ ጥቅሙን ያውቁ ስለነበር ነው ቢባል እንኳ መንግስቱ ይሄን ማወቅ አይችሉም ብሎ ማሰብ ይከብዳል፡፡ ግን አፍሪካዊ መሪ ናቸውና የአፍሪካውያን መሪዎች የጋራ መፈክር የሆነውን "በስልጣን የመጣ ዓይኑ ይውጣ"ን መፎክር ነበረባቸውና ፎከሩት፡፡

ይህ ድርጊት የደርግ የመጨረሻው መጀመሪያ ነው፡፡ የእነዚህ ጄኔራሎች መገደል በቁም ለነበሩት ጄኔራሎች እንዴት ያለ ስሜት እንደሚፈጥርባቸው፣ ምን አይነት የሞራል ዝቅጠት እንደሚያስከትልባቸው አልታሰበም፡፡ ከዚህ በኋላስ ጦርነትን ለማሸነፍ እንዴት ይታሰባል? ለሁሉም ጦር ሠራዊት ተስፋ አስቆራጭ ሆነ፡፡ በተለይ የቀሩት ጄኔራሎች

በሙሉ ልብና በጀግንነት ተዋግተው ሊያዋጉ ቀርቶ የወደፊት ህይወታቸውን ከደርግ ውድቀት በኋላ በምን አይነት ካፒታል መመስረት እንዳለባቸው ያውጠነጥኑ ገቡ፡፡ ቀድመው የጀመሩትም፣ አዲስ ጀማሪዎችም በተገኘው አጋጣሚ መቦጨቃቸውን ተያያዙት፡፡ መረጃ ለጠላት በገንዘብ መሸጥ፣ ምሽግ ውስጥ ያለውን ወታደር ደመወዝ ማስቀረት፣ ስንቁንና አልባሳቱን በገፍ ለጠላት መሸጥን አጧጧፉት፡፡ ሁሉም ባይባልም በርካታዎቹ የዚህ አይነቱን ተግባር እንደታተሩበት ከራሳቸው አንደበት በተከታዩ ተከታይ ንዑስ ርዕሳችን የምናየው ይሁንና የጀመርነውን እንቋጭ፡፡

ጄኔራሎች ተገደሉ፡፡ የእነሱን የአዛዥነት ቦታ ማን ይሸፍነው? የቀሩት ጄኔራሎችስ በቂ ነበሩ ወይ? ክፍተቱንስ መሙላት ይችላሉ ወይ? ተብሎ ቢጠየቅ፤ ከተገደሉት ጄኔራሎች ውጪ የቀሩ በርካታ ጄኔራሎች ነበሩ የሚል መልስ ብናገኝም፤ የተፈጠረውን ክፍተት መሙላት የሚችሉ ሆነው በዝተው ግን አናገኝም፡፡ የብቃት፣ የችሎታና የጀግንነት ጉዳይን ማንሳት አይጠበቅብንም፤ አንድ ጄኔራል እርከኑን ጠብቆ እዚያ ደረጃ እስከደረሰ ድረስ ለጦር ሜዳ ውሎ አስፈላጊነቱ አያጠያይቅምና፡፡

ስለዚህ የተፈጠረውን ክፍተት ማን ይሙላው? ጓድ ሊቀመንበር ሌተናል ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም ፈጣን ምላሽ ይሰጡናል፡፡

ያዝ በለው! ማዕረግ እንደፈንዲሻ! ዝገን! የታባቱ! ሁሉ በእጃችን ሁሉ በደጃችን! ጠላታችን ደስ አይበለው፤ ወዳጃችን ይመርበት ነው መልሳቸው፡፡

እዚህ ላይ ስም መጥቀሱ ብዙም አስደሳች አይሆንም እንጂ እየጠቀስን ብንዘረዝር ማን ከምን ተነስቶ በአንድ ጊዜ ምን እንደሆነ ስናይ፤ በእርግጥ ማዕረግ እንደ ቡና ቁርስ እየዞረ እንደተዘገነ እንረዳለን፡፡ ከዚህ ጊዜ በፊትም በአንድ ወቅት እንዲሁ ዘግነው ያለስራ ውጤታቸው ከፍ ያሉ ነበሩና አሁንም ደግመው ሲዘግኑ የበለጠ ደረጃ ላይ የደረሱ በርካታ ናቸው፡፡

ሻለቃ የነበረውን በአንድ ጊዜ አራት እርከን አዘልለው ሜጀር ጄኔራል፣ ሌተናል ኮሎኔል የነበረውን አራት ግዙፍ ግዙፍ ደረጃዎችን አዘልለው ሌተናል ጄኔራል እያሉ አንቆጠቆጧቸው፡፡ ከሹመቱ ጋርም በግዙፍ ግዙፍ የጦር ክፍሎች ላይ የአዛዥነት ስልጣን ተሰጠ፡፡ ያለ ልምድ፣ ያለ ችሎታ፣ ያለ ትምህርት፣ ያለ ስልጠና የተሾሙት ባለሥልጣናት ስለተመደቡበት ከፍተኛና ቁልፍ ቦታ እንዳችም ግንዛቤ የሌላቸው ቀላል ቁጥር አልነበራቸውም፡፡ ቢያንስ እንኳን ተቀራራቢ ማዕረግ የነበራቸውን ከፍ እንዲሉ ማድረግ አላስፈለገም፡፡ ይልቁንም በትክክለኛው አካሄድ ብርጋዴል ጄኔራል ሆነው የቆዩትን ሜጀር ጄኔራል ማድረግ ሲቻል እነሱ ባሉበት ቆመው ቀርተው ከሻለቃነት ተነስተው



በአንድ ቀን ሜጀር ጄኔራል በሆኑት ስር እንዲሆኑ ተደረገ፡፡ አሁንም በዚህ ተግባር ሌላ የሞራል ድቀትና የስነልቦና ውድቀት ተከሰተ፡፡

ሙያና ብቃት በታማኝነት ተሻሩ፡፡ ታዲያ ያንን ሁሉ በግድም በውድም የታጠቀ ጦር ሠራዊት ማን ይምራው? ውጊያውስ በምን አይነት የጦር ሜዳ እቅድ ይከናወን? ማንስ በማን ይታዘዝ? ደርግስ ሽንፈቱን በዚህ መልክ ካፋጠነው በኋላ እንዴት ድልን ይጠብቃል? እኛስ ምን እንጠብቃለን? ወደተከታዩ ርዕሰ ጉዳያችን እንለፍ እንጂ፡፡

ግላስኖስት እና ፔሬስትሮይካ

የደርግ መንግስት የውስጥ ሠላም ቢያጣም፤ ሁኔታው ሁሉ በጦርነት ላይ ጦርነት፣ በችግር ላይ ችግር ቢሆንበትም ሁሉንም ነገሮች ለመለወጥና ቅርፅ ለማስያዝ ተፍ ተፍ ማለቱን ቀጥሏል፡፡ ሆኖም የውስጥ ረብሻው ሳይበቃ ሌላ መዘዝ መጣ፡፡

የሶቭየት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ ዋና ፀሐፊና የፌዴራል ሪፐብሊኩ ፕሬዝዳንት ሊዮኔድ ብሬዥኔቭ ከሞቱ በኋላ ቸርኒኮቭና ሚሊንኮቭ የተባሉ ሁለቱ አረጋውያን በተከታታይ የሶቭየትን ፕሬዝዳንትነት ስልጣን ይዘው የነበረ ቢሆንም፤ አፍታ ሳይቆዩና እውቅናም ሳያገኙ በሞት ስለተለዩ፤ እ.ኤ.አ በ1985 መጋቢት ላይ (በእኛ አቆጣጠር 1977 ዓ.ም መሆኑ ነው) ሚካኤል ጎርባቾቭ የሶቭየት መሪ ሆነ፡፡

ብዙም ሳይቆይ ጎርባቾቭ የኮሚኒስትን ስርዓት ሰብዓዊ ገጽታ ለመስጠት በሚል መነሻ አዲስ መፈክር ይዞ ብቅ አለ፡፡ የመፈክሩን ዓላማም ለኮሚኒስት ፓርቲው አባላትና ለአገሪቱ ባለሥልጣናት ማስረዳቱን ቀጠለ፡፡ የሶቭየት ኅብረት የወደፊት አቅጣጫ ምን መምሰል እንዳለበት፣ የሶሻሊስት ስርዓቱ ያስገኛቸውን አገራዊ እድገቶች እንዴት ጠብቆ ማቆየትና ማስቀጠል እንደሚቻል ሲሰብክና የሀሳቡን ደጋፊዎች ሲያሰባስብ ቆይቶ እ.ኤ.አ በ1989 “ፔሬስትሮይካ” የተሰኘ መጽሐፍ አሳትሞ አስራጨ፡፡

በጎርባቾቭ አገላለፅ ፔሬስትሮይካ ማለት “አንድ አገር ባለችበት እንዳትረግጥ አዳዲስ አሰራሮችን መዘርጋት፣ ማኅበራዊ እድገትን ማፋጠን፣ የአሠራር ስልቶችን ለማፋጠን ሲባል የሚካሄዱ የቅየሳ ስልቶችን ስላልተለመዱ ብቻ ፈጥኖ መቀበል እንጂ ማንገራገር ተገቢ አለመሆኑን፤ በዚህ ዓይነት አሰራር የሚገኙ እድገቶችን ጠብቆ ከማቆየት ባለፈ፣ የበለጠ መሻሻል ሊያስገኙ የሚችሉ ሌሎች ዘዴዎችን ከመጠቀም ወደኋላ አለማለት፣…” የሚል ነው፡፡ የዚህ መፈክር ቅጥያ የሆነውን “ግላስኖስት”ን ደግሞ ወዲያው ደረበበት፡፡ “ግላስኖስት” በጎርባቾቭ ገለፃ፤ “ግልፅነት” ማለት ሲሆን፤ በግልፅነት ውስጥ ተካተው የሚተነተኑት ደግሞ “ህዝቡ የራስ ተነሳሽነት እንዲኖረው ማበረታታት፣ የፈጠራ ስራን ማጎልበት፣

ስርዓት ያለው ግልፅነትን መፍጠር፣ ለእያንዳንዱ ግለሰብ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት፣ ሰብዓዊ ክብሩን መጠበቅ፣ በራሱ መቆምና በራሱ መተዳደር እንደሚችል መንገር፣ በሶሻሊስታዊ ስርዓት ያልተቆጠበ የንግድ ስራን ማበረታታትና ታላቋን ሶቭየት በየዘርፉ በፍጥነት ማዘመን…" የሚል ሆኖ፣ በግርድፉ ሲታይ በጎ አስተሳሰብ መስሎ ውስጡን ለቄስ የሚሉት አይነት መፈክር ቢሆንም፤ ጐርቫቾቭን "ያዲሲቷ ሩሲያ መሪ" ብሎ ህዝቡ አወደሰው:: ምዕራባውያን ጐርቫቶቭ ምን እያለ እንደሆነ በጥልቀት ገብቷቸዋልና የብሪታኒያና የአሜሪካ መሪዎች ባልተለመደ ሁኔታ ጐርቫቶቭን ደጋግሞ መገናኘት፣ መወያየት ትልቁ ስራቸው ሆነ::

የግላስኖስትና የፔሬስትሮይካ ጥምር ፖሊሲ በሂደት የሶቭየትን ብቻ ሳይሆን የዓለምን የኃይል ሚዛን ሙሉ ለሙሉ ለወጠው:: ታላቋ ሶቭየት ኃያልነቷ አክትሞ ለምዕራቡ ርዕዮት መንበርከክ ነበረባት::

ሌላው አገር እንኳ በሶሻሊስት ስርዓት የሚገኙ አገራዊ ጥቅሞችን አጣጥሞ ሰላቆዬ ብዙም አይከነክንም:: ለኢትዮጵያ ግን ደፍራ የማትጎነጨው ፅዋ ነበር:: ፔሬስትሮይካ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ፤ ሶቭየት በምስራቅ አውሮፓ አገሮች ላይ አሳርፋው የነበረውን ክንድ አነሳች:: የኢኮኖሚ ትብብሯን አቆመች፣ የሚጠቅሟትንም የማይጠቅሟትንም ራስ ራስህን ቻል በሚል ግልፅነት በተሞላበት አገላለፅ እየገፈተረች ወደራሷ ተመለሰች:: ምስራቅ አውሮፓ በለውጥ ማዕበል ተናጠ:: የበርሊን ግንብ ፈርሶ ምስራቅና ምዕራብ ጀርመን ተቀላቀሉ::

በሶቭየት ሶሻሊስታዊ ርዕዮት ተጠምቀው ለዘመናት የርዕዮቱ ታማኝ ሆነው ሲተዳደሩ የነበሩ የፖላንድ፣ የሮማኒያ፣ የቼኮዝላቫኪያ፣ የአልባኒያ … ህዝቦች ኮሚኒስት መሪዎቻቸውን በአመፅ ከስልጣን አባረሩ፣ አሰሩ፣ ገደሉ::

እነ ብሬዥኔቭ "የኢምፔሪያሊዝም ነፀብራቅ" እያሉ ሲያወግዙት የኖሩት ነገር ሁሉ በጐርቫቶቭ ተቃራኒ መፈክር ይበረታታ ጀመር::

ፔሬስትሮይካ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ የሚያመጣ፣ ግላስኖስት ፖለቲካዊ ነፃነት የሚያላብስ ትርጉም እንዳለው ግልፅ እየሆነ ሄደ:: በግላስኖስት መፈክር በ14 ትናንሽ አገሮች ታጅባ በታላቅነት ስም ሶቭየት ኅብረት እየተባለች በገናናነት የቆየችው ሩሲያ የፌዴሬሽን ውላቸውን ቀድዳ ጥላ በሠላም ሸኘቻቸው:: አገራቱ የየራሳቸውን ባንዲራ መልሰው አነሱ:: እነዚህ አገሮች ኮሚኒስት መሪዎቻቸውን በአመፅም በምንም አስወግደው ሌላ ባለሥልጣን ሲተካ የምዕራብ ዓለሙን ርዕዮት ለመከተል አማተሩ:: ምዕራባውያንም እቅፍ ድግፍ አድርገው ተቀበሏቸው፤ በካፒታሊዝምም አጠመቋቸው::



በፔሬስትሮይካ መፈክር መሠረትም የቅይጥ ኢኮኖሚን በመከተል ሩሲያ ብቻዋን የምትገፋ መስላ ቆየች:: የቀዘቃዛው ጦርነት ማክተም የዚህ መፍክር ውጤት ሆኖ እንደትልቅ ጀብደኛ ጐርቫቶቭ ተወደሰበት::

በአሜሪካና በእንግሊዝ ጉትጎታ የመፈክሩን ውስብስብነት በፍጥነት እንዲገላልጥ የተመከረው ጐርቫቶቭ፤ "እሺ" አለ:: ከአነሳሱ በበጎ ታይቶ የነበረው መፈክር የሶሻሊስት አራማጅ አገሮችን ሁሉ አጠቃሎ በአሜሪካና በእንግሊዝ ኅተራ ከተታቸው:: ከዚሁ ጋር ታላቋ ሶቭየት ፈራረሰች:: ለዚህ ተግባሩ ነው ጐርቫቶቭ የኖቤል ሽልማት የተሸለመውና ከሽልማቱ ጋር በተሰጠው ገንዘብ ሚሊየነር ሆኖ ህይወቱን በተደላደለ መንገድ መምራት የቀጠለው:: የጐርቫቶቭን ክህደት የተረዳው የሶቭየት ሠራዊት በመሪው ላይ አደመ::መፈንቅለ መንግስትም ሞከረ፤ ሆኖም ወዲያው አድማው ተበትኖ ሙከራውም ከሸፈ:: ጉርቫቾቭ ይህን ካደረገ በኋላም ስልጣኑን ለቦሪስ አስረክቦ ከጨዋታ ሜዳው ወጣ::

በሶቭየት አንጋችነት ህልውናቸውን መስርተው የነበሩ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች ሶቭየት ስትፈራርስ በድንገት ክልትው፣ ክልትው አሉ::

መንግስቱ ኃይለማርያም በዙምባቡዌ ሐራሬ ሆነው ለጣሊያናዊው ጋዜጠኛ ለሪካርዶ ኦሪዚዮ ይህን ጉዳይ በተመለከተ የገለፁለትን ከራሳቸው አንደበት እናድምጥ::

"… ጐርቫቶቭን የማውቀው ገና ወጣት የማዕከላዊ አባል ሳለ ነው:: ፖሊት ቢሮ ሳይገባ በፊት" … መንግስቱ በእርጋታና በጥርጣሬ የተሞላው እንግሊዝኛቸው፤ የሶቭየት ጉዳይ ሲነሳ ለወጥ ይልና ፈጣን ይሆናል ይለናል ሪካርዶ ኦሪዚዮ::

"… ጐርቫቶቭ ሲመለከቱት ጥሩ ሐቀኛና ለሶሻሊዝም ታማኝ ሰው ይመስል ነበር:: ለእኔ የነበረው ስሜትም ወዳጃዊና የጋለ ነበር:: ይሁንና በ1985 ስልጣን ላይ ፊጥ ብሎ ከወጣ በኋላ ግን ፔሬስትሮይካና ግላስኖስት ማለት አመጣ:: በዚህ ጊዜ ታዲያ ስለሁኔታው በጥልቀት ለመረዳት በማሰብ አዲስ አበባ ሆኜ ቀጠሮ ለመያዝ ስልክ ደወልኩለት:: ምን እየተሰራ እንደሆነና የሁለቱን መፈክሮች ትርጉምም ለመረዳት ወደ ሞስኮ አቀናሁ:: ሁለቱ ቃላቶች መፈክሮች ይሁኑ እንጂ ምንነታቸውን አልተረዳሁም ነበር:: ለምን? ቢባል ደግሞ መልሱ እንኳን እኔ ቀርቶ የሶቭየት ህዝብም ስላልተረዳቸው ነው:: እናም ጓድ ጐርቫቶቭ፤ እርስ በርሳችን ግልፅ እንሁን:: የራሳችንን አቅጣጫ በጊዜ ለማስተካከል እንዲያመቸን የአቅጣጫ ለውጥ ካለ ይነገረኝ:: የናንተ ጥንካሬ ጥንካሬያችን፣ ድክመታችሁ ድክመታችን ነው አልኩት::"

ጐርቫቶቭ ይህን የግል ሚስጥሩን ለሶሻሊዝምና ለሶቭየት ታማኝ ለሆኑት ለመንግስቱ መንገር አልፈለገም:: ስለዚህ ሣቅ አለና "ጓድ

መንግስቱ ኢየሰቡ፤ ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮት አንዲት ሚሊሜትር እንኳ አላፈገፍግም፡፡ በሶሻሊስታዊ የስራ ውጤታችን እኮራለሁ፡፡ ወደፊትም የምኮራ ነኝ" አላቸው፡፡

"ከዓመታት በኋላ" አሉ መንግስቱ፤ ረጋ ባለና በተቆጠበ አንደበታቸው "ከዓመታት በኋላ አማጽያኑ ወደ አዲስ አበባ በመገስገስ ላይ እንዳሉ እርዳታ በመሻት ስልክ ደወልኩለት፡፡ ለጥያቄዬ የሰጠኝ መልስ፡ እንረዳሃለን አንተ ብቻ በፅናት ቁም፡፡ ሊነቅፉህ ይችላሉ፤ ሆኖም በታሪክ ውስጥ እንደ ትልቅ መሪ የሚያስቆጥርህ ትልቅ ስራ ለኢትዮጵያ ሠርተሃል፡፡ ጥንታዊውን ዘውዳዊ አገዛዝ በመገርሰስህና በመካከለኛው ዘመን የእድገት ደረጃ ላይ የነበረችውን ሃገርህን ዘመናዊ እንድትሆን በማድረግህ በታሪክ ውስጥ ትገቢ ስፍራህን ይዘሃል፤ የሚል ነበር፡፡ ግብዝ! አሁን ለዚህ የኖቤል የሠላም ሽልማት ይስጡት? ለጠላቶች መሣሪያ እያቀበለ እኔን በቃላት ይሸነግለኛል፡፡ እየዋሸኝ እንደሆነ ስለገባኝ ከዚያ ቀን በኋላ ዳግመኛ አልደወልኩለትም፡፡ ማን ወዳጃችን፣ ማን ጠላታችን እንደሆነ እንኳ ለመለየት ባለመቻላችን መጥፎ ጊዜ እየተቃረበ ለመሆኑ ጠቋሚ ነበር"

መንግስቱ ሞስኮ ችላ ካለቻቸው በኋላ ፊታቸውን እንደገና ወደ ዩ.ኤስ. አሜሪካ አዞሩ፡፡ "... ፕሬዝዳንት ማን ነበር ስሙ? .... ማን ነበር .... ካርተር? አይደለም ቆየኝ ... ማን ነበር ከእሱ በኋላ የነበረው ...? አዎ አስታወስኩት ሮናልድ ሬጋን ነው፡፡ ሬጋን እኔን ለመርዳት እምቢ አለ፡፡ ሬጋንና ጎርባቾቭ ማለት ለእኔ ሁለት ገፅታ ያለው አንድ ሠይጣን ማለት ናቸው! ጎርባቾቭና ሬጋን ፀረ እድገት የሆነ ሴራ አንድ ላይ አሲረዋል፡፡ ጎርባቾቭ የካደው እኔን መንግስቱን ብቻ ሳይሆን መላው ዓለምንም ነው፡፡ ያፈራረሰውም ሀገሩን፣ መላውን ዓለም አቀፍ ሶሻሊስት ንቅናቄ ማለትም ኮሚኒስቱንና ብሔራዊውንም ጭምር ነው፡፡

ስልጣን ላይ የወጣው በሶቭየት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ አካባቢ የሰፈነውን ሙስና በጽኑ ለመዋጋት እንደሚፈልግ በማሳመን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ፓርቲውን ከአደጋ ለማዳን የሚያስችል ምንም አይነት የስርዓት ማሻሻያ ወይም ለውጥ ለማድረግ አልፈለገም፡፡ ስለዚህ አመጣጡ ፓርቲውን ለማፈራረስ እንጂ ለማዳን አልነበረም፡፡ ..." /TALK OF THE DEVIL 2003/

መንግስቱ እንዳሉት ምንም የቅድመ ዝግጅት ሁኔታ እንዳይደረግ ጎርባቾቭ በማለሳለስ እያዘናጋ 4 ዓመታት ያህል ከቆየ በኋላ፤ ነገሩ ሁሉ በምስራቅ አውሮፓ ትርምስምሱ እየወጣ መሆኑን ያዩት መንግስቱ ጉዳዩ ግልፅ እየሆነላቸው ሄደ፡፡

ታዲያ በቅፅበት ምን ማድረግ ይቻላል? ሲያብጠለጥሉት የኖሩትን ካፒታሊስት አገር ተደግፈው አያንሰራሩ ነገር፡፡ የርዕዮት ለውጥ



ለማድረግም አጋዥ አገር በተለይ በራሷ ላልቆመች አገር የግድ ያስፈልጋታል፡፡ በነበረው አይቀጠል ነገር ባለቤቱ ተንሻፈፈ ብሎ የጣለውን ጫማ እኛ አጥልቀን እየተባለ ተቃዋሚው በዛ፡፡ እንዲያ ሲያዜሙለት፣ ሲፎክሩ ሲሸልሉበት፣ ተፈጥሮን በቁጥጥር ስር እናደርጋለን እያሉ ሲዝቱበት የነበረው ርዕዮት፣ ሶሻሊስታዊ ኢትዮጵያን እንገነባለን ተብሎ በሕገመንግስቱ ሳይቀር አንቀፅ የተበጀለት ... ሕገመንግስቱ በፀደቀ ገና ሁለት ዓመት ሳይደፍን ሶሻሊዝም ሲሞት መንግስቱ እንዴት ግራ ይገባቸው? መጥኔ! እንግዲህ ምን ይሁን? ያን መራራ ፅዋ ከመጎንጨት በቀር ምርጫ የለም፡፡

ከጥቅምት 29 እስከ ህዳር 2 ቀን 1981 ዓ.ም ተደርጎ በነበረው የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 9ኛ መደበኛ ስብሰባ ድርጅቱ የመጨረሻ ግቡ የሶሻሊስት ስርዓቱን መገንባት እንደሆነ ቢያረጋግጥም፤ የግል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት መጠነኛ እርምጃዎች ለመውሰድ ተገዶ ነበር፡፡ በዚህም ከመንግስት ጋር በጋራ የሚሰሩ ኢንቨስተሮችን፣ የአነስተኛ ኢንደስትሪዎችንና የሆቴል አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችን የካፒታል ጣራ ከፍ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ነገር ግን በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተካሄደ ከነበረው ለውጥ ጋር ሲመዛዘን ፈፅሞ በቂ አልነበረም፡፡ ስለዚህ የነገሩን ቁርጥ መሆን የተረዱት ጓድ ፕሬዝዳንት የካቲት 28 ቀን 1982 ዓ.ም በተካሄደው የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 11ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የሶሻሊስት ግንባታ መርህን በመሠረዝ የቅይጥ ኢኮኖሚ መርሐግብርን አፀደቁ፡፡ በፖለቲካው በኩልም ኢሠፓን የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶችን ሊያቅፍ በሚችልና "የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (ኢዴአፓ) በተሠኘ አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ እንደሚተካ አረጋገጠ፡፡ ምንም ቢባል ግን ረፍዶ ነበር፡፡

እነ አጥናፉ አባተ የሞቱበት፣ የሞቱለት ወይም የተገደሉበት የ"ቅይጥ ኢኮኖሚ" ጭቅጭቅ ቀኑ ከጨለመ በኋላ ፀደቀ፡፡

በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ ፕሬዝዳንት መንግስቱ እነዚህን ውሣኔዎች ሲያፀድቁ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላቱ በስብሰባው እለት እየተነሱ ሶሻሊዝምን እየወረፉ በሚያስቅ አነጋገር አዳራሹን በሣቅ ሲንጡት መዋላቸው ነው፡፡ ይህንንም ያይን እማኞች ደጋግመው ተርከውታል፡፡

ሻለቃ ካሣዬ አራጋው ከስብሰባው መሃል ብድግ ብለው፤ "ይሄንን የሰው አገር ደበሎ አውልቀን እንድንጥል በማድረግዎ፤ በታሪክ ትልቅ ስፍራ የሚያሰጥዎ ነው ...!" እያሉ ሲናገሩ፤ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ቀበል አድርገው፤ "ደበሎ አልከው ካሣዬ? ሰው አበላሸው እንጂ ቢያንስ ለደሃው ገበሬ የኑሮ ለውጥ ያመጣ ስርዓት ነበር፡፡ የአንድ እናት ልጆች እርስ በርስ የተሳየፍንበት የብዙ ሺህ ሰዎች ደም የዋጀው ክቡር ዓላማ ነበር" አሉ በቁጭትም፤ በትዝብትም፡፡ ቀጥሎ ኮሎኔል እንዳለ ተሠማ ተነሱና፤

"በእውነቱ ጓድ ሊቀመንበር እርስዎ ትናንት በተናገሩት የአዲስ አበባ ህዝብ ከደስታው ብዛት በውስኪ ሲራጭ ነው ያነጋው..." ሲሉ ተሰብሳቢው ሁሉ በሣቅ አውካካ።

ፕሬዝዳንቱ በምፀት ሣቅ ጥርሳቸውን ብልጭ አድርገው አንገታቸውን ደፉ።

ዳቦ ጠፍቶ ህዝቡ በየዳቦ ቤቱ ወረፋ ይዞ በሚፋለምበት ወቅት ስለውስኪ መራጨት ማውራት አስቂኝም፣ አሳዛኝም ነዋ። ያም ሆኖ ከ5 መቶ ሺ. ብር በላይ ካፒታል ያለው ግለሰብ ነጋዴ እንዳይኖር ተደርጎ የነበረው ደንብ ከፍ ማለት እንደሚችል በመታወጁ ደስ የተሰኙ ባለሃብቶች መኖራቸው አይዘነጋም።

የሆነው ሆኖ ተግባራዊ ለውጡን በውል ያላወቁትን፤ ነገር ግን በቃሉ ፍቅር ወድቀው የተዋደቁለትን ርዕዮት ሳይወዱ በግድ መነጠላቸው ሳያንስ፤ ትናንት የወርቅ ካባ ያሉትን በቅፅበት ደበሎ እያሉ ሲፎልሉበት ማየት እስተዛዛቢ ነበር።

ከዚህ በኋላ ልዩ ልዩ የሙያ ማኅበራት እየፈራረሱ፣ የተደራጁ አምራቾች ጥሪታቸውን ተከፋፍለው እየተበታተኑ፣ ከመንግስት ቁጥጥር ውጪ ሆነው በየመስላቸው የግል መንገድ መንጎድ ጀመሩ። ሁሉም ነገር አቅል አጣ። ፓርቲ ነሽ፣ ወታደር ነሽ ምንድነሽ .... እየተሰነጣጠቀ፣ እየተፍረከረከ ሄደ። ትዕዛዝ ከላይኛው አካል ወደታች ደርሶ መፈፀሙ አጠራጣሪ ሆነ። አማፅያኑ በየቀኑ አዳዲስ ግዛት መያዝ ቀላል ተግባር ሆነላቸው። ጠሩ ሽሽትን ስራዬ ብሎ ያዘው። ለደርግ መንግስት የሚወግን ታማኝ ወዳጅ አገር ጠፋ። የመንግስቱ ታማኞች እንደድሮው ማጎብደድ፣ ለመወደድ መጣጣራቸውን አቆሙ። በአጭሩ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ብቻቸውን ሲፍገመገሙ ነው ቀሪዋን አንድ ዓመት ያሳለፏት ማለት ይቻላል።

እንዲያውም ብርቱ ሆነው እንጂ እንደነገሩ አስደንጋጭነት ቢሆንማ፤ "ግላስኖስት፣ ፔሬስትሮይካ፣ ግላስኖስት ፔሬስትሮይካ..." እያሉ አብደው በአደባባይ ቢዞሩ ማን ይፈርድባቸው ነበር? የሰው ብርቱነት ይሄን አይነት ክስተት በመቋቋሙ ይረጋገጣል።

### የደርግ መንግስት ፍፃሜ እና የኢህአዴግ ድል

ዛሬም ድረስ ሁሉንም ወገን የሚያስገርም ጥያቄ ነው። ሌላው ቀርቶ የቀድሞ የኢህአዴግ ታጋዮች የጦር ግንባር ትዝታቸውን ሲተርኩ፤ ".... አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው ... ያንን የሚያክል ግዙፍ ሠራዊት፣ ታንኩ፣ ጀቱ፣ ...." ዋ...ይ ዘይገርም! በማለት ከመደነቃቸው ብዛት የጀመሩትን ዓረፍተ ነገር መቋጨት ይሳናቸዋል።

ደርግ በአፍሪካ ውስጥ ግዙፍ የተባለ ሠራዊትን ነበር ያደራጀው። በ12 ቢሊዮን ዶላር ወጪ እንዲገነባ የተደረገው የደርግ ሠራዊት በመቶ



ሺዎች የሚገመት የሰው ኃይልም ነበረው። ሽንፈቱ የዳዊትንና የጎሊያድን ፍልሚያ የሚያስታውስ ነው። ምንም እንኳ ተቃዋሚዎቹ የአሜሪካን መጠነ ሰፊ ድጋፍ ቢያገኙ፤ ታጋዮቹ ራሳቸው የዓላማ ፅናታቸውና ጀግንነታቸው አስደናቂ ቢሆን፣ የአመራሮች ብቃት ባያጠያይቅ፣ በውጊያ ስልት ከደርግ ቢበለጡ፣ እንዴት ለድል በቁ? ብሎ ከመጠየቅ የቦዘነ የለም።

ለድል የበቁበትን ምክንያት የሚገልፁ ዘርፈ ብዙ ትንታኔዎች ቢሰጡም፤ "ምንም ይሁን፤ ቢያንስ እንኳን ደርግ በነበረው የሰው ኃይል ብዛት ብቻ እንዴት አላሸነፈም?" የሚል መከራከሪያ መነሳቱ አይቀርም። ጥያቄውን ተገቢ ጥያቄ እንዲሆን ያደረገ የሰፋ ያለመመጣጠን ልዩነትም ነበራቸው።

ቢሆንም፤ መፈንቅለ መንግስቱ ያስከተለውን መዘዝ ሳንዘነጋ፤ የደርግ መንግስት የሰው ኃይሉን በአግባቡ ተጠቅሞ እንዳያሸንፍ እንኳ ሌላ መሰናክል ተፈጥሮበት ነበር። ይህም የወኔ፣ የስንቅና የትጥቅ፣ እንዲሁም የጀግንነት ችግር ያልነበረበትን ግዙፍ ሠራዊት ወኔውን ሰልቦ፣ ጀግንነቱን ነጥቆ፣ ሥነልቦናው እንዲላሸቅና ተፍረክርኮ እንዲቀር የሚያደርግ ተግባር መፈፀሙ ሲሆን፤ ከራሳቸው ከቀድሞ ባለሥልጣናት አንደበት እንደሚከተለው እንሰማዋለን። ነገር ግን የታጋዮቹን ጀግንነት ለማደብዘዝ እንዳልሆነ በቀላሉ መታወቅ አለበት። የነሱ ጀግንነት የሚያጠያይቅ አይደለምና።ከዚያ ባለፈ ለማሳየት የሻትኩት የጃንሆይን ዙፋን ያወዛወዘው ሙስና መሆኑን እንዳየነው ሁሉ፤ ለደርግ መንግስት ውድቀት መፋጠንም ሙስና የማይናቅ አስተዋፅኦ ማበርከቱን ነው።

በ1996 ዓ.ም ከእስር የተለቀቁት ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ ዛሬም ድረስ በእስር ላይ ሆነው ዓለም በቃኝ የሚገኙ የቀድሞ የደርግ ባለሥልጣኖችን ሁሉ አነጋግረው በ2001 ዓ.ም ለሕትመት ካበቁት "ምስክርነት" ከተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ የተገኙ ምላሾችን ነው የምናየው።

ፀሐፊው "የምድር ጦር ወታደራዊ ደህንነት ኃላፊ የነበሩትን ኮሎኔል ታምራት ይልማን ስለመከላከያ አዛዦች ችግር፣ ስለጦር አለቆች ደካማነትና በንቅዘት የተዘፈቁ መሆናቸውን በሚመለከት ላቀረብኩላቸው ጥያቄ መልስ ሰጥተውኛል" ይላሉ።

ኮሎኔል ታምራት ይቀጥላሉ፤ "... ደርግ የጠሩን ድርጅት ለማሟላት በገፍ ያቀርባል። ነገር ግን የነበሩት የጦር አዛዦች ደግሞ በከፋ ዘረፋ ላይ ተሰማሩ። አዛዦቹ የጦሩን ቀለብ ያለ ይሉኝታ ለነጋዴ ሸጡት። ስኳር፣ የጦር ቀለብ፣ ልብስ፣ ጫማና ካልሲ ሳይቀር በጠራራ ፀሐይ መርካቶ፣ ወሎ፣ ደሴና አስመራ ለነጋዴ ተቸበቸበ። ንቅዘት ነውር መሆኑ የቀረ መሰለ። የጠሩ መኪናዎች ከነተሳቢዎቻቸው የጦር ድርጅቶችን ጭነው መርካቶ ለገበያ መቅረባቸው ይፋ ሆነ።..."

ይህን ጉዳይ እነ ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን በጠሩ ስም የፍጆታ እቃዎች እያወጡ ለነጋዴ ይሸጡ እንደነበር የምድር ጦር ወታደራዊ ደህንነት ኃላፊ ኮሎኔል ታምራት ይልማ፣ የበፊት የአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስትር የነበሩት ኮሎኔል መርሻ ወዳጆም አጉልተው እንደሚናገሩት ፀሐፊው

ይገልፃሉ፡፡ ምላሻቸው ይቀጥላል፤ "... የጦር ድርጅት፣ ቀለብ፣ የሠራዊቱ ደሞዝ፣ መድሐኒት ማናቸውም ለሠራዊቱ የሚጠቅም ነገር ሁሉ እየተዘረፈና እየተሸጠ ወደግል ኪስ ገባ፡፡ የጦር አለቆች ከሾፌሮች ጋር በመመሳጠር ነዳጅ፣ ስኳር፣ ጥይት፣ መድሐኒትና ሌሎች ለውጊያ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን ጭምር ለሚወጋቸው ጠላት ያለይሉኝታ ሸጡት፡፡ (የደብረብርሃንና የደብረታቦር ግንባር በዚህ የበለጠ ታዋቂ ነበሩ)

"ማሰልጠኛ ማዕከሎች የንቅዘትና የዘረፋ ማዕከሎች ሆኑ፡፡በሰልጣኞች ስም ከማከፋፈያ ድርጅቶች የማይጠየቅና የማይገዛ የፍጆታ ሸቀጥ አልነበረም፡፡ በጦሩ ስም የከፈን ጨርቅና የሬሣ ሳጥን ጣውላ ሳይቀር ተገዝቶ ተሸጧል፡፡ የጦሩ አለቆች የጦሩን ደሞዝ፣ ለቤተሰቡ የሚያደርገውን ተቆራጭ ነግደውበታል፡፡በወለድ ለነጋዴ እያበደሩ ከብረውበታል፡፡ ባንክ ውስጥ በስማቸው እያስቀመጡ ወለድ አግኝተውበታል፡፡በዚህ አድራጎታቸውም በሚመሩት ጦር ላይ የአስተዳደር በደል አድርሰውበታል፡፡ወደ መውደቂያችን መቃረቢያማ የጦር አለቆች የቀን ጅብ ሆኑ!" በማለት ይናገራሉ፡፡ለዘረፋና ለጥቅም ሲባል የዘመቻ እቅዶች ይነደፉና እንዲከሽፉ ይደረግ እንደነበርም ጨምረው ይገልፃሉ፡፡

"በሞቱ፣ በጠፉ፣ ወይም በተማረኩ የጦሩ አባላት ስም የሐሰት ሠነድ እየተፈረመ ስርቆት ተፈፅሟል" (ገፅ 409)

ፀሐፊው የምድር ጦር የአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ መኮንን ለነበሩት ለዘገየ ልውል ሠግድ ሙስናን በሚመለከት ጥያቄዎችን አዘጋጅተው ይሰጧቸዋል፡፡ ምላሽ ሰጭው መልሱን ለመስጠት ቃል ገቡና በሦስተኛው ቀን እንዲህ አሏቸው፤ "ወንድሜ ሆይ! ቃሌን በማጠፌ አዝናለሁ፡፡ የማስታውሳቸውን የዘረፋና የንቅዘት ጉዳዮች በቅደም ተከተል መዝግቤ ልሰጥህ ካልኩ በኋላ መልሼ ሳነባቸው ህሊናዬን አስጨነቁት፡፡ ዘራፊ ሰዎችን በተራ ደርድሬ ያሰለፍኳቸው መስሎ ታየኝ፡፡ በዚህ የተነሳ የፃፍኩትን ቀድጄ ጣልኩት" በማለት መለሱ፡፡ ይሄን ያህል ዘግናኝና ለመግለፅ የሚቸግር ከአእምሮ በላይ የሆነ ዝርፊያ ተጧጡፎ ነበር፡፡

የበርካታ ሌቦችን ስም ዝርዝር ቀደው የጣሉት ሰው በቃላቸው በጥቂቱ መልስ ለመስጠት ሞክረዋል፡፡ እንዲህ ይነበባል፤ "እኛ የሠራዊቱ መሪዎች እጅግ አሳፋሪ ታሪክ አለን፡፡ እገሌ ከእገሌ ሳይባል የጦር ማሠልጠኛ ማዕከላት አዛዥ የነበሩ፣ የፋይናንስና የድርጅት፣ የስንቅና ትጥቅ መምሪያ መኮንኖች፣ ደመወዝ ከፋዮችና የትራንስፖርት ክፍል ኃላፊዎች፣ ሐረርጌ ውስጥ ከ"ኩልሚስ" (ከሶማሊያ ታጋዮች) ጋር ተመድበው በማንኛውም ደረጃ የሰሩ የሠራዊቱ አባላት እጅግ ከፍተኛ ዘረፋ አካሂደዋል፡፡

"ማንኛቸውም የስራ ኃፊነታቸውን ትተው በቀጥታ በዘረፋ ተሰማርተው ነበር፡፡ የጦር አለቆችን በስም ጠርቼ ስነግርህ በጣም ቅር ይለኛል፡፡ የፈፀሙትን ዘረፋ መጠን መገመት ለህሊና ይከብዳል! ሠነድ ተደልዟል፣ የሞቱ ወታደሮች ደመወዝ ተበልቷል፣ ሌላው ቀርቶ የጦር አዛዦች የመንግስት ባንክ ዘርፈዋል፡፡ የባህርዳር ንግድ ባንክና የደብረብርሃን ንግድ



ባንክ ቅርንጫፎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ (ዘራፊው ጄኔራል በቦንብ ጋየ ብለው ዋሽተው ነበር) "... የፈንጅ ማምከኛ የሚሆኑ አህዮች መግዣ ተብሎ ከመንግስት ገንዘብ እየወጣ ተዘርፏል፡፡ ሳስበውና ሁኔታው ከፊቴ ሲመጣ ያስጨንቀኛል፡፡ በአገርና በህዝብ ላይ ከፍተኛ ደባና በደል ተፈፅሟል" ብለዋል፡፡ በነገራችን ላይ የሁሉም ባለሥልጣናት ግልፅ የሆኑ ተመሣሣይ የእምነት ቃሎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ቀድሞ በየግንባሩ ሲታገሉ የቆዩና የሲቪል ህይወት የጀመሩ ተራ ወታደሮችና ባለሌላ ማዕረጎችም እየዘገቡናቸው የሚተርኩት እውነታ ነው፡፡ ሌላው ፀሐፊው እስር ቤት ውስጥ ያነጋገሯቸው የምድር ጦር ስንቅና ትጥቅ መምሪያ መኮንን የነበሩትን ብርጋዴል ጄኔራል ሰብስቤ ንጋቱን ነው፡፡

ጄኔራሉ፤ "... አለቆች ብዙዎቹ መጠን የሌለው ስግብግብነት አጠቃቸው፡፡ ለጦሩ ስንቅ ይቀርቡ የነበሩና ገበያ ያላቸው ስንዴ፣ ስኳር፣ ሻይ ቅጠል፣ ጤፍ፣ የመሣሠሉትን መሸጥ የተለመደ ሆነ፡፡ ስኳር "ገፍትር" የሚል ስም ወጥቶለት ለሠራዊቱ ከማደል ይልቅ ለነጋዴ መገፍተር፣ መቸብቸብ የተለመደ ሆኖ ነበር፡፡ ለጦሩ ቀሊብ ተብሎ ወደ ጢጣ ወሎ የተላከ የሠራዊት ስንቅ ደሴ ከነጋዴ መጋዘን ውስጥ ሲራገፍ ተይዟል፡፡ ለጦሩ ቀለብ በዋናነት የሚቀርበው ጤፍ ነበር፡፡ ጤፍ ማቅረብ ችግር ስለነበር 40 በመቶ ጤፍ፣ 35 በመቶ ስንዴ፣ 25 በመቶ ማሽላ ወይም ዘንጋዳ ተቀናጅቶ እንዲፈጭና እንጀራ እንዲሆን ይደረግ ነበር፡፡ የአገዳ የእህል ውጤት የሆነ ዱቄት መነፋት ስላለበትና፤ ሲነፋ በኩንታል ከሰባት እስከ አስር ኪሎ ሊጎድል ስለሚችል ተስተካክሎ እንዲላክ ተወስኖ ነበር፡፡ ነገር ግን የጦሩ ቀለብ አቅራቢ መኮንኖች ዱቄቱን አያስነፉትም፤ የማያስነፉትም ለስርቆት እንዲመች ነበር፡፡ ሳይነፋ እንጀራ ሁን ሲሉት እህል እህል አይልም፡፡ ጦሩም ሳይበላ ተዋጋ ይባላል! ችግሩ እየታወቀ እርማት አይደረግም፡፡ ስርቆቱ ከታች እስከ ላይ በሰንሰለት ስለነበር አጥፊዎች አይጋለጡም፡፡ ቅጣት አይደርስባቸውም፡፡

"በወሎ ጢጣ የነበሩ የጦሩ አለቆች ለጠላት የከባድ መሣሪያ ጥይት ጭምር ሸጡ፡፡ ቀለብ የሚሰፈርለት በበጀት የሚታወቅ የኢትዮጵያ ሠራዊት 300,000 /ሦስት መቶ ሺ/ ደርሶ ነበር፡፡ ለቀለቡም መንግስት በዓመት ብር 344,000,000 /ሦስት መቶ አርባ አራት ሚሊዮን ብር/ ይሰፍር ነበር፡፡ የአዛዦቹ ዘረፋ ይሉኝታ አጥቶ ነበር፡፡" በማለት ሁኔታውን ዘርዝረውታል፡፡ ሌሎች ጄኔራሎችም ይሄንኑ አረጋግጠዋል፡፡

"... በተለይም የደርግ አባሉ ሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን መጀመሪያ የመከላከያ ሚኒስትር፣ በኋላ የኤርትራ ራስ ገዝ ዋና አስተዳዳሪና የጦሩ የበላይ አዛዥ ሆነው ዓይን ያወጣ ዘረፋ ይፈፅሙ ስለነበር ብዙ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ተከተሏቸው፡፡

"ከጄኔራሉ ጋር እጅና ጓንት ሆነው ዘረፋውን አጧጧፉት፤ በጦሩ ስንቅ ማመላለሻ ከባድ መኪኖች፣ በአውሮፕላንና በመርከብ ያለይሉኝታ ለነጋዴ ሸቀጥ አዲስ አበባና አስመራ እያመላለሱ ሸጡ" የደርግ አባሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ፍቅረስላሴ ወግደረስ ተስፋዬ ገብረኪዳንን ሲገልጿቸው፤ "ደፋር፣

ዘራፊ፣ ከሰው ተግባቢ፣ ለምንም ነገር ደንታ ቢስ፣ ደስታና ፌንጠዝያ ወዳጅ…" በማለት ነው፡፡ /ገጽ 412/

ከዚህም ባለፈ "የሦስት ማዕዘን ዕዝ" አደረጃጀት ለጦሩ ሽንፈት ተጨማሪ ሚና እንደነበረው በብዙዎች ተገልጿል፡፡ የፖለቲካውም ሆነ የወታደራዊው ደህንነት ባለስልጣናት እርስ በርስ ይወነጃጀላሉ፡፡

ብርጋዴር ጄኔራል ግርማ አየለ፤ "የጦር አዛዦች የሙያ ብቃት የጎደላቸው፣ ሌሎች አመራሮች አብዮቱን አምርረው የሚጠሉ፣ መጀመሪያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደርን፣ በኋላ የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊኩን ለመጣል የታገሉ የአገር ፍቅር የነጠፈባቸው ዘራፊዎች! ናቸው" ብለዋቸዋል፡፡ ሦስት የተለያዩ አዛዦች ሲመደቡም መረጃው እያፈተለከ በጠላት እጅ በቀላሉ ይገባ ነበር፡፡

እንዲህ ነው፡፡ እንዲህ ሆኖ ደመወዜ ለቤተሰቤ ይሰጥልኛል ብሎ ህይወቱን በየግንባሩ ሊሰዋ የተዘጋጀ ሠራዊት ከተማ ያሉ ወላጆቹ ሲራቡ፣ ለአገሩ የሚከፍለው ዋጋ ከንቱነቱ እየገባው ሲሄድ ሠራዊቱ ባይፍረከረክ እንጂ ቢፍረከረክ ምኑ ይገርማል? መልሱ ይሄ ነው፡፡

የእርስ በርስ ጦርነት እንደመሆኑ መጠንም ተዘርፎ የሚቸበቸበው ስንቅና ትጥቅ፣ እንዲሁም አልባሳት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለተጋዳላዮች ይደርስ ነበር፡፡ በተለይ ስኳሩ የኢህአዴግ የጀርባ አጥንት ነበር፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን በሙስና በጠላቶቻቸውም በወዳጆቻቸውም ፈፅሞ የማይታሙት ፕሬዝዳንት መንግስቱ፤ ሁኔታውን መቆጣጠር ተስኗቸው ከወዲያ ወዲህ እየተንከላወሱ ማስለጠኛዎች እንዲገነቡ፣ በፍጥነት ምልመላ እንዲደረግ፣ ለጦሩ ስንቅና ትጥቅ እንዳይጎልበት ይጣጣሩ ነበር፡፡ ህዝቡ ከጎናቸው እንዲሆን በተለያየ መንገድ የማሳመንና የመቀስቀስ ተግባራቸውን ቀጥለውበት ነበር፡፡

ለምሳሌ ነገሩ ሊያበቃ ሦስት ወር በቀረው ጊዜ "የሻዕቢያ የወያኔና የኦነግ የተባበረ ውጊያ መንግስትን ከመጣልና ፕሬዝዳንቱን ከማባረር አልፎ ህዝብን የመከፋፈልና ሌላ ግዛት የመፍጠር ዓለማ ያለው መሆኑን ተረድተናል…." የሚሉ በተለያዩ አህጉራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በግልና በፖለቲካ ድርጅቶቻቸው አማካኝነት ህዝቡ የአማፅያኑን ውጊያ እንዲያወግዝ ጥሪ አቅርበው ነበር፤ ይህን መሠረት በማድረግም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ውጊያውንና አሜሪካ ለአማፅያኑ የምታደርገውን ድጋፍ በጽኑ ተቃውመው ሠላማዊ ሰልፍ ወጡ፡፡ ይህን ያዩት መንግስቱ የተማሪው ወኔ ሳይበርድ በቀጥታ ወደ ስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ጎራ በማለት፤ "በቃላት ማውገዝ ብቻ ሳይሆን ከአብዮታዊ ሠራዊቱ ጎን ተሰልፋችሁ ገንጣይና አስገንጣዮችን መዋጋት አለባችሁ፡፡ እነሱ እዚህ ሰሜን ሸዋ ጅሁር ደርሰው ትምህርት ነው? ሠላማዊ ሠልፍ ነው? ወይስ እንደወያኔ ወጣቶች መዋጋት ነው ያለባችሁ? ተነሱ እንጂ ጎበዝ!" በማለት ቀስቅሰው አብዛኛው ተማሪ ፈቃደኝነቱን ገልጾ ወደማሠልጠኛ ካምፕ ገብቶ ነበር፡፡ ግን ረፍዷል፡፡ በዘረፋ የተሰማሩ አመራሮች ከውጊያው ይልቅ ለሌብነቱ ልዩ ትኩረት



ስለሰጡ፤ በየግንባሩ ሽንፈት፣ በሽንፈቱም ላይ ሌላ ሽንፈት እየተደራረበ ሄደ፡፡ በአጭር አገላለፅ ከ1980 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ በነበሩት ጊዜያቶች የተካሄዱት ጦርነቶች ለአማፅያኑ አሸቻጋሪ የነበሩ መሆናቸው ባይካድም፣ በጣም አስቸጋሪ ግን አልነበሩም፡፡ እንዲያውም በእስር ላይ የሚገኙ የቀድሞው የጦር አዛዦች እንደሚሉት ከሆነ፤ የመጨረሻዎቹ ሦስት ዓመታት አማፅያኑ ከትግራይ አዲስ አበባ ለመድረስ የወሰደባቸው ጊዜ ነው ባይ ናቸው፡፡ ምንም ተባለ ምን ሻዕቢያና ወያኔን የሚያቆማቸው ኃይል አልተገኘም፡፡

ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም መንግስታቸው ከወደቀና እሳቸውም በሽሽት ዙምባቡዌ ከሄዱ በኋላ፤ "እኔ የታገልኩት ከሻዕቢያ ጋር ነው፤ ወያኔ ጎርፍ ያመጣው ድንጋይ ነው" ብለው ተሳልቀዋል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ወያኔ ጎርፍ ያመጣው ድንጋይ አልነበረም፡፡ እርሳቸውም ይሄንን አሳምረው ያውቁታል፡፡ ስለዚህ ለማለት የፈለጉት "ወያኔን ብቻውን ማሸነፍ እችል ነበር፤ ግን ሻዕቢያ ሲያብርለት ሳላሸንፈው ቀረሁ" እንደማለት ነው፡፡

ይህችን የ"ጎርፍ" ምሳሌ ስለሰጡን እያመሰገንን ጎርፉ እንዴት እየተንፎለፎለ የደርግን መንግስት እንደጠራረገው በአጭሩ ለማየት እንሞክር፡፡

በእርግጥም ድርጊቱ በጎርፍ የሚመሰል ነው፡፡ ጎርፉ የመነጨው ከኤርትራ በርሃ ነው፡፡ ገድቦ ለማስቀረት የተሞከረውም እዚያው ነበር፡፡ ሳይሆን ቀረና የናቅፋን ሰንሰለታማ ተራራ አጥለቅልቆ፣ አፋቤትን አዳርሶ ለመረብ ወንዝ ገበረ፡፡

ከዚያ የተነሳው የሕወሓት ጎርፍም ኃይሉን ጨምሮ ያገኘውን ሁሉ እየጠራረገ ሽሬ ደረሠ፡፡ የደርግ ሰራዊት ጎርፉ ሽሬ መድረሱን ሲሰማ ከመጥለቅለቅ አደጋ ራሱን ለማዳን የትግራይን ግዛት በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ለቆ ወጣ፡፡ ማስቀረት እንደማይችል ስለተረዳም ምንም አይነት የመገደብ ሙከራ አላደረገም፡፡ ትግራይን ነፃ ለማውጣት የተነሳው ድርጅት "ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ" ሕወሓት ግቡ የነበረችውን የትግራይ ግዛት ሙሉ በሙሉ ቢያጥለቀልቃትም፤ ጎርፍ ነውና፤ ጎርፍ ደግሞ አንዴ ከላይ ከተነሳ ቁልቁል ከመውረድ በቀር ሌላ ምርጫ የለውምና፤ ወረደ … ጋራ ሸንተረሩን፣ ሜዳ ገደሉን እያዳረሰ አማራ ክልል ሲገባ፤ እዚያም ያገኘውን "ኢህዴን"ን (በኋላ ብዓዴን) ከእነግሳንግሱ ጠራርጎት ቀጠለ፡፡ ከላይ ከሰሜን የተነሳው ጎርፍ እንዲህ በፍጥነት ነጉዶ ነጉዶ በምስራቅ ኢትዮጵያ በሐረርጌና ባሌ፣ በምዕራብ ኢትዮጵያ በወለጋ አካባቢ ረጋ ብሎ ይወዛወዝ ከነበረው ሐይቅ ከኦነግ ጋር ተገናኝቶ ከሩቅ የመጣ ጎርፍና ረግቶ የቆየ ሐይቅ የሚያደርጉትን አይነት የሠላምታ ልውውጥ አደረጉ፡፡ ጎርፉ ከላይ፣ ሐይቁ ከስር ሆነው ወዲያ …. ወዲህ … ሲናጡ የተፈጠረው ማዕበል ፕሬዝዳንት መንግስቱን አሽቀንጥሮ ጣላቸው፡፡ በዚህ መሰሉ ጎርፍ ተገፍትረው ዙምባቡዌ የገቡት መንግስቱም፤

ባሉበት ሆነው ስለጎርፍ ተረቱ፡፡ ተረቱንም ተጠቀምንበት፡፡ ማን በጎርፍ እንደመጣ፣ ማን በጎርፍ እንደወጣ ተረዳንበት፡፡

ከሕወሓት በኋላ በመጨረሻዎቹ ዓመታት ደርግ ላይ ያመፁ ብሐረተኛ ድርጅቶች "ኢህዴን" (ኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ) እና "ኦነግ" (ኦሮሞ ነፃነት ግንባር) ነበሩ፡፡ ስለእነዚህ ድርጅቶች መጠነኛ ቅኝት አድርገን ወደ ተነሳንበት ርዕሰ ጉዳይ እንመለሳለን፡፡

የኦሮሞ ህዝብ የብሔራዊ ማንነት ጥያቄ በተደራጀ መልኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀሰቀሰው "የቱለማና ሜጫ ራስ ገዝ ማኅበር" በጃንሆይ ዘመን በጥር ወር 1955 ዓ.ም ሲመሠረት ነው፡፡ ሆኖም የማኅበሩ ዓላማ የነፃነት ትግል ሳይሆን፤ በኦሮሞ ግዛቶች የትምህርት፣ የጤና፣ የመገናኛና ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮች እንዲገነቡ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ነበር፡፡ በወቅቱ በኦሮሞ ስም ማኅበሩ ይቋቋም እንጂ የአባላቱ ምልመላ የደቡብ ተወላጆችንም ያካተተ ነበር፡፡

የማኅበሩ ፕሬዝዳንት የነበሩት የፖሊስ ሠራዊት አዛዥ ሆነው የተሾሙት ብርጋዴር ጄኔራል ታደሰ ብሩ ስለነበሩ የጃንሆይ መንግስት ስጋት ቢያድርበትም እንቅስቃሴያቸው ሠላማዊ ነው ብሎ በማሰብ ተወት አድርጓቸዋል፡፡ በዚህ መሐል በ1959 ዓ.ም በጥቅምቱ የጃንሆይ የንግስ በዓል ላይ የግድያ ሙከራ ለማድረግ ሲያሴሩ ተገኙ ተብለው ተወነጀሉ፡፡ አስተባብለው ታለፉ፡፡ ብዙም ሳይቆይ በሲኒማ አምፒር ቦምብ ሲፈነዳ የማኅበሩ አባላት ተጠያቂ ሆኑ፡፡ አቀናባሪዎቹ ጄኔራል ታደሠ ብሩና ሌላው አባል መቶ አለቃ ማሞ መዘምር ናቸው በሚል ውንጀላ ማኅበሩ እንዲፈርስ ተደረገ፡፡ ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ የተሰወሩትን ጄኔራል መንግስት አድኖ ይዞ ለፍርድ አቀረበና የሞት ፍርድ አስወሰነባቸው፡፡ ውሣኔው ግን በይግባኝ ወደ እድሜ ልክ ተቀየረ፡፡

ከአብዮቱ በኋላ ጄኔራሉ እንደ ሌሎች የፖለቲከኛ እስረኞች በምህረት ቢለቀቁም፤ ከህቡዕ የኦሮሞ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ስለፈጠሩና፤ ደርግ አካሄዳቸው ስላለማረው "የመሬት አዋጁን በመቃወም" በሚል ክስ በ1967 አስረሸናቸው፡፡በዚያወቅት ይሙት በቃውን የፈረሙት ሊቀመንበሩ ተፈሪ በንቲ ነበሩ፡፡

ቀጥሎ በቀድሞው የሜጫና ቱለማ ማኅበር አባል በነበረ ግለሰብ መስራችነት "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ነፃነት ግንባር" በሚል ስያሜ በ1963 ዓ.ም አካባቢ ተቋቁሞ የነበረው ሲሆን፤ አንዳች ተግባር ሳያከናውንና በአግባቡም መደራጀት ሳይችል በራሱ ጊዜ ተበተነ፡፡

በአብዮቱ ወቅት የፖለቲካ መፈክሩ "ኅብረብሔራዊነት" ላይ ያተኮረ ስለነበር የኦሮሞ ብሔራዊ እንቅስቃሴዎች አልታዩም፡፡ ጥቂት የኦሮሞ ምሁራን በኅብረብሔራዊ ድርጅቶች ውስጥ በተለይም በመኢሶንና በኢጭአት ውስጥ ስለነበሩ ራሳቸውን እንደ ወኪል፣ ህዝቡም እንደተወካይ ካላያቸው በቀር ሌላ እንቅስቃሴ አልነበረም፡፡



ከዚህ አንፃር ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ በኦሮሞ ህዝብ ስም የሚንቀሳቀስ ድርጅት የተገኘው በ1968 ዓ.ም ኦነግ (ኦሮሞ ነፃነት ግንባር) ሲቋቋም ነው፡፡

ኦነግ ከተመሠረተ ጀምሮ ከሻዕቢያ የማቴሪያልና የቴክኒክ ድጋፍ እየተቸረው በሐረርጌ፣ በባሌ፣ በወለጋና በአካባቢው መሸጎ የሽምቅ ውጊያውን ቢቀጥልም፤ በውስጡ በነበረው የእርስ በርስ ሽኩቻና፤ በህዝቡ ውስጥም ራሱን ለማስረፅ የሚያስችል ዘዴ በአግባቡ ባለመቀየሱ የዓመታት ትግሉ የሕወሓትን ያህል ደርግን መፈታተን አላስቻለውም፡፡ ነገር ግን ከተመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ደርግ የፍፃሜ ዘመን ድረስ በደርግ ላይ ካመፁ ብሔረተኛ ድርጅቶች ውስጥ አንዱ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ደርግን ለመጣልም በደቡብ ምዕራብ ያለውን ይዞታውን በማስፋትና ከወያኔ ጦር ጋር ተቀናጅቶ በማጥቃት የድርሻውን ተወጥቷል፡፡ ይህ ድርጅት ከአብዮቱ በኋላ በደርግ ላይ፣ ከደርግ ውድቀት በኋላ በኢህአዴግ ላይ ህቡዕ እንደገባ ዛሬም ድረስ አለ፡፡

ሌላው በ1973 ዓ.ም የተቋቋመው "የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ" (ኢህዴን) ሲሆን፤ ከተበታተነው የኢህአፓ ሠራዊት ተርፈው በሰሜን ወሎ በትጥቅ ትግል ይንቀሳቀሱ የነበሩ ታጋዮች ስብስብ ነው፡፡ ሕወሓት አማራ ክልል ሲደርስ ቅንጅት ፈጥረው አብረው ታግለዋል፡፡ የደርግን ፍፃሜ ለማፋጠን ከፍተኛ መስዋዕትነትም ከፍለዋል፡፡ የአነሳስ መሠረቱ ግን ከስሙም እንደምንረዳው ኅብረብሔራዊ እንጂ፤ ብሔረተኛ አልነበረም፡፡

እንግዲህ ሕወሓት ከትግራይ ግዛት ድል በኋላ ያለው አዝማሚያ ሁሉ ቀላል እንደሆነ ሲረዳና አገራዊ አጀንዳ ማውጣት ግድ ሲሆንበት፤ የዚህ አጀንዳ አስፈፃሚ ይሆናሉ ብሎ ያሰባቸውን ድርጅቶች፤ አነሳሳቸው ብሔረተኝነት ከነበረ እሰየው፤ ኅብረብሔራዊም የሆኑ ካሉ በብሔረተኝነት ማጥመቅ በሚል መነሻ "የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር" (ኢሕአዴግ)ን ወደማዋቀር አመራ፡፡

በዚህ መሠረት ኢህአዴግ የተዋቀረው በተለያዩ ድርጅቶች ጥምረት ሲሆን፤አባል ድርጅቶቹም ሕወሓት፣ ኢህዴን (ከድል በኋላ ብዓዴን ተብሎ የአማራን ህዝብ እንደሚወክል ይፋ ያደረገው)፤የኦሮሞን ህዝብ ይወክላል ተብሎ የተቋቋመው (የኦሮሞ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት) ኦህዴድ፤እንዲሁም የተማሩ የደርግ ሠራዊት መኮንኖች የተሰባሰቡበት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ(ኢዴመአን)ነበሩ፡፡

በእነዚህ በኢህአዴግ ስር ከተካተቱ ድርጅቶች ውስጥ ሕወሓትና ኦህዴድ በብሔረሰብ ላይ የተዋቀሩ ሲሆኑ፤(የመጀመሪያው በትግራይ፣ ሁለተኛው በኦሮሞ)ኢህዴንና ኢዴመአን ኅብረብሔራዊ ናቸው፡፡

ከማይታወቀው ኦህዴድ ይልቅ የሚታወቀው ኦነግ በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዳለው ቢታወቅም፤ ከኦነግ ጋር ከድል በኋላ ግንባር ለመፍጠር ሳይቻል ስለቀረ ሕወሓት ኦህዴድን ለማቋቋም ተገደደ፡፡ ስለዚህ ከኦነግ የጦር ምርኮኞችና በኦነግ ካልታቀፉ ምሁራን የተውጣጡ አባላትን መልምሎ

አቋቋመ፡፡ ኢህዴንም ከድል በኋላ ብዓዴን ነኝ ይበል እንጂ በአማራ ክልል ውስጥ ሲታገል በነበረበት ጊዜ የሚታወቅበት ስም ኢህዴን የሚለው ነበር፡፡

በመኮንኖቹ ስም የተቋቋመው ኢዴመአን የጦር ምርኮኞችን በፖለቲካ መድረክ ዙሪያ ከማሰባሰብ ያለፈ የፖለቲካ ሚና ሳይኖረው የከሰመ ነው፡፡

እነዚህን የድርጅት አነሳሶችና አወቃቀሮችን ከወዲሁ ቀድሞ መግለፅ ያስፈለገው፣ ኢህአዴግ ኢህአዴግነቱን ያወጀውና በዚህ ስምም እየተጠራ ትግሉን የቀጠለው የትግራይን ግዛት በቁጥጥሩ ስር ካደረገ በኋላ፣ እዚያው ትግራይ ላይ ቅድመ የቤት ስራውን አጠናቆ ለአዲሱ ኢህአዴጋዊ አጀንዳ ኢህአዴጋዊ ትግሉን ቀጥሎ እየተጠራበት መምጣቱን ለማስገንዘብና፣ አዲስ አባባንም የተቆጣጠረው በዚሁ ስሙ መሆኑን ከወዲሁ ለመጠቆም ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜም ብዓዴን፣ ኦህዴድ፣ ሕወሓት፣ ከድል በኋላ የተቋቋመው የደቡብ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደህዴን) እና ሌሎች አጋር ድርጅቶች ተጣምረው የሚገኙበት "ኢህአዴግ" መንግስት ሆኖ አገር እየመራ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ይህ በግልፅ የመታወቁን ያህልም በ1993ዓ.ም በውስጡ ካጋጠመው ክፍፍል ውጭ እንደ ድርጅትም የበላይነቱ እንደተጠበቀ ነው፡፡በግለሰብ መሪዎች ደረጃም እንደዚያው፡፡

እናም ኢህአዴግ ትግሉን ቀጠለ፡፡ የደርግ መንግስት የብሔረተኞችን ጦርነት መቋቋም እየተሳነው ሄደ፡፡

የደርግ መንግስት ውድቀት እጅግ በተፋጠነ መንገድ የቀጠለው ከ1980 ጀምሮ ነው፡፡ እስከ 1983 ድረስ ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሞ ለመፋለም ከመሞከሩም ባሻገር፣በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ አዳዲስ ምልምሎችን በውድም በግድም በፍጥነት ወደተገነቡ የማሰልጠኛ ጣቢያዎች እያጋዘ በለብለብ ስልጠና ወደ ጦር ግንባር ቢያሰማራም፣ የጠበቀውን ውጤት ሊያገኝ አልቻለም፡፡

በተለይ በየካቲት ወር 1982 ዓ.ም ሻዕቢያ ከፍተኛ እልቂት በታየበት ጦርነት የደርግን የባህር ኃይል ደምስሶ ምፅዋን ሲቆጣጠር መንግስት የባህር ወደቡን ከማጣቱም ሌላ፣ ትግራይ ሙሉ በሙሉ በሕወሓት እጅ ስለነበረች ኤርትራ ውሰጥ ለሚገኘው ጦር ስንቅ የማቅረቢያ መንገድ አጣ፡፡

በዚህ መሀል ኢሕአዴግ ወደ አዲስ አበባ የሚያረማምዱትን ተከታታይ ዘመቻዎች ከፈተ፡፡ በ1982 ዓ.ም የመጀመሪያ ወራት የጎንደር ክፍለሀገርን ለመቆጣጠር የከፈተው ዘመቻ ለጊዜው ቢከሽፍበትም "ጉና" በተባለው ተራራ ላይ በተደረገ ጦርነት በብዙ የህይወት መስዋዕትነት ደብረታቦርን ተቆጣጠረ፡፡ ቀጥሎም ደቡብ ወሎ ውስጥ "መራኛ" በተባለው ስፍራ ባገኘው ወሣኝ ድል ወደ ሰሜን ሸዋ ለመረማመድ ቻለ፡፡



እነዚህን ድሎች ከተቀዳጀ በኋላ ኢ.ሕአዴግ አዲስ አበባን ለመቆጣጠር ወኔ በሚቀሰቅሱ ታሪካዊ ስሞች የሰየማቸውን የጦር ዘመቻዎች አወጀ፡፡

በ"ዘመቻ ቴዎድሮስ" ጎጃምን ተቆጣጠረ፡፡ በቀድሞው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ መሪ አንቀሳቃሽ በነበረውና የወሎ ተወላጅ በሆነው በዋለልኝ መኮንን ስም "ዘመቻ ዋለልኝ" ብሎ በሰየመው ዘመቻ የደርግን ሠራዊት ከወሎ ክፍለሀገር ጠራርጎ አስወጣ፡፡ ቀጥሎ "ዘመቻ ቤሉሱማፍ ወልቂጡማ" (በኦሮምኛ ነፃነትና እኩልነት ማለት ነው) በሚል ስያሜ ባዘመተው ጦር ከጎጃም ወደ ወለጋ መሸጋገር ቻለ፡፡

እነዚህን የመሳሰሉ ወሣኝ ድሎች በፍጥነትና በተከታታይ እየተቀዳጀ መጥቶ የኢህአዴግ ሠራዊት አዲስ አበባን ከሰሜን፣ ከምስራቅና ከምዕራብ አቅጣጫ ከበባት፡፡ የደርግ ሠራዊት በብዙ ግንባሮች ጠንክሮ ለመከላከል ሞከረ፡፡ በተለይ አምቦ ከተማ ላይ የነበረው ሠራዊትና ህዝቡ የኢህአዴግን ጦር አላሳልፍ ብሎ ከፉኛ ተፈታትኖት ነበር፡፡ የደርግ መንግስት ከጽኑ የመከላከል ተግባሩ ጎን ለጎን ከ1970ዎቹ ጀምሮ ዞር ብሎ አይቶት የማያውቀውን፣ በተቀናቃኞቹ ዘንድም ተቀባይነት ያልነበረውን የሠላም አማራጭ ማማተር የጀመረው ሁኔታው እዚህ ደረጃ በደረሰበት ጊዜ ነበር፡፡

እነዚህ ግንባር የፈጠሩ ብሔተኞች አፍሪካ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ የረጅም ዓመታት የሽምቅ ውጊያ ግዙፉን የደርግ ሠራዊት ደረማምሰው፣ እዚህ ደረጃ ደርሰው፣ ሙሉ ለሙሉም ወታደራዊ ድልን ከተጎናፀፉ በኋላ የሠላም ድርድርን ይፈልጋሉ፣ ይቀበላሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት መሆኑ ቢታወቅም፣ በተለይ አፍቃሬ ኢሕአዴግ የነበረችው አሜሪካ የመጀመሪያዋ አደራዳሪ መስላ ለመታየት ሞከረች፡፡ በዚህ መሠረት የመጀመሪያው የሠላም ድርድር በቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት በጂሚ ካርተር አማካኝነት በ1982 ዓ.ም መጀመሪያ በአትላንታ፣ ቀጥሎ በናይሮቢ የሠላም ድርድሮች ተካሄዱ፡፡ ይህም በሻዕቢያና በደርግ መንግስት መካከል የተካሄደ ነው፡፡ በምን እንደሚደራደሩ ግን ሻዕቢያም፣ ደርግም፣ አደራዳሪው ቡድንም ቢጠየቁ መልስ የላቸውም፣ ሊኖራቸውም አይችልም፡፡ ስለዚህ ለደንቡ ያህል ጥቂት ተጨቃጭቀው ሳይግባቡ ተለያዩ፡፡

ቀጥሎ በመጋቢት 1982 በደርግና በሕወሓት መካከል ሮም ላይ በቀድሞው የኢጣሊያ አምባሳደር ሸምጋይነት የተደረገው የሠላም ድርድር ሲሆን፣ ሕወሓት "ሌሎች የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችም መሳተፍ አለባቸው" የሚል መከራከሪያ በማንሳቱ፣ ቀድሞ የከሸፈው ድርድር ውጤት አልባ ሆኖ ተበተነ፡፡

ሦስተኛውና የመጨረሻው አስገራሚ የሠላም ድርድር ለንደን ላይ በደርግና በኢሕአዴግ መካከል የተካሄደው ነው፡፡ በ1983 ዓ.ም በግንቦት ወር የመጀመሪያ ቀናቶች "የለንደን ጉባዔ" ተብሎ በሚታወቀውና በአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና የአፍሪካ ጉዳዮች ኃላፊ በነበሩት በሄርማን ኮኸን ሰብሳቢነት የተደረገው ሙከራ ላይ የኢትዮጵያ መንግስትን ልዑክ መርተው የሄዱት ባለቀ ሰዓት ሹመት የተሰጣቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ተስፋዬ ዲንቃ ነበሩ፡፡ የመደራደሪያ አቅም ቀርቶ የማምለጫ መንገድ ባልነበራቸው ሁኔታ ለሰላም ድርድር መሰብሰባቸው ሳያንስ፤ ጉባኤው እየተካሄደ ባለበት ሰዓት ፕሬዝዳንት መንግስቱ አገር ጥለው መሄዳቸው ተሰማ፡፡

ጂሚ ካርተርና ሄርማን ኮኸን ወደ አዲስ አበባ በተደጋጋሚ መጥተው ከመንግስቱ ጋር ውይይቶችን አድርገው ጨርሰዋል፡፡

ስለዚህ ቀጣዩን ሂደት በደንብ ያውቁት ነበር፡፡ በተለይ ሚስተር ኮኸን ለንደን ላይ አደራዳሪ ሆነው ተቀምጠው በነበረበት ጊዜ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም ግንቦት 13 ከአገር መውጣታቸውን ግንቦት 14 ጉባዔው ላይ ሲሰሙ የመገረም ፊት ያሳዩት ሲቀልዱ እንጂ ከልባቸው አልነበረም፡፡

መጨረሻው ደረሰና ግንቦት 16 ቀን 1983 ዓ.ም ሻዕቢያ የዓመታት ዒላማው የነበረችውን አስመራን ሙሉ ለሙሉ በእጁ አደረጋት፡፡ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ማለዳ ላይ የኢህአዴግ ሠራዊት አዲስ አበባን ተቆጣጠረ፡፡ በእለቱ የመንግስቱና የቤተመንግስቱ ታማኝ ጠባቂዎች ከድል አድራጊው ወገን ጋር ካደረጉት መጠነኛ የተኩስ ልውውጥ በስተቀር የተፈጠረ ሁከት አልነበረም፡፡

ኤርትራ ውስጥ ይገኝ የነበረው ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት ከፊሉ ወደ ሱዳን፣ ከፊሉ ወደ ትግራይ ተበተነ፡፡ በአስመራና በአካባቢዋ የሚገኘው ጦርም ትጥቁን እየፈታ ለሻዕቢያ እጁን ሰጠ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አዲስ አበባ ውስጥ የነበሩ የመንግስት ከፍተኛ የጦር ባለሥልጣናት ምንም አይነት አውሮፕላን ከአዲስ አበባ እንዳይነሳና ሁሉም ባለበት እንዲረጋ ኢህአዴግ የሰጠው ማስጠንቀቂያ እንዳለ ሆኖ፤ በልዩ ልዩ ዘዴ ከአዲስ አበባ ወጥተው ለማምለጥ የሞከሩትን ባለሥልጣናት ግን የራሳቸው ባልደረባ የነበሩት የደህንነት ሚኒስትሩ አከሽፉባቸው፡፡ ከግንቦት 20 በፊት ከነበሩት ጥቂት ቀናቶች ጀምሮ የአዲስ አበባን መውጫና መግቢያ በአራቱም አቅጣጫ ጠባቂ መድበው የደርግ ባለሥልጣኖችን የማምለጥ ሙከራ በመግታታቸውም፤ ኤምባሲ ውስጥ ገብተው ከተጠጉትና በረቀቀ ዘዴ ማምለጥ ከቻሉት በጣት የሚቆጠሩ ባለሥልጣናት ውጪ ሁሉም እየተለቀሙ ተይዘው ወደ ወህኒ ወረዱ፡፡ ከረጅም ዓመታት የፍርድ ሂደት



በኋላም የሞት፣ የእድሜ ልክና ከ5 እስከ 20 ዓመት የሚደርስ የእስር ቅጣት ተወሰነባቸው፡፡

ኢህአዴግ ሙሉ በሙሉ አገሪቱን ያዘት፡፡የሻዕቢያና የኢህአዴግ የተባበረ የረጅም ዓመት ውጊያቸው በድል በተጠናቀቀ ማግስትም በ1984ዓ.ም ኤርትራ በሪፈረንደም ተገንጥላና ነጻ አገር ሆና የራሷን መንግስት መሰረተች። ኢትዮጵያም ሁለት አገር ሆነች፡፡ከ7ዓመት በኋላም በኢሳያስ የሚመራው የሻዕቢያ መንግስት በ1990ዓ.ም የድንበር ትንኮሳ አድርጎ አንድ የነበሩ ሁለት አገሮች ወደ ጦርነት አምርተው በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የኢትዮጵያና የኤርትራ ወጣቶች በጦርነቱ ሊያልቁ ግድ ሆነ፡፡እነዚህ ሁለት መንግስታት ዛሬም ድረስ በክፉ ዓይን የሚተያዩ ሆነዋል፡፡

ከደርግ ውድቀት በኋላ የኢትዮጵያ የቀድሞው ሕገመንግስት ተሽሮ ኢህአዴግ የራሱን ሕገመንግስት በ1987ዓ.ምአፅድቆ በብሔር ተኮር ፌዴራሊዝም አገሪቱን እየመራ ይገኛል፡፡

ድል አድራጊው የኢህአዴግ መንግስት ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ይህ መጽሐፍ ለሕትመት እስከበቃበት 2004 ዓ.ም ድረስ ኢትዮጵያን እያስተዳደረ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ከ4 ዓመታት በኋላ የ25ኛ ዓመት የብር ኢዮቤልዩ በዓሉን ያከበራል ማለት ነው፡፡

ወደጓድ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ሽሽት እናመራለን፡፡

የመጨረሻዎቹ ቀናት

ፕሬዝዳንት መንግስቱ ብዙ ጣሩ፣ ብዙ ዋተቱ፣ የቻሉትን ሁሉ ሞከሩ፡፡ ግን አቃታቸው፡፡ ሁሉም ፊቱን አዞረባቸው፡፡ የጦር አዛዦች አንጓጠጧቸው፣ ከዷቸው፡፡ ሚያዚያ ወር ላይ ክፉኛ ተስፋ ቆርጠው ነበር የታዩት፡፡ እናም ለመጨረሻ ጊዜ ከህዝባቸው ጋር ማውራት ፈለጉ፡፡ ሚያዚያ 11 ቀን 1983 ዓ.ም ሁሉም መስሪያ ቤቶች ተዘግተው ህዝቡ በየቤቱ ተቀምጦ የፕሬዝዳንቱን ንግግር በብዙሃን መገናኛዎች እንዲያደምጥ ተደረገና ጓድ መንግስቱ ግማሽ ቀን የፈጀ ንግግራቸውን አሰሙ፡፡ ልብ በሚነካ አገላለፅ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነቱን፣ ሉዓላዊነቱንና ነፃነቱን ለማጠንከር ያደረገውን መስዋዕትነት እያመሰገኑ፣ የጦሩን አሰላለፍና የጠላትን ግስጋሴ እየጠቆሙ፣ የአብዮቱን ፍሬዎች እየዘረዘሩ፣ ብርቱ የመከላከያ ኃይል ለመገንባት የተደረገውን ጥረት እያብራሩ ቀጠሉና፤ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚቃጣበትን ማንኛውንም አይነት አፍራሽ ተግባር በውል እንዲመረምርና ማድረግ ያለበትን ነገር መወሰን እንደሚገባው አስገነዘቡ፡፡ ገለፃቸውን ሲደመድሙም "... በዚህ ገለፃዬ ውስጥ እንዲህ ይሁን፣ እንዲህ ይደረግ፣ የሚል ጥቆማና መሪ ሀሳብ ለማቅረብ አልፈለግሁም፡፡ ነገር ግን የመላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ግልፅ

አቋምና ፈጣን ውሣኔ እጠይቃለሁ፡፡" ካሉ በኋላ የብሔራዊ ሸንጎውን አስቸኳይና ልዩ ስብሰባ የጠሩ መሆናቸውን ለህዝቡ አሳውቀው ወደ ትካዜያቸው ተመለሱ፡፡ ከንግግራቸው ውስጥ "ለኢትዮጵያ አንድነት የሚበጅ እስከሆነ ድረስ ስልጣን ይዞ የመቆየት ፍላጎትና ጉጉት የለኝም" የሚል ዓረፍተነገር ስለተካተተበት አዳማጩ ህዝብ "በቃ ስልጣን ሊለቁ ነው" የሚል ግመት ወስዶ ነበር፡፡ ግን አላሉም፡፡

መንግስቱ ሳያውቁት የጃንሆይን የመጨረሻ ትንቢት ፈፀሙት ማለት ነው፡፡ ጃንሆይ "ለአገር የሚጠቅም ነገር እስካለበትና፤ ህዝቡም የእኛን መወገድ ከፈለገ ..." ብለው ነበር፡፡ ሲቀጥሉም፤ "እናንተ ካልቻላችሁ ደግሞ የእናንተ ታሪክ እዚያ ላይ ይቆምና የእኛ ይቀጥላል...." ማለታቸውን አይተናል፡፡ አዎ፤ ሶሻሊዝም ቆሞ የጃንሆዩ ዘመን የአሜሪካ ካፒታሊዝም ቀጠለ...፡፡ ሚያዚያ 14 ቀን "ልዩ" የተባለው 3ኛው የብሔራዊ ሸንጎ ጉባዔ ተካሄደ፡፡ በጉባዔው አዳራሽ ግን የሸንጎው አባላት ብቻ አልነበሩም የታደሙት፡፡ ከተራ ሰው ጀምሮ እስከ ባሥልጣናት ድረስ ከ3ሺ በላይ ዜጎች ታድመው አዳራሹ ሞልቶ ቆመው የታደሙ ሁሉ ነበሩ፡፡ ስርዓት፣ ደንብ፣ ትዕዛዝ፣ መሪ፣ ተመሪ ብሎ ነገር በዚያ ሰዓት ፋሽኑ ያለፈ ከመሆኑም በላይ፤ የመንግስቱ ተፈሪነት ራሱ ቀርቶ እኩል የሚመላለሱት በርክተዋል፡፡

ይሄንን ጉዳይ መንግስቱ በትዝታቸው ገልፀውታል፤ "አንድ ሰው ቀና ብሎ አይቶኝ አያውቅም ነበር፡፡ 17 ዓመት ሙሉ! በዚያ በመጨረሻው ሸንጎ ብቻ ተደፈርኩ፤ እነ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ሲፎልሉብኝ" ብለዋል፡፡

የሸንጎው ዓላማ በኢኮኖሚያዊና በወታደራዊ ጉዳዮች ላይ ተወያየቶ አስቸኳይ ህዝባዊ ውሣኔ ማሳለፍ የነበረ ቢሆንም፤ የፕሬዝዳንቱ 3 ሰዓት የፈጀ ንግግር ግን "ኧረ ጎበዝ ምን ይሻላል?" የሚል ሆኖ የሚጠቃለል ነው፡፡ "... ጠላት ሊቦጫጭቀን አሰፍስፎ ከበራችን ላይ ቆሟል፡፡ አሁን ችግሩ የአገር አንድነት ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዳችንን ህልውና ፈተና ላይ የጣለ ሆኗል፡፡ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ውይይት አድርገን የመፍትሄ ሀሳብ በጋራ ማመንጨት አለብን" በሚል የውይይት መድረኩን ከከፈቱ በኋላ ለ3 ተከታታይ ቀናት ውይይቱ ቀጠለ ፡፡

"ሠላማዊ መፍትሄ እየተፈለገ፤ ጎን ለጎን ደግሞ ለአንድነታችን ጠንክረን እንዋጋ" የሚለውና "የእርስ በርሱ ጦርነት የሚቆምበት ሠላማዊ መፍትሄ ይፈለግ" የሚለው ሀሳብ ተደጋግሞ ከታዳሚው ተሰነዘረ፡፡ እንዴት? ቢባል ግን መልስ የለም፡፡ ብቻ ግን ተሰብሳቢው እየተነሳ ያሻውን ማለት ጀመረ፡፡ እያንዳንዱ ሀሳብ ፕሬዝዳንቱን የሚያስከፋ ነበርና አዘኑ፡፡



አንድ ጄኔራል ተነሱና "ለምን የተኩስ አቁም ስምምነት አናደርግም? አሉ፡፡ ከአንድ የጦር ጄኔራል ይሄ ቃል መውጣቱ ያሳዘናቸው መንግስቱ "ይሄ ባንተ በመነገሩ አዝኛለሁ" አሉ፡፡

የባህር ኃይል አዛቹ ደግሞ "ህዝብ ካልፈለገን ለምን ስልጣን አንለቅም? ህዝብ እስከፈለገን ድረስ በቻ ነው በሥልጣን መቆየት ያለብን" ሲሉ፤ ከባህር ኃይል አዛዥነታቸው በላይ የኢሠፓና የብሔራዊ ሸንጎው አባልም ስለነበሩ መንግስቱ በመከፋት "እኛም እንዲህ እንላለን እንዴ?" በሚል ቅሬታቸውን በፊታቸው ጭምር አሳዩ፡፡

ኮሎኔል ፍስሃ ደስታ ቀጠሉ፡፡ በግዕዝ የተናገሩት ንግግር ወይም የሰጡት ሀሳብ "የፈላ ውሃና ቀዝቃዛ ውሃ ቀርበልሃል፤ ወደመረጥከው እጅህን ንከረው" የሚል ነው፡፡ ፕሬዝዳንቱ ቅስማቸው ቢሰበርም ጉባዔው ግን ቀጠለ፡፡ ከመንግስቱ እጠገብ የተቀመጡት ዶ/ር አበበ ዓለሙ ቀጠሉ፤ "የኢትዮጵያ ህዝብ ልጇን አጥባ፣ አጣቢውንም፣ ልጇንም ወደ ደጅ እንደምትደፋ ሰነፍ ሴት የሚሆን አይመስለኝም፡፡ ህዝቡ እኛን ከጠላ ሀገሩን ከእኛ ጋር ሊደፋት አይገባውም" በሚል "ስልጣን እንልቀቅ" አሉ፡፡ ተጨበጨበ፡፡

ተከታዩን ታሪካዊ ንግግር ያደረጉት አቶ አብርሃም ያዬህ የነበሩ ሲሆን፤ በቁጥር 2ቱ ነበር መጽሐፍ ገጽ 356 የተካተተው ገለፃቸው እንዲህ ይነበባል፤ "... እኔና ገብረመድህን በሬዲዮና በቴሌቪዥን ያን ሁሉ የለፈለፍነው መንግስቱ ኃይለማርያምን፣ ለገሠ አስፋውንና ተስፋዬ ወልደስላሴን ከውድቀታቸው ለማዳን አልነበረም፡፡ እነሱ ቢወድቁ ባይወድቁ የእኛ አጀንዳ አልነበረም፡፡ እንደፈቀዳቸው ይሁኑ፡፡ የእኛ ዋና አጀንዳ የኢትዮጵያ ህዝብ ሐቁን አውቆ የወያኔን ማንነትና ምንነት ተገንዝቦ ሴራውን ለማክሸፍ እንዲታገል ማንቃት ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን አልተገነዘበልንም፡፡ በወያኔ ጭብጥ ውስጥ ሲገባ ግን አብርሃምና ገብረመድህን የተናገሩት ለካ ይኸ ኖሯል? ብሎ በቁጭት ያስታውሰናል፡፡ ያኔ እሣት ሆኖ ያንገበግበዋል፡፡

አሁንም ስለአገራችን ስለኢትዮጵያ ብዬ እናገራለሁ፤ የእሷ ነገር ያሳስበኛል፤ ያሳዝነኛልም፡፡ ይህ የመጨረሻ ቃሌ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የምናገርበት መድረክ እንደሌለ አውቃለሁ፡፡ ሁሉም ነገር አብቅቷል፡፡ ወያኔ መምጣቱን ልንገራችሁ፡፡ ኤርትራን ያስገነጥላል፣ መሬት ቆርሶ ለሱዳን ይሸጣል፡፡ ይህን ልታውቁት ይገባል፡፡ ዛሬ የተናገርኩት የመጨረሻ ኑዛዜዬን ነው፡፡ ከአሁን በኋላ አንገናኝም፡፡ እኔ መሄጃ አለኝ፤ እሄዳለሁ፡፡፡ እያንዳንዳችሁ ግን ስለአገራችሁም፤ ስለራሳችሁም አስቡ..." በማለት ሲናገሩ አዳራሹ በፀጥታና በተመስጦ ነበር ያደመጣቸው፡፡

ቀጥሎ የላስታ አውራጃ እንደራሴ የሆኑት ቄስ? መነኩሴ? ተነሱና ".... መቼም ይሄ የመጨረሻችን ነው፤ ከዚህ በኋላ አንገናኝም፡፡ ስለዚህ

የተሰማኝን ልተንፍስ...” አሉና ቀጠሉ “... እነዚህ ሰዎች (ኢህአዴጎች) እየታገልን ነው የሚሉት ሰፊውን ህዝብ ከጭቆና ለማውጣት በሚል ነው፡፡ ሌሎችም እንዲያ ይላሉ፡፡ እናንተም ወደ ስልጣን ስትመጡ እንዲህ ብላችሁ ነበር፡፡ ወንበራቱን ካገኛችሁ በኋላ ግን ህዝቡ ተረሣ፡፡ እነዚህም ከጫካ መጥተው እርስዎ የተቀመጡባት ወንበር ላይ ሲቀመጡ ይህን ሰፊ የሚሉትን መከረኛ ሕዝብ ይረሱታል፡፡ እርስዎ ግን እዚችው ወንበር ላይ እንደተጣበቁ እንደ ቴዎድሮስ ሽጉጥዎን ጠጥተው እንደሚያልፉ እተማመንብዎታለሁ!” አሉ፡፡ የእኒህ ሰው ትንቢት ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም በከፊል ግን ተፈጽሟል፡፡ መንግስቱ ሽጉጥ አልጠጡምና፡፡

በዚህ ንግግር መንግስቱ ሣቁ፡፡ በዚህ መልኩ ቀጥሎ ብዙ ብዙ ሀሳቦች፣ ሾርኒዎች፣ ዘለፋዎች፣ ተስፋ አስቆራጭ ትንበያዎች ሲንሸራሸሩ ከቆዩ በኋላ የፕሬዝዳንቱ የማጠቃለያ ሀሳብ፤ “... ደም እንደ ጎርፍ ይፈሳል፣ ህንፃዎች ይደረመሳሉ፣ ከዚህ በኋላ የሚሆነው ይሆናል...” የሚል ይዘት ያለው ሆኖ ቢጠናቀቅም ጉባዔው ከላይ እስከ ታች በሚወርድ ትዕዛዝ ተፈፃሚ የሚሆን ውሣኔ አሳልፎ ነበር፡፡ ውሣኔዎቹም ውይይት፣ ድርድር፣ የሠላም ኮሚሽን፣ ህዝባዊ የሆነ የክተት አዋጅ ... ወዘተ እንዲደረግ የሚያሳስቡ ቢሆኑም በአገር ውስጥም በውጭም ድጋፍ ቢቸረውም ረፍዷልና ሊተገበር አልቻለም፡፡ መንግስቱ የመጨረሻ ጊዜያቸው እንደደረሰ ስለተረዱም የመልሶ ማጥቃት ዝርዝር እቅዶችን ማውጣትና ጦሩን እየተዟዟሩ “በርቱ!” ማለታቸውን እርግፍ አድርገው ትተው በትካዜ ተዋጡ፡፡ ሚያዚያ 18 ቀን ባለቀለት ወንበር ላይ ሹመት ሰጡ፡፡ በዚህም ሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን የኢህድሪ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ አቶ ተስፋዬ ዲንቃ ጠቅላይ ሚኒስትር፤ እንዲሁም ለሌሎች ተመሣሣይ ሹመት ከሰጡ በኋላ ሻምበል ለገሠ አስፋውንና ኮሎኔል ፍስሐ ደስታን በጡረታ አሰናበቱ፡፡

ሚያዚያ 19 “የአሜሪኪ መንግስትና ህዝብ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ፀንቶ መኖር ያላቸውን ጽኑ አቋም በድጋሚ በማረጋገጥ የአሜሪካ መንግስት የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ ሸንጎ 3ኛ አስቸኳይ ጉባዔ ያሳለፈውን ውሣኔ የሚደግፍ መሆኑንና ለተግባራዊነቱም አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚሰጥ ያረጋግጣል...” የሚል መልዕክት ለፕሬዝዳንት መንግስቱ ደረሳቸው፡፡

ጉባዔው ያሳለፋቸው ዝርዝር ውሣኔዎች “አንድነት የፀናባት ኢትዮጵያን” ከማስቀጠል ጋር እንጂ ከመገንጠል ጋር ፈጽሞ የሚስማማ አልነበረምና አዲስ አበባን ከበው የያዟት ተቃዋሚዎች የሚስማሙበት አልሆነም፡፡

ሆኖም የአሜሪካን የይምሰል መግለጫ ተከትለው ሩሲያ፣ ቻይና፣ ካናዳ፣ ግብፅና ሌሎች አገራት የሸንጎውን ውሣኔ መደገፋቸውን ገለፁ፡፡



ኢትዮጵያውያኑም በሠላማዊ ሰልፍ ድጋፋቸውን አረጋግጠው፤ አማፅያኑን የሚደግፉትን አገራትም አወገዙ፡፡

በዝምታ ቀናቶችን አሳልፎ የቆየው ኢህአዴግ በውጭ ቢሮ ጽ/ቤቱ በኩል ተከታዩን መግለጫ ይፋ ሲያደርግ የሸንጎው ውሣኔም ሆነ ማናቸውም ዓይነት የሠላም ድርድሮች ሁሉ ከንቱነታቸው ግልፅ እየሆነ ሄደ፡፡

“ከኢህአዴግ የውጭ ቢሮ ጽ/ቤት የተሰጠ መግለጫ፡፡

“የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከግንቦት 2 እስከ 4 ቀን 1983 ዓ.ም በነፃ መሬታችን ላይ አስቸኳይ ስብሰባ አካሂዶ ወቅታዊ ጉዳዮችን በሚመለከትና አስፈላጊ ውሣኔዎችን በማሳለፍ ተጠናቋል፡፡

አስቸኳይ ስብሰባው በአሁኑ ወቅት ደርግ፣ ኢሠፓና መሰሎቹ በአንድነት በመሰባሰብ የኢህአዴግ የሽግግር ፕሮግራም ተግባራዊ እንዳይሆን የተጠነሰሰ ሴራ በሚመለከት ሆኖ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ደርግ ያወጀው የሽግግር መንግስት፣ ኢህአዴግንና ሌሎች ታጋይ ኃይሎችን በፀረ አንድነት ስያሜ በማግለል ደርግና የትምክህተኞች ኃይል ስብስብ ኢ.ዲ.ኀ.ቅ እና ሌሎችም ስልጣን ለመያዝ በአሜሪካ ኤምፔሪያሊዝም አይዞህ ባይነት በተለያዩ የውጭ አገር ከተሞች ሽር ጉድ እያሉ ይገኛሉ፡፡

የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ የደርግ ሸንጎ ያሳለፈውን የሠላም ውሣኔ አልተቀበለውም፡፡ ኢህአዴግ በስመ አንድነት ወይም በወረራ የተመሠረተ የባርነትና የግዛት አንድነት የህዝብ አንድነት ይሁን ብሎ ለመከራና ለጭቆና አሳልፎ አይሰጥም፡፡ ማንኛውም ብሔርና ብሔረሰብ የራሱን ዕድል በራሱ በመወሰን ነፃ መንግስት መስርቶ ባስፈለገው መንገድ እንዲጓዝ ይበልጥ ኢህአዴግ ሲታገልለት የቆዬ ዴሞክራሲያዊ መንገድ ከመቼውም ጊዜ በላይ ፍቱን መፍትሄ መሆኑን አስምሮበታል፡፡ በኤርትራና በኢትዮጵያ ለ30 ዓመታት ሲካሄድ የቆየውን ጦርነት በተመለከተ ማንም ወሣኝ ሳይሆን የኤርትራ ቅኝ ግዛት ጥያቄ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እልባት አግኝቶ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ ቅኝ አገዛዝ ቀንበር ተላቅቀው ነፃ አገራቸውን እንዲመሠርቱ ሁሉ ኢትዮጵያዊ አምኖበት መቀበል አለበት፡፡ ኢህአዴግ ያቀረበው አስተማማኝና አጥጋቢ መፍትሄ፣ ግልፅና ጠቃሚ ነው፡፡ ኢትዮጵያ አትቆራረስም ብሎ መጮህ ትርፉ ጦርነትና እልቂት ስለሆነ አንድነት ለብዝበዛና ለባርነት አሳልፎ የሚሰጥ መሣሪያ ከመሆኑ ባሻገር የህዝቡን ጥቅም ሊያስጠብቅ አይችልም፡፡ በዚህ ላይ ኢህአዴግ የሽግግር ፕሮግራም ብዙ የፖለቲካ ኃይሎች በነፃና ዴሞክራሲ የሚሳተፉበት፣ ህዝቡ በየድርጅቱ መሪነት እድሉን በራሱ ወደሚወስንበት መድረክ የሚያሸጋግር ፕሮግራም መሆኑን በድጋሚ አረጋግጧል፡፡

አስቸኳይ ስብሰባው በቅርቡ በአሜሪካ መንግስት አቀራራቢነት በደርግ፣ በኢህአዴግ፣ በኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባርና በህዝባዊ ግንባር ኀርነት ኤርትራ መካከል ለንደን ውስጥ ሊካሄድ የታቀደውን የሠላም ኮንፍረንስ የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በጥልቀት መርምሮ መሳተፍ ተገቢ ሆኖ ቢያገኘውም፤ በዚሁ የለንደኑ ኮንፈራንስ አቀራራቢ የሆኑት መንግስታትና ደርግም ሆነ ቀኞችና ወላዋይ ድርጅቶች ለኢህአዴግ ሠላማዊ ሽግግር ፕሮግራም ያላቸውን ጠማማ አመለካከት አስወግደው የሽግግር ፕሮግራሙን ሲቀበሉ ብቻ ነው፡፡ ይህ የኢህአዴግ የሽግግር ፕሮግራም ታማኙን በልዩ ልዩ መንገድ ያረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ለህዝቡ የሚበጁ መፍትሂዎች ከዚህ የበለጠ ሌላ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚገባ አምኖበታል፡፡

ኢሠፓና መሰሎቹ ያቀረቡት የሽግግር ፕሮግራም የህዝብን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት በፍፁም የሚፃረር፣ በይዘቱም ለህዝቡ የማይበጅ ፀረ ህዝብ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የለንደኑን ኮንፍረንስ የኢህአዴግ ዓላማ በተግባራዊነቱ ታምኖበት ተቀባይነቱ ካልተረጋገጠ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አጥብቆ ለማሳሰብ የሚወደው ነገር ቢኖር፤ የምንወስደው ሰፊ ወታደራዊ ማጥቃት በአገሪቱ የሚፈጥረው የእርስ በርስ እልቂት ታይቶ ከማያውቅ ደረጃ ይደርሳል፡፡ የኢህአዴግ ዓላማ ተግባራዊነቱን የሚያገኘው በጦርነቱ ስለሆነ ጦርነቱ በከፋ መልኩ ይቀጥላል፡፡ የአገሪቱ ህዝብ የስቃይና የመከራ ህይወት ይራዘማል፡፡ በፀረ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች የኢህአዴግ ሠንደቅ ይውለበለባል፡፡

ይህ የጦርነት ክስተት እንዳይፈጠር የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጦርነቱን ለማቆም ዋነኛው አማራጭ መንገድ የኢህአዴግ ሠላማዊ ሽግግር ፕሮግራም በውጭና በሃገር ውስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያን እንዲቀበሉት ሲያስገነዝብ፤የኢትዮጵያ ህዝብ ከዚህ የጦርነት ኀሳት ለመዳን የደርግ፣ የኢሠፓና የግብረአበሮቹ ፀረ ዴሞክራሲያዊ ኀዳናዎች ሳይከተል አጥብቆ እየተቃወመና እየታገለ ከኢህአዴግ ጎን ተሰልፎ የሽግግር ፕሮግራሙን ተግባራዊ እንዲያደርግ ጥሪውን ያሰማል"

*የኢህአዴር የውጭ ቢሮ*

*13/03/ኢ.ኤ.አ 1991፤*

*ማሕተም፡፡*

ይህ መግለጫ ይፋ ከተደረገ በኋላ ደርግ አንድነትን፣ ኢህአዴግ ፀረ አንድነትን ሲያቀነቅኑና ለአመታትም ሲፋለሙበት የኖሩበት ነጥብ እንደመሆኑ መጠን፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞም በመካከላቸው አንዳችም ለሠላም ስምምነትና ድርድር የሚያበቃ ክፍተትም ፍላጎትም እድልም፣ ተስፋም ባለመኖሩ የቀረው አንድ ነገር ብቻ ሆኗል፡፡ ያም የእርስ በርስ



ፍጅቱን በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ባሉ ከተሞች ማጧጧፍና፤ ህዝቡን ማስጨረስ፣ በጦርነቱም የከተማዎቹን የመሠረተ ልማት አውታሮች ማውደም፤ ህንፃዎቹን ማስደርመስ ....ነበር፡፡ ይህ እንዳይሆን አስበው አገሪቱን በሠላም ለቀው በሚስጥር ሹልክ ያሉትን ጓድ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያምን ማመስገን ተገቢ ይመስላል፡፡

በወቅቱ ባልተያዙ ከተሞች አነስተኛም ቢሆን ሠራዊት ነበራቸው፡፡ 10ሺ የሚደርሱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማሠልጠኛ ውስጥ ከመኖራቸውም በላይ፤ ከልዩ ብርጌድ ሠራዊቱና ሸሽተው አዲስ አበባ ከገቡት ጋር ተዳምሮ ወደ 40 ሺ የሚጠጋ ሠራዊት ከእነትጥቁ ነበራቸው፡፡ ያም ሆኖ መንግስቱም እንደሚሉት በርሃ ውስጥ እንደ አዲስ የሽምቅ ውጊያ ለመጀመር ካልሆነ በቀር ፊት ለፊት ለመጋፈጥ የሚያስችል አይደለም፤ ሁኔታውም ምቹ አይሆንም፡፡

በዚህ መሠረት ግራ ቀኙን አይተው ተስፋ ያጡት ፕሬዝዳንት የአሜሪካን ግፊት መቀበል ነበረባቸው፡፡ እናም ግንቦት 13 በጠዋት ብላቴ ማሰልጠኛንና በውስጡ ያሉትን ምልምሎች ለመጎብኘት በሚል ጉዞ ጀመሩ፡፡

የመንግስቱን ከአገር አወጣጥ በተመለከተ እውነታውን በስተመጨረሻ የምናየው ይሁንና የቅርብ አጃቢዎቻቸውና ሾፌሮቻቸው እንዲሁም ራሳቸው መንግስቱ ለጋዜጠኛ ገነት አየለ ያሉትን እናስቀድም፡፡

ጄኔራል ቁጥር 20 እንዲህ ይላሉ "... ለጉብኝቱ በተወሰነው ቀን አብረዋቸው ከሚሄዱት አንዱ በመሆን ከጠዋቱ አንድ ሰዓት አውሮፕላን ማረፊያ ተገኘሁ፡፡ ሌላ አንድ ጄኔራልም በቀጠሮው ሰዓት ተገኝቶ ይጠባበቃል፡፡ ብናይ ብናይ እስከ 5 ሰዓት ድረስ ምንም የለም፡፡ ብላቴ ካለው አዛዥ ጋር በስልክ ስነጋገር አንድ አውሮፕላን በብላቴ በኩል ማለፉን ቢነግረኝም፤ አካባቢው ብዙ አውሮፕላኖች የሚመላለሱበት ስለነበር አልጠረጠርኩምና ዘግይተው ነው ብዬ መጠበቄን ቀጠልኩ፡፡ ወዲያው ግን ቺፍ ኦፍ ስታፉ ደወሉና ባስቸኳይ ቤተመንግስት እንድትመጣ ስላሉኝ ሄድኩ፡፡ ስደርስ ጄኔራል ተስፋዬ በሬዲዮ የተነገረውን ሲነግረኝ ማመን አቃተኝ ..." በማለት ".... እንደሚመስለኝ የመንግስቱን መሄድ አስቀድመው ያወቁ ሰዎች ነበሩ፡፡ ተገደው ወይም ተፅዕኖ ተደርጎባቸው ሄዱ የሚለውን ለማመን ያስቸግራል" ሲሉ፤ ግምታዊ ድምዳሜያቸውን ካዩዋቸው ነገሮች ተነስተው ያስቀምጣሉ፡፡ ጓድ ቁጥር 22 ደግሞ "ስለአወጣጣቸው ኮሎኔል መንግስቱ ያወሩት ውሸት ነው፡፡ እሳቸው ያወሩትን፣ የሳቸውን ትረካ አላምንም" ሲሉ፤ አጃቢ ቁጥር 5 ተብለው በትዝታዎች ቁጥር 1 መጽሐፍ ቃላቸውን ያሰፈሩት የመንግስቱ

የቅርብ አጃቢና ኬንያ ድረስ የሸኟቸው የሰጡት ምላሽ ደግሞ በአጭሩ እንዲህ ይነበባል፡፡

"... ከመንግስቱ ጋር በጣም ስለምንቀራረብና እንደወንድማቸው ያዩኝ ስለነበር፣ ስለሚያምኑኝና ቤተኛም ስለበርኩ፤ በዚያን እለት ማለዳ ላይ ወደመኖሪያ ቤታቸው ሄጄ ወ/ሮ ውባንቺን ሠላም ብዬ ጓዶች ለእለቱ ፕሮግራም ዝግጁ መሆናቸውን ሪፖርት አደረኩ" በማለት ከሌላው ጊዜ የተለዩ የጉዞ እንቅስቃሴ እንዳልነበር ይጠቁማሉ፡፡ ሲቀጥሉም "ሁላችንም ብላቴ ሞቃታማ ስለሆነ ቀላል ወታደራዊ ዩኒፎርም ነው የለበስነው፡፡ መንግስቱም ቢሆኑ ዘወትር ከሚይዙት ሳምሶናይትና በትረ መኮንናቸው በስተቀር ሌላ ነገር አልያዙም፡፡ ሻንጣ ወይም ቦርሳ አልተጫነም፡፡ ከፓይለቱና ከረዳት ፓይለቱ ጭምር ጠቅላላ አውሮፕላኑ ውስጥ የነበርነው ዘጠኝ ሰዎች ነበርን፡፡ ሁኔታዎች የተለወጡት ብላቴ ልንደርስ ስንል ነው፡፡ ፕሬዝዳንቱ ፓይለቱን ቀጭን ትዕዛዝ ሰጡት፡፡ "ከፍተኛ ስብሰባ ስላለብኝ ወደ ናይሮቢ ሂድ" አሉት፡፡ "ወደዚያ እንሄዳለን ስላልተባልኩ ካርታ አልያዝኩም" አለ ፓይለቱ፡፡ አጃቢዎቹም እኔም ደነገጥን፡፡ እሳቸው ግን ፍንክች ሳይሉ "የምቀርበት ጉዳይ አይደለምና እንደምንም ብለህ ሂድ፤ ካስፈለገ ከኮንትሮል ታወር ጋር ተገናኝተህ እንዲመሩህ አድርግ፣ ብቻ ናይሮቢ መድረስ አለብኝ" አሉት፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ ናይሮቢ ደረስን፡፡ ከዚያ በኋላ የሆነው ፍፁም የተደናበረና ውዥንብር የበዛበት ነው፡፡ በበኩሌ ማታውን ወደዙምባብዌ ከተጓዘው ግሩፕ ጋር እንድሄድ መንግስቱ ጠይቀውኝ ነበር፡፡ እንደማልሄድና ወደአገሬ መመለስ እንደምፈልግ ስገልፅላቸው አልተቃወሙኝም ወይም ሊያሳመኑኝና ሊያስቀሩኝ አልሞከሩም፡፡ ስመለስ የሚጠብቀኝ መጥፎ ነገር ሊኖር እንደሚችል በመግለፅ ግን ስጋታቸውን አልሸሸጉኝም፡፡

"ሀሳቤን እንደማልለወጥ ሲረዱ ለጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን የሚሰጥ ደብዳቤ ጽፈው ሰጡኝ፡፡ ይሄንንም በማግስቱ እንደተመለስኩ ለጄኔራሉ ሰጥቻለሁ፡፡ እንግዲህ በሬዲዮ እወጃው እንደሰማነው የወቅቱ ርዕሰ ብሄር ጄኔራል ተስፋዬ ስለነበሩ ይጠቅማል ያሉትንና ከመሄዳቸው በፊት ሊነግሯቸው ያልቻሉትን ጉዳዮች ነው ደብዳቤው ላይ ያሰፈሩት፡፡

ከደብዳቤው ሌላ እኔ በቃል እንድነግርላቸው የላኩኝ መልዕክትም ነበረ፡፡ እሱም፤ 1. በጓድ መንግስቱ ገመቹ ትዕዛዝ ብቻ ሊወጣ የሚችል ከሰባት ሚሊዮን ተኩል በላይ የሆነ ብር፣ 2. ፍቅረስላሴ ወግደረስና ኃይሉ ይመኑ የሚያውቁት ከድሬዳዋ የጫት ገቢ የሚገኝና ለሱዳንና ለሶማሌ ነፃ አውጪዎች በየጊዜው ወጪ እየተደረገ የሚሰጥ ተቀማጭ ገንዘብ፣ 3. በገልፍ ጦርነት ለኩዌት ድጋፍ ስለሰጠን የኩዌት መንግስት በእርዳታ የሰጠን 20 ሚሊዮን ብር (ኃይሉ ይመኑና የገንዘብ ሚኒስትሩ የሚያውቁት) ይሄ ሁሉ ገንዘብ እንዳለ አውቀህ፣ ከጓድ ነሲቡ ታዬ ጋር



ተነጋግረህ፣ ጦርነቱ ከቆመ ለከባድ ኢንደስትሪዎች ማቋቋሚያ ይሆናል የሚል ነበር፡፡ ደብዳቤውንም መልዕክቱንም አድርሻለሁ፡፡

በበኩሌ ምናልባት መንግስቱ ከመሄዳቸው በፊት ለጄኔራል ተስፋዬ ነግረዋቸዋል የሚል ግምት አለኝ፡፡ በሬዲዮ የመንግስቱ መጥፋት የተነገረበትን ሰዓት ሳገናዝበው ተስማምተው ያደረጉት ይመስለኛል፡፡ እኛ ከዚህ ተነስተን እዚያ የደረስንበትን ሰዓትና መሄዳቸው በስድስት ሰዓቱ ዜና ላይ ከመታወጁ በፊት (በኋላ እንደሰማሁት) ጄኔራል ተስፋዬን ከስብሰባ ላይ አስጠርተው በስልክ ያነጋገሯቸውን ጊዜ ሳስበው ሁለቱ ተስማምተው ይሆናል የሚል ጥርጣሬ አሳድሮብኛል፡፡

ባለቤታቸው እኛ ወደ ብላቴ ከሄድን በኋላ በሌላ አውሮፕላን ተሳፍረው ዙምባቡዌ መሄዳቸውን በኋላ ሰማሁ፡፡ ያኔ ቤተመንግስት ስደርስና ሠላምታ ስንለዋወጥ ግን መንገድ ሊሄድ እንደተሰናዱ አልነገሩኝም" የሚል ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ (ትዝታዎች ቁጥር 1 ገጽ 53) ፕሬዝዳንት መንግስቱ ግን "አካሄዴ ከሀገር ወጥቼ ለመቅረት ሳይሆን፤ ቀደም ብሎ ከቻይና ተገዝቶ በምፅዋና አሰብ ወደቦች መያዝ ምክንያት ሊገባ ያልቻለውን መሣሪያ በኬንያ በኩል ለማስገባት ከፕሬዝዳንት አራፕ ሞይ ጋር ለመነጋገር ነው" የሚል ሲሆን፤ ለአንባብያን ሁኔታው ግልፅ ይሆን ዘንድ ከጋዜጠኛ ገነት አየለ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ ቀንጨብ አድርጌ አካትታለሁ፡፡ ከተጠየቁ በኋላ ዙሪያ ጥምጥም የሆነ መልስ በመስጠት ላይ ሳሉ፤

ገነት፤ "ከአገር እንዴት እንደወጡ እንዲነግሩኝ ነበር የጠየቅሁዎት፤ ወደዚያ ብንመለስ"

መንግስቱ፤ ".... ከቻይና መንግስትና ከሌሎችም ወደ 70 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ መሣሪያ ገዝተን ስለነበር ያንን ልናስገባ ስንል አሰብን አስያዙት፡፡ የአሠብ መያዝ ጦርነቱን ውስብስብ አደረገው፡፡ ቻይናዎቹን በአውሮፕላን አቅርቡልን ብንል፤ በአውሮፕላን ማቅረብ አንችልም የምንችለው በመርከብ ነው አሉን፡፡ ይሄ በጣም አስቸጋሪ አጣብቂኝ ውስጥ ከተተን፡፡ በምፅዋ እናስገባ፤ በአሰብ እናስገባ፡፡ ....

..... የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ብላቴ ስልጠና ላይ ስለነበሩ ብላቴን ለመጎብኘት ተነሳሁ፡፡ በዚያው አንድ ነገር አሰብኩ፡፡ በሚስጥር ኬንያ ለመሄድ፣ ይህም አስፈላጊ ያልሆነ ግምት ተሰጥቶት ወሬ እንዳይዛባና "እንደዚህ ሄዶ ነበር" እንዳይባል ጥንቃቄ በማድረግ በጣም ከተወሰኑ ሰዎች በስተቀር ማንም ሰው እንዳይሰማ ወሰንኩ፡፡ .... አራፕ ሞይን በሚስጥር ለማነጋገር ፕሮግራም አወጣሁ፡፡ መጀመሪያ ደቡብ በመሄድ ማንም ሳይሰማ ናይሮቢ ደርሼ ለመምጣትና በፕሮግራሙ መሠረት ብላቴ እንደታቀደው ለመሄድ ወሰንኩ፡፡ ....

እኔ ጠዋት በሁለት ሰዓት ወደ ብላቴ በረርኩ፡፡ ከቦሌ የተነሳሁት ከጠዋቱ ልክ ሁለት ሰዓት ላይ ነው፡፡ ቡፋሎ አነስተኛ አውሮችላን ነው፡፡ ወደ ሦስት ሰዓት ላይ እነ ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን፣ በርከት ያሉ ከፍተኛ ባለሥልጣኖችና የጦር አለቆች ይሰባሰባሉ፡፡ አንድ ነገር ማዘጋጀት ነበረባቸው፡፡"

ገነት፡- "እርስዎን ለመሸኘት ነው የተሰባሰቡት?"

መንግስቱ፡- "... ምን እኔን ይሸኛሉ? እኔማ ሄጃለሁ፤ መንገድ ላይ ነኝ፡፡ ሦስት ሰዓት ላይ ነው የተሰባሰቡት፡፡ ገና እግሬ ሲወጣ ማለት ነው፡፡ እኔ ሁለት ሰዓት ላይ ወጣሁ፤ እነሱ ሦስት ሰዓት ላይ ተሰባሰቡ፡፡ ይሄን የምነግርሽ ከወጣሁ በኋላ የተረዳሁትን ነው፡፡ እኔ አምስት ሰዓት ናይሮቢ ደርሼ መውረድና መታየት አልፈለግሁም፡፡ አምባሳደሩ እንዲመጣ ስጠይቅ "የለም ኡጋንዳ ሄዷል፡፡ የፖለቲካ አታሼው ብቻ ነው ያለው" አሉኝ፡፡ እሱን አስጠርቼ ፕሬዝዳንት አራፕሞይን "እባክዎ በጣም ጥብቅ ለሆነ ጉዳይ ለአጭር ጊዜ ላነጋግርዎ እፈልጋለሁና ቢቻል እዚህ ኤርፖርት ያለዚያም ቤተመንግስትዎ ያነጋግሩኝ" ብለህ ንገር ብዬ ላኩት፡፡"

ገነት፡- "ይቀርታ ላቋርጥዎትና ከዚህ በፊት እንዲህ ያለ ሚስጥራዊ የሆነ ጉብኝት በሚያደርጉበት ጊዜ በአካባቢዎ ያሉትን ሰዎች እንዲሁም የፕሮቶኮል ኃላዎች ያሳውቃሉ ወይስ እንዴት ነበር ከዚህ በፊት በሚስጥር ጉብኝት የሚያደርጉት?"

መንግስቱ፡- "አዎን፤ እሱማ አውሮፕላን የሚያዘጋጁልኝ፣ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ የሚያደርጉልኝ እነሱ አይደሉም እንዴ?"

ገነት፡- "እና ያውቁ ነበር ማለት ነው?"

መንግስቱ፡- "እንዴ! ከቦሌ አይደለም እንዴ ተሳፍሬ የሄድኩት?"

ገነት፡- "ግን እነሱ ኬንያ መሄድዎን አያውቁማ"

መንግስቱ፡- "እሱንማ እንዴት ብዬ እናገራለሁ? እኔ ብላቴ ነው የምሄደው ነው ያልኩት፡፡ ደግሞ ነው፡፡ ኬንያ ሄጄ ፕሬዝዳንት አራፕሞይን ለማነጋገር ነው፡፡ ማንም እንዲሰማ ማንም እንዲያውቅ አልፈለኩም፡፡ ቢችሉ...."

ገነት፡- "እና ለማንም አላማከሩማ?"

መንግስቱ፡- "ቢችሉ ..." እያሉ ሌላ ነገር ማውራታቸውን ይቀጥሉና ከኬንያው ፕሬዝዳንት ጋር ስለነበራቸው ቆይታ ይተርካሉ፡፡

ቆይታው መሣሪያ በሞምባሳ በኩል የሚያስገቡበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹላቸው መጠያየት እንደነበር ነው መንግስቱ የሚገልፁት፡፡ አራፕሞይ ደግሞ እሽታቸውን እንደገለፁና፤ ምሣ በልተው እንዲመለሱ እየጠየቋቸው ሳለ፤ በመሀል አንድ መልዕክተኛ መጣና ለኬንያው ፕሬዝዳንት አንድ ነገር ሹክ አላቸው ይላሉ መንግስቱ፡፡ ሲቀጥሉም "ምን



እንደሆን አልገባኝም፡፡ ለካስ በአዲስ አበባ ሬዲዮ ስልጣን በፈቃዴ ለቅቄ የመሄዴ ነገር ተነግሮ እሱን ሪፖርት እያደረጉላቸው ነው፡፡ ሁኔታውን ከሳቸው አፍ ሰማሁ፡፡ በፈቃዴ ስልጣኔን ለቅቄ መሄዴን አራፕሞይ ነገሩኝ፡፡ ገረመኝ፡፡ ወዲያውኑ አዲስ አበባ ደወልኩና አንድ ሰው አገኘሁ..." እያሉ ይቀጥላሉ፡፡ ይህ ያገኙት ሰው ሁሉም ስብሰባ ላይ እንደሆኑ ይገልፁላቸዋል፡፡

"በእውነቱ እነተስፋዬ ተሰባሰቡ አልተሰባሰቡ ምንም የሚከፍቱት ድስት እንደሌለ አውቃለሁ፡፡ እኔ ምንም ልሁን፤ ግድ የለኝም፡፡ አሁን ጥያቄው ወያኔ እየገፋ ነው፡፡ የታጠቀ ህዝብና ሠራዊት ይዞ መመከት የሚቻለው እንዴት ነው? ስለዚህ እንደገና አራፕሞይን ሄድኩና "ሌላ ነገር ልጠይቅዎ ነው" አልኳቸው፡፡ "ምን" ሲሉኝ "አንድ አውሮፕላን እዘዙልኝና ቻይና ልሂድ" ስላቸው ነገሩ ከበድ አላቸው መሰለኝ፤ ትንሽ ጊዜ ስጠኝ፣ ልምከርበት ብለው ብዙ አስጠበቁኝ፡፡ ቆይተው መጡ፡፡ በዚያን ጊዜ ውስጥ ለካ ከአሜሪካኖቹ ጋር ግንኙነት አድርገው ኖሯል..." እያሉ በመተረክ አራፕሞይ "አዝናለሁ ወዳጄ አልችልም፤ ስልጣን ለቀህ ከአገር መውጣትህን አሜሪካኖች ሰምተዋል፤ ስለዚህ የጠየከውን ብናደርግ ብሔራዊ ጥቅማችን አደጋ ላይ ይወድቃል..." የሚል መልስ እንደሰጧቸውና፤ ቻይና ሄደው ስለመሳሪያው ጉዳይ በግንባር የመነጋገር እቅዳቸው እንደማይሆን ሲረዱ፤ "እሺ በቃ ወደ ዙምባቡዌ ሄጄ ከሙጋቤ ጋር ተነጋግሬ ሌላ መንገድ እንድፈልግ ወደዚያ የምሄድበትን ትራንስፖርት ስጡኝ አልኳቸው" ይሉናል፡፡

"በመጨረሻ ምሽት ላይ አውሮፕላን ቀርቦልኝ ልሳፈር ስል ሻለቃ ደመቀ ባንጃው ቀረበና "እኛ እንመለስ" አለኝ፡፡ "ለመመለስ ነፃ ናችሁ፤ ግዴታ የለም" ብየው ተሰነባብተን ተለያየን" ብለዋል መንግስቱ፡፡

አንድ ፕሬዝዳንት አገሩን ከመጨረሻው ጥቃት ስለሚከላከልበት ስለ 70 ሚሊዮን ዶላር መሣሪያ ጉዳይ እንዴት ብቻውን ሚስጥር አድርጎ ይይዛል? ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሊይዝ ስድስት ቀናት በቀረው ሁኔታ የተባለው ምሣሪያ ስድስት ወር እንኳን ቢቀረው እንዴት በዚያ ሰዓት ይታሰባል? ሁሉም ሽሽት ላይ በነበረበት በዚያ ቅፅበት መሣሪያ ለማምጣት የተዘጋጀ ፕሬዝዳንት ለባለስልጣናቱ መንገርና እየተከላከሉ እንዲቆዩ፣ መሣሪያው ስለሚገባበት ሁኔታ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ሳይገልፅ በሚስጥር ማድረግ ይገባዋል? ይሄ እንዴት ይታመናል?

በመንግስቱ አገላለፅ'ኮ ሐራሬም የሄዱት ሙጋቤ ከቻይናዎቹ ጋር ጥሩ ቀረቤታ ስላላቸው መሣሪያውን የማስገባቱን ሂደት እንዲያፋጥኑላቸው ለመወያየት መሆኑ ነው፡፡

ከቦሌ አለመነሳታቸውም በደንብ ይታወቃል፡፡ በጥቅሉ በማስተባበያ ገለፃቸው ውስጥ አንዲት የምትታመን ዓረፍተ ነገር

ካለመኖሯም በላይ፤ 1ኛ. መንግስቱ 5 ሰዓት ናይሮቢ ከመድረሳቸው በፊት 4 ሰዓት ላይ ባለቤታቸው ወ/ሮ ውባንቺ ቢሻው በሌላ አውሮፕላን ወደ ዙምባቡዌ ሄደዋል። ዜናው 6 ሰዓት ላይ ከመሰራጨቱ በፊት።

2ኛ. የፕሬዝዳንቱ አጎት የሆኑትና በዙምባቡዌ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው ይሰሩ የነበሩት አምባሳደር አስራት ወልዴ በነዚያ ቀናቶች አዲስ አበባ የነበሩ ሲሆን፤ ወ/ሮ ውብአንችን እና ልጆቻቸውን ይዘው የሄዱትም ራሳቸው ናቸው። የመንግስቱ የመጀመሪያ ልጅ ከአንድ ዓመት በፊት ዙምባቡዌ ውስጥ ዩንቨርሲቲ ገብታ ስትማር ብትቆይም፤ ሁለቱ ልጆቻቸው ግን በዚያው እለት ወደ ዙምባቡዌ እንዲሄዱ ተደርጓል። ከሙጋቤ ጋርም ፍፁም ወዳጆች ነበሩ።

ይሄ "ሳላስበው ነው የወጣሁት" የሚለው ነገር ከግራም ከቀኝም ቢታሰብ እውነት አለመሆኑ ለማንም አይሰወርም። ነገር ግን መንግስቱ በሽምቅ ውጊያ ለመቀጠል ሲያስቡ በአሜሪካ "አይሆንም" በሚል ግፊት ተገደው መሄዳቸው አይካድም። ይልቅ አንድ እውነት አላቸው። ቀንደኛ ጠላታቸው እንኳን ሳይቀሩ "መንግስቱ የገንዘብን ጥቅም ራሱ የሚያውቁት አይመስለኝም። አምስት ሳንቲም አይፈልጉም። ሌላው ቀርቶ የፕሮቶኮላቸውን ሳይቀር ለግንባታ ይዋል ነው የሚሉት" ይሏቸዋል።

መንግስቱ "በሻምሶናይት የታጨቀ ዶላር ይዘው ነው የወጡት አሉ?" ስትል ትጠይቃለች ገነት።

"... ከኢትዮጵያ ስወጣ በቻዬን አይደለም የወጣሁት። አብረውኝ የነበሩ ሰዎች ገንዘብ ጭኜ ወጥቼ ከሆነ መመስከር ይችላሉ። በትረመኮንኔንና የደንብ ልብሴን ነው ይዤ የወጣሁት። ራቁቴን ነው የወጣሁት። የገንዘብ ሰው ብሆን ኖሮ ያንን በመሰለ ቀውጢ ጊዜ ሳይሆን 17 ዓመት በስልጣን ላይ በነበርኩበት ወቅት የፈለኩትን ማድረግ እችል ነበር። ሀገሬን ለመልቀቅ ከመገደዴ ጥቂት ሳምንታት በፊት የኩዌት መንግስት በስሜ በቼክ የላከውን 20 ሚሊዮን ዶላር ትቼ ነው የወጣሁት። ከዚያ ጥቂት አመታት ቀደም ሲል የሊቢያው ኮሎኔል ጋዳፊ እንደዚሁ በስሜ የላከውን 150 ሚሊዮን ዶላር ገቢ አድርጌ ለአገር ግንባታ ውሏል። እኔ ለአገሬ ገንዘብ አምጪ እንጂ ገንዘብ ዘራፊ አይደለሁም። የባዕዳን ፊት እንደ እሣት እየገረፈኝ፣ ከውጪ እርዳታ እየለመንኩ እያመጣሁ ነው ለግብርና፣ ለኢንደስትሪ፣ ለማዕድን ሲውል የነበረው። ስምንት ቢሊዮን ሩብል አልከፈልንም። ከብዙ ሶሻሊስት አገሮች የመጣ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ አልተከፈለም። በነፃ ብር እያመጣሁ ለአገር ልማት ያዋልኩ ነኝ። በዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ አይጠረጥረኝም።...

"ወያኔዎች እንደራሳቸው ስለሚመስላቸው የፈለጋቸውን ሊያስወሩ ይችላሉ። እነሱ በባዶ እግራቸው መጥተው ዛሬ ባለማርቸዲስ ናቸው። በቁምጣ መጥተው ዛሬ ሚሊየነሮች ናቸው። የእነሱ ጠቅላይ ሚኒስትር



(የነበረው) ታምራት ላይኔ የመንግስት ካዝና ውስጥ እጁን ከቶ ሳይርመጠመጥ ጥቂት ዓመታት እንኳን መቆየት አልቻለም። ሌሎችም ያው የምናያቸው ናቸው። በሙስና እየተጨማለቁ የአዲስ አበባን ወሀኒ ቤት አጥለቅልቀውት የለ? ያችን አገር ከ17 አመቴ ጀመሮ እስከ 1983 ድረስ ለ33 ዓመታት አገልግያታለሁ። ሳገለግል ደግሞ በወታደርነት በበረሐ ተቃጥዬና ብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን አሳልፌ ነው። በመሪነት አገልግያለሁ። ጡረታ የለኝም። ለሀገሬ ደምቻለሁ። እንቅልፍ ሳያምረኝ ደክሜያለሁ፣ ቤት የለኝ፣ መኪና የለኝ፣ የሰው ተመፅዋች ሆኜ ነው የምኖረው። ምንም የማያውቁኝ፣ የማይወልዱኝ አፍሪካውያን ወንድሞቼ ዛሬ በድካሜ ጊዜ፣ ጤናዬ በጎደለ ጊዜ ሲመግቡኝ ወያኔ ገንዘብ ወሰደ ቢለኝ አይደንቀኝም። ፍርዱን ለታሪክ እተወዋለሁ።

አፍሪካውያን መሪ ጓዶች ሳይጥሉኝ ደግፈውኛል። ልጆቼን አስተምረውልኛል። የምግደረደርበትን ገንዘብ ረድተውኛል፤ እየረዱኝም ነው።

"ዛሬ የሚፀፀቱም፣ ወያኔ የሚጨፍርባቸውም እንዳሉ አውቃለሁ። ደስተኛ ሆኖ የሚኖር የእነሱ ጥገኛና ተለጣፊ ካልሆነ በቀር በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ ደልቶት እንደማይኖር እገነዘባለሁ። በእኔ ላይ በደረሰውም ተደሳች አይደለም፤ ለራሱም ተደሳች አይደለም" (ትዝታዎች ቁጥር 1 ገጽ 352)

ግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ.ም በ6 ሰዓቱ ዜና "ለሀገሪቱ ሰላም እንደሚበጅ የመንግስት ምክር ቤት ስላመነበትና እርሳቸውም ስለተስማሙበት ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም በራሳቸው ፈቃድ አገር ለቀው ወጥተዋል..." የሚል ዜና በብዙሃን መገናኛ ተደመጠ። "የፕሬዝዳንትነት ስልጣኑንም ሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ተረክበው ይሰራሉ" ተባለ።

በተከታዩ ሰዓት ዜናው ሲደገም ግን የክብር ስማቸውም፤አንቱታውም ቀረና "መንግስቱ ኃይለማርያም አገር ጥሎ ፈረጠጠ" ተብሎ ተሰራጨ፤ተደጋግሞም ተደመጠ።
እንዲህ ተብሎ እንዲነበብ ያደረጉት ታማኝ ነው ብለው ቀደም ሲል ሾመዋቸው የነበሩት ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ናቸው።የቀድሞው ወዳጃቸውን ከዷቸው፣አላገጡባቸው ማለት ነው።በማን ዘንድ ሊወደዱ እንዲህ እንዳደረጉ የብዙዎች ጥያቄ ሆኗል።

ከዚህ ዜና ጋር በተያያዘ አንድ እውነት አዘል ቀልድ አለ፤ እንዲህ የሚል፤ ዜናውን ያነበበው ጋዜጠኛ ዳሪዎስ ሞዲ ነገሩ ካለፈ በኋላ ሲጠየቅ ነው፤ "መጀመሪያ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ከአገር ወጥተዋል፤ ብለህ አንብበህ በድጋሚ ስርጭቱ ግን ፕሬዝዳንትም ሳትል፣ አንቱታውንም

ትተሀ "አንተ" እያልክ የጠራሃቸው ለምንድነው?" ተብሎ ሲጠየቅ፤ "ብችል አንቺ ብለው ደስ ይለኝ ነበር" አለ፡፡

እውነትም እንደማንኛውም አፍሪካዊ መሪ የመንግስቱ ረጅምና በውጣ ውረድ የተሞላ የስልጣን ዘመናቸው በውዳሴ ከንቱ የተሞላ እንደነበር ቀልዱ ያስረዳናል፡፡ በእርግጥ ከመንግስቱ አገር ወዳድነት እንፃር፣ በህዝቡም፣ በሠራዊቱም ዘንድ በቆራጥነታቸው ስለሚታወቁ "አገር ጥዬ ሸሸሁ" ቢሉ ሐፍረት ነውና ማስተባበላቸው አይገርምም፡፡ ግን "ማን ያምነኛል?" ብለው ራሳቸውን አለመጠየቃቸው ግልፅ ድክመት ነው፡፡

የመንግስቱ ሽሽት ይፋ ከሆነ በኋላ ርዝራዡ ሠራዊት ወደ ከተማ እየሸሸ መጣ፡፡ ትጥቁን ፈቶ እየተማረከ፣ ሌላውም እየሸጠ ተበታተነ፡፡ መንግስቱ "አገር ጥሎ ኮበለለ ተብሎ ለህዝቡ መገለፁን ስሰማ ታመምኩ..." እስከማለት ደርሰዋል፡፡

ሊያሳምማቸው የቻለው እንዲያ ተብሎ እንዲገለፅ ያልፈለጉት፤ ነገር ግን እንዲህ ተብሎ የተገለፀባቸው ዜና ብቻ ነው፡፡ "... እርሳቸውም አምነውበት፣ አገር ለቀው ሄደዋል፣ ፈርጥጠዋል፣ ሸሽተዋል..." ይህም ሲባል እርሳቸው ምን ተብሎ ለህዘብ እንዲገለፅላቸው ነበር የፈለጉት? የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም፡፡

መንግስቱ እንዲባል የፈለጉትና ቀድመውም ከታማኛቸው ከጄኔራል ተስፋዬ ጋር ያቀዱት፤ ሁኔታው ከፍቶ የቀናት እድሜ ብቻ እንደቀራቸው በመረዳት፤ ኢህአዴግ አዲስ አበባ በሚገባበት ጊዜ "ፕሬዝዳንቱ ከቀናት በፊት ከቻይና የተገዛውን መሣሪያ ለማምጣት ከአገር ወጥተው ነበር፡፡ በመሐል ኢህአዴግ ሲገባ ባላሰቡትና ባልጠበቁት መንገድ በወጡበት ለመቅረት ተገደዱ" የሚለው የታሪካቸው ማብቂያ ሆኖ እንዲቀር ነበር፡፡ ሳይሆን ቀርቶ ኢህአዴግ ቤተመንግስቱን ከመቆጣጠሩ በፊት እግራቸው እንደወጣ ለህዝብ ይፋ ሆነ፡፡ በዚህም ፕሬዝዳንቱ ተበሳጩ፡፡ ብስጭታቸውንም ለመግለፅ ስልክ ደውለው ጄኔራሉን አስጠሩ፡ ጄኔራሉ ግን ሊያናግሯቸው ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ ስለዚህ ከነንዴታቸው ቤተሰቦቻቸው ወደሄዱበት ወደ ዙምባቡዌ አመሩ፡፡ መረጃው በእቅዱ መሠረት ይፋ ሲሆን እውነት መስሎ እንዲታይም አወጣጣቸው ድንገት እንደነበር ሊጠቁሙ የሚችሉ ዘዴዎችን መጠቀም ነበረባቸው፡፡ ያንንም አድርገዋል፡፡ ከኬንያ ወደ ዙምባቡዌ የተጓዙትም አሜሪካ በላከችላቸው አውሮፕላን ነው፡፡

## የሶሻሊስት መሪዎች ውድቀትና የመንግስቱ የስደት ህይወት

ውድቀቱ የደርግ መንግስትና የፕሬዝዳንት መንግስቱ ብቻ አልነበረም፡፡ የመላው ዓለም ሶሻሊስት አራማጅ አገራት የሆኑ መንግስታት ሁሉ በጋራና ሆን ተብሎ በተሰራ ስራና ሴራ የወደቁበት ዘመን ነው፡፡



ማን መቼና እንዴት በማን በምን አይነት ዘዴ መውደቅ እንዳለበት ታቅዶ ያለቀና በተያዘለት እቅድ መሠረትም ተግባራዊ የሆነ፤ በኃይል የሚወርዱ መንግስታት የትኛው እስር ቤት መግባት እንዳለበት፣ ማን በግዞት መኖር እንደሚገባው፣ ማን አገሩ ላይ ታስሮ እንደሚቀር በዝርዝር ሰፍሮ ያበቃለት ጉዳይ ነው፡፡ በአምባገነንነት የሚፈረጁ መንግስታት ስም ዝርዝር ተመዝግቦ፣ መውደቅ እንዳለባቸው ታምኖበት ተወስኗል፡፡

በዚያ ወቅት አሜሪካ ከፍተኛ የቤት ስራዋ ይሄ የነበረ ከመሆኑም በላይ፤ ወደ ተግባር ለመለወጥ ቀላል ስራዋ ነበር፡፡ ስራው የከበደው የማንም እጅ እንደሌለበት ለማሳመን የሚደረጉ የረቀቁ አሰራሮችን መቀመር የግድ በመሆኑ ምክንያት ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ሽፋንነት ይረዱ ዘንድም አሜሪካ ሠላማዊ አደራዳሪ መስላ መታየት ግዴታዋ ነበር፡፡ የአፍሪካ፣ የእስያና የአውሮፓ ኮሚኒስት አገዛዞች በጋራ ሲወድቁም በተጠቀሱት አገራት ህዝቦች ዘንድ የአሜሪካ ስም እንዳይነሳ ልዩ ጥንቃቄ አድርጋለች፡፡ እንግሊዝም ጭምር፡፡

የደርግ መንግስት ምንም አይነት ተቃዋሚ ባይኖረውና ሻዕቢያ ወያኔ ገለመሌ ባይኖሩ ኖሮም የግድ መውደቅ ግን ነበረበት፡፡ "በአዲሱ የአሜሪካ ርዕዮት እመራለሁ ተውኝ" ቢል እንኳ የቀድሞ መሪ ስለሆነ ብቻ ተቀባይነት አያገኝም ነበር፡፡

ጓድ መንግስቱ "ያካሄድነው'ኮ አብዮት ነው!" እያሉ ይፎክሩ እንደነበረው ሁሉ፤ እኛም አሜሪካን "ያካሄደችው'ኮ የዓለም አብዮት ነው!" ማለት እንችላለን፡፡

ይሄን ለማለት ያስፈለገኝ "የመንግስቱን ከአገር የመውጣት ዘዴ ያቀናበረችው አሜሪካ ናት" የሚለውን እውነት ለማጠናከር አይደለም፡፡ እሱ ከነጭም በላይ ንፅት ያለ ሐቅ ነውና ምንም ማጠናከሪያ አይፈልግም፡፡

ከዚህ ይልቅ ጠርነት የሌለባቸው ኮሚኒስት አገራትስ መች ቀረላቸው? ለማለትና ለተከታዩ የመንግስቱ ኃይለማርያም ምላሾች መንደርደሪያ ይሆነኝ ብዬ ነው፡፡

መች ቀረላቸው? ለሚለው የፖላንዱ ፕሬዝዳንት ያሩዜልስኪ፣ (ፍፁም አምባገነን ኮሚኒስት መሪ) የአልባኒያ መሪዎች ባልና ሚስቱ ነዝህሚጅ ሆጃ እና ኤንቨር ሆጃ (አልባኒያን የመጀመሪያዋ ሃይማኖት የሌለባት አገር አድርገው መስጊድና ቤተክርስቲያን አፍርሰው በምትኩ 700 ሺ የማይንቀሳቀስ የታንክ ሐውልት በከተማዋ የገነቡና ሶሺሊዝምን ከጥቃት ለመከላከል በሚል በሰሩት ፒራሚድ የአገሪቱን ሐብት ያደቀቁት፣ ህዝቡም በሐውልት ታንኮች እየገባ ተጠልሎ እንዲከላከል ያደረጉ (የሚገርመው የእማሆይ ቴሬዛ አገር አልባኒያ መሆኑ ነው)፣ የሃይቲው መሪ

ዥን ክሉድ ዱቫልዮ (ቮዶ የሚባል ሚስጥራዊ ሃይማኖት መስርቶ በቤተመንግስት ራሱ አምላክ ሆኖ የሚመለክበትን ስርዓት የመሠረተ፣ አባትየውና ልጁ ዥንክሉድ ዱቫልዮ ፓፓ ዶክ እና ቤቢ ዶክ ሃይቲን ሙልጭ አድርገው የዘረፉ ተከታታይ ፕሬዝዳንቶች ሲሆኑ፤ "አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር" እያለ የሚቀጥለውን ክርስቲያናዊ ፀሎት "አባታችን ቤቢ ዶክ ሆይ፤ በቤተመንግስት የምትኖር፣ ስምህ ይቀደስ … መንግስትህ በሐይቲ እንደሆነች…" እየተባለ የሚቀጥል ፀሎት አርቅቀው ከትምህርት ቤት ጀምሮ ለሐይቲ ዜጎች ያስተማሩና የአገሪቱን የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ ህዝብ እምነቱን አስቀይረው በአብዮታውያኑ እንዲያምኑ ያደረጉ…)፣ የሴንትራል አፍሪካው የእድሜ ልክ ፕሬዝዳንት፣ ቀጥሎ ንጉስ የሆኑት ቦካሣ (የሰው ስጋ በመብላት የተከሰሱና ከእያንዳንዱ የዓለም አገራት ሴቶች አንድ አንድ ሚስት ያገቡ፣ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ሚስቶቻቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ ልጆች የወለዱ፣ ለእያንዳንዷ ሚስት በሴንትራል አፍሪካ ዋና ከተማ በባንጉይ ምርጥ ምርጥ ቪላ ቤት የሰጡ፣ አገሪቱን የግላቸው ሱቅ ያደረጉ፣ በቦካሳ መንገድ፣ በቦካሳ ስጋ ቤት፣ በቦካሳ ዩኒቨርሲቲ፣ በቦካሳ ቡቲክ፣ በቦካሳ ጎዳና፣ በቦካሳ … ተጉዥ መጣሁ በሚያስብል መልኩ የአገሪቱን ሀሉንም ነገር በስማቸው ከመሰየም አልፈው ሁሉም ተቋማት በራሳቸው ስም የተመዘገቡ የነበሩ፣ የትምህርት፣ የገንዘብ፣ የፍርድ፣ የማስታወቂያ፣ የንግድ፣ የሁሉም የአገሪቱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ሁሉ ሚኒስትር የነበሩ…)፣ በአምባገነንነታቸው የሚታወቁት ሰው በላ የኡጋንዳው ኢዲአሚን ዳዳና ሌሎች ሁሉ በአንድ አይነት ዘመን የወደቁ ናቸው፡፡ የወደቁት ግን በሸማቂ ቡድን አልነበረም፡፡ በተከታታይ በተደረጉ በራሳቸው ህዝቦች የከተማ ሠላማዊ ሰልፍ አማካኝነት ነው፡፡ በመፈንቅለ መንግስት ነው፡፡ ተተኪዎቹንም በካፒታሊዝም አጥምቀው አዘጋጅተዋል፡፡

የኢትዮጵያው መንግስቱም ከተጠቀሱትና ካልተጠቀሱት አገራት መሪዎች ውድቀት እኩል በአንድ ጀንበር የሆነ ሁነት ሲሆን፤ የግላስኖስትና የፔሬስትሮይካ ግብም ይሄው ነበር፡፡ ለእነዚህ መንግሥታት ውድቀትና ለርዕዮቱ ማክተም፣ ብሎም ዓለምን በአንድ አሜሪካና በጥቂት አጋር አገራት እግር ስር ለማንበርከክ፣ ዓለም በአንድ ጎታ ትከተት ዘንድ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት እቅድም ተይዞለት ቅድመ ስራው ተጠናቆለት ወደ ተግባር የተለወጠ ዓለም አቀፍ ስራ ነው፡፡ ይህ ዓላማ ግቡን ይመታ ዘንድም በየአገራቱ እንኳንስ የታጠቀ ተቃዋሚ በአገሪቱ ውስጥ ያለበትን መንግስት መርዳት፤ በሠላም እየተገዙ የነበሩ ህዝቦችን በአንድ ቀን ለማሳመፅና መሪውን ለማስወገድ አልከበደም፡፡ ስለዚህም አሜሪካ ጥገኝነት ሰጭ አገራትን ሲቻል በራሷ ምርጫ፣ ካልሆነም ወዳቂውን መንግስት እንዲመርጥ በመፍቀድ በቅድሚያ ማመቻቸትና ሠላም አስከባሪ መስሎ



መታየት የስራው አፈፃፀም እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ የአገር ምርጫው ለራሳቸው ከተተወላቸው መሪዎች ውስጥ አንዱ መንግስቱ ኃይለማርያም ናቸው፡፡ ኢዲአሚን ዳዳ ሳውዲ ዓረቢያ፣ ቦካሳን ወደ አስር ቤት፣ ዱቫልዮንና መሰሎቹን ወደ ቀድሞ ገዥዎቻቸው ወደ ፈረንሣይ፣ አውሮፓውያኑን ባገራቸው እስር ቤት ወዘተ… እንደሚሆን እንደሚሆን አደረጓቸው፡፡ የእነቦካሳ ንብረት በፈረንሣይ ተወረሰ፡፡ የዱቫልዮና የሌሎቹ የስዊዝ ባንክ ገንዘብ ተወረሰ፡፡ ያልተወረሰው ገንዘብ የመንግስቱ ኃይለማርያም ሲሆን፤ ያልተወረሰውም በየትኛውም አገር ባንክ ምንም ገንዘብ ስላልነበራቸው ብቻ ነው፡፡ እና … እነዚህን ሁሉ አምባገነን መሪዎች በያሉበት አገር እየዞረ፣ በየታሰሩበት እስር ቤት እየሄደ፣ ጥገኝነት ጠይቀው እየኖሩ ያሉትን በየተጠጉበት አገር እየተዟዟረ ስላለፈው ታሪካቸው እየጠየቀ፣ የሰጡትን ምላሾች አሰባስቦ እ.ኤ.አ በ2003 ዓ.ም ጣሊያናዊው ጋዜጠኛ ሪካርዶ ኦሪዚዮ Talk of The Devil በሚል ርዕስ ለሕትመት አበቃው፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው በአማርኛም ጭምር "የሠይጣን ኑዛዜ" ተብሎ የተተረጎመው ይህ መጽሐፍ፤ በሚያሳፍርና ፍትሐዊነት በጎደው መልኩ የፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያምን ታሪክ ከሰው ስጋ በሊታዎች ከእነቦካሳ፣ ከእነ ኢዲአሚን ዳዳ፣ ከእነዱቫልዮ … ከሁሉም ወዳቂ የቀድሞ ሶሻሊስታዊ መሪዎች ጋር አካትቶ ነበር ለሕትመት ያበቃው፡፡ መንግስቱ ምንም አምባገነን ቢባሉም ከእነዚህ ዘራፊዎችና ሰብዓዊነት ካልፈጠረባቸው መሪዎች ተርታ ተመድበው መፃፋቸው ተገቢ አለመሆኑ ለማንም ግልፅ ከመሆኑም በላይ የጣሊያን ምሁራንና ጋዜጠኞች ባገኙት ቀዳዳ ሁሉ አእንደማይተኙልንም ይጠቁማል፡፡

ለማንኛውም መንግስቱ ለሌሎች ከሰጡት ምላሽ ይልቅ ለዚህ ጋዜጠኛ የሰጡት ምላሽ በአጭሩም ቢሆን የተሻለ ይመስላል፡፡ ሊዋሹት መሞከርንም የፈለጉት አይመስልም፡፡ ለዚሁ ጋዜጠኛ በጠየቃቸው መሠረት በመጠኑ ገልፀውለታል፡፡እናም የስደት ህይወታቸው በራሱ ታሪክ ነውና ከዚሁ መጽሐፍ በመነሳት አለፍ አለፍ እያልን ጥቂት ገለፃዎቻቸውን አድምጠንላቸው እናብቃ ልላችሁ ነው፤ እንዲህ የተንደረደርኩት፡፡

መንግስቱ ምንም እንኳ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ቢታይባቸውም፤ ከሐራሬ ወጣ ብሎ በሚገኘው እና ለመኖሪያነት በተከለለው አካባቢ በሚገኘው መካከለኛ ቪላ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ እየኖሩ ነው፡፡

እድሜያቸው ሰባ ሞልቷል፡፡ ፀጉራቸውንም ሽበት ወሮታል፡፡….‹‹እንዴት ነህ ነው ያልከኝ…››ጥያቄውን ደገሙት፡፡ትንሽ አሰ..ብ ካደረጉ በኋላ መልስ ሰጡ፡፡‹‹እኔነቴን ከጠየከኝማ ተርፌያለሁ፤እንዲያውም ደህና ነኝ እንበለው…››

መንግስቱ ደስ ባላቸውና ፈካ ባሉ ቀን የሚያስቡት በጭራሽ እንዳልታሰሩና ነፃ እንደሆኑ አድርገው ነው፡፡ "ፈጽሞ ተረስቼ አላውቅም፡፡ አሁንም ቢሆን በታዳጊ ሀገሮች በተለይም አፍሪካ ውስጥ ሁነኛ ወዳጆች አሉኝ፡፡ መቼም ስማቸውን ይዘረዝርልኛል ብለህ አትጠብቅም?" ይሉታል ለጋዜጠኛው፡፡

በደበራቸውና በከፋቸው ቀን ደግሞ አብዛኛዎቹ ሰዎች መጥፎ እንደሆኑ አድርገው ይገምቱና ተስፋ በመቁረጥ ስሜት ውስጥ ጭ…ልጥ ብለው ይገባሉ፡፡ "የትም ቦታ ብሄድ እታወቃለሁ፡፡ እንግዲህ የት መሄድ እችላለሁ? ምንም ቢሆን ምን ያው መንግስቱ ነኝ" ይላሉ፡፡ መንግስቱ ሐራሬ ከገቡ ከ10 ዓመት በኋላ ወደ ሆቴሎች እየሄዱ ዘና ማለት ጀምረው ነበር፡፡ ሆኖም የሚከታተላቸው ሐበሻ መኖሩን ካረጋገጡ በኋላ ልማዳቸውን ቀየሩ፡፡ የሙጋቤ መንግስትም ራሳቸውን እንዲደብቁ አስጠነቀቃቸው፡፡

በስደት ህይወት 10 ዓመታትን እንዳሳለፉም የልብ ህመማቸው ስላሰቃያቸው በዙምባብዌ የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ወደ ጆዋንስበርግ በመጓዝ ጋርደን ሲቲ ከሚባል የህክምና ተቋም ቀጠሮ ይይዛሉ፡፡ ህክምና ከማግኘታቸው በፊት ግን ወሬው ጋዜጠኞች ጆሮ ደርሶ ዓለም አቀፍ ርዕስ ሆነ፡፡ የኢትዮጵያ መንግስትም አጋጣሚውን ተጠቅሞ በዘር ማጥፋት ወንጀል እንደሚፈለጉ ገልጾ ባስቸኳይ ተላልፈው እንዲሰጡት እስከመጠየቅ ደረሰ፡፡ ይህም የሞት ፍርድ ማስከተሉን የተረዱት መንግስቱ ህክምናውን ርግፍ አድርገው ትተው ወደ ዙምባብዌያቸው ተመለሱ፡፡

"ውለታ ቢስ ዲቃሎች!" አሉ መንግስቱ በጥላቻ ድምፅ፡፡ ፊታቸውን ቅጭም አድርገው ቀጠሉ፤ "ደቡብ አፍሪካ በአፓርታይድ መዳፍ ስር በነበረችበት ዘመን ኤ.ኤን.ሲን በፋይናንስ ጭምር ስረዳ ቆይቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ እኔ ዛሬ እርዳታቸውን በምሻበት ወቅት ሊረዱኝ ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ ሐራሬን ከመልቀቄ በፊት አካሄዴ በጤና ጉዳይ እስከሆነ ድረስ ምንም ችግር እንደማይገጥመኝ አረጋግጠውልኝ የነበረ ቢሆንም፤ ለኢትዮጵያ መንግስት አሳልፈው ሊሰጡኝ ተዘጋጅተው ነበር፡፡ …. እነዚህ ዛሬ የፕሪቶሪያን መንግስት የተቆጣጠሩትን ወገኖች የቀድሞ የትጥቅ ትግል ጓዶች፣ ወዳጆቼና የስራ ባልደረቦቼ አድርጌ እገምታቸው ነበር"አሉ፡፡

መንግስቱ ጓድ ሙጋቤን ማሞካሸት ዋና ስራቸው ነው፡፡ ሙጋቤም በበኩላቸው "በአህጉሩ ውስጥ ለነፃነት የተደረጉ ጦርነቶችን ሁሉ የረዱ ሰው ናቸው" በማለት ያንቆለጳጵሷቸዋል፡፡ ከብዙ አቅጣጫ መንግስቱን ከአገራቸው እንዲያባርሩና አሳልፈው እንዲሰጡ የሚሰነዘረውን ግፊት ሙጋቤ ጆሮ አይሰጡትም፡፡



በተለይ አሜሪካ ሙጋቤን "አምባገነን ደብቀሃል" በሚል ለመተቸት አፏን ስታሞጠሙጥ ሙጋቤ በሳቅ እየተፍለቀለቁ "በመጀመሪያ ደረጃ መንግስቱን ወደ ሐራሬ ያመጣችኋቸው እናንተ መሆናችሁን አስታውሱ እንጂ" በማለት ይሳለቃሉ፡፡

የመንግስቱን ጉዳይ በተመለከተ አሜሪካ አስፈላጊ ወጪያቸውን ለመሸፈን ቃል የገባችው ገና በማለዳ ነበር፡፡ ሙጋቤ ግን ተቃወሟቸው፡፡ "ገንዘባቸውን እንደማልፈልግ ነግሬያቸዋለሁ፤ አንድ ድሃ አፍሪካዊ ብሆንም ወጪውን ራሴ እሸፍናለሁ" ነበር ያሉት፡፡

እውነትም ከፍተኛውን የመንግስቱን የስልክ ወጪ ከመሸፈን አልፈው ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ሙጋቤ በሚገባ ሸፍነውላቸዋል፡፡ መንግስቱም ለቀድሞ ወዳጃቸውና ለአሁኑ ባለውለታቸው ለሙጋቤ ሲ.አይ.ኦ በመባል የሚታወቀውንና በህዝብ ዘንድ ብዙም የማይወደደውን የሙጋቤ የደህንነት መስሪያ ቤት እንደ አማካሪ ሆነው በማገልገል ውለታቸውን እየከፈሉ ነው፡፡

"እኔ የጦር ሰው ነኝ፤ አገሬን ከጎሰኝነትና ከፊውዳሊዝም ለመታደግ ስል ያደረኩትን አድርጌያለሁ፡፡ ዓላማዬ ያልተሳካው ክህደት ስለተፈፀመብኝ ብቻ ነው፡፡ ዘር ማጥፋት የሚባለው ነገር አብዮቱንና ሁሉም ሰው ተጠቃሚ የሆነበትን ስርዓት ለመከላከል ከተደረገ ትክክለኛ ጦርነት ውጪ ምንም ሊባል አይችልም" የሚሉት መንግስቱ ከባለቤታቸው ከወ/ሮ ውባንቺ ቢሻውና ከሦስቱ ዶ/ር ልጆቻቸው ከአንድነት፣ ከትዕግስትና ከትምህርት ጋር ከፊል ነፃነት ባለው አኗኗር ህይወታቸውን ይመራሉ፡፡ ሙጋቤ "ምነው መንግስቱ ሆስፒታል የመክፈት እቅድ አለህ እንዴ?" ብለው የቀለዱትም ልጆቻቸው ሁሉ የህክምና ዶ/ር በመሆናቸው ነው፡፡

መንግስቱ ከሪካርዶ ኦሪዚዮ ጋር በሚነጋገሩበት ጠበብ ያለች ቢሯቸው ውስጥ ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን ሙሉ የኢትዮጵያ ካርታ አፈጠጡበት፡፡ እሱ ላይ እንዳተኮሩ በትካዜ አፍጥጠው ቆዩና ቀጠሉ "… በጋው ላይ አማፅያኑ ያለምንም ፋታ ወደ አዲስ አበባ በመገስገስ ላይ ነበሩ፡፡ በመጨረሻው ሰዓት ሁሉም ፊቱን አዙሮብኝ ነበር፡፡ እናም አየር ኃይሉ ለነበሩት ተዋጊ ሚግ አውሮፕላኖች መለዋወጫ ስላልነበረው በረድፍ የሚጓዘውን የጠላት ጦር ለማጥቃት አልተቻለም፡፡

በዚያ ወቅት አሜሪካኖች የጉዳዩ ቀጥተኛ ተሳታፊ እየሆኑ የመጡበት ጊዜ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ጣልቃ የገቡት ወታደራዊ እርዳታ ለመስጠት ሳይሆን የማመልጥበትን ዘዴ ሊያመቻቹልኝ ኖሯል፡፡ ይህ የሚደረገውም ለሀገሪቱ የተሻለ በጎ ነገር እንደሆነ ተደርጎ በመታሰቡ ነበር፡፡ ስምምነቱም፤ እኔን፣ ቤተሰቤንና ጥቂት የቅርብ ደጋፊዎቼን ጭምር ደህንነቱ ባስተማማኝ ሁኔታ ወደሚጠበቅበትና ሠላማዊ ወደሆነ ቦታ የሚወስደንን አውሮፕላን ሊልኩልን ነበር፡፡…" በማለት ገለፀውለታል፡፡

“በዴሞክራሲ ያምናሉ?”

“ዴሞክራሲ የሚሰራው አውሮፓ ውስጥ ነው፡፡ የአፍሪካውያን ባህል የተለዩ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ዛሬ ያለችበተን ሁኔታ ተመልከት፡፡ የመድበለ ፓርቲ ስርዓት እያሰፈንን ነው እያሉ ያወራሉ፡፡ በተጨባጭ በማድረግ ላይ ያሉት ግን ጎሰኝነትን ማስፋፋት ነው፡፡ አገሬ እራሷ ቁጥራቸው አነስተኛ በሆነ አንድ ጎሣ አባላት ቁጥጥር ስር ከመውደቋም በላይ በጎሣ የተከፋፈለች ለመሆን በቅታለች፡፡ ይህ እንግዲህ ልክ እንደ መላዋ አፍሪካ ኋላ ቀር መሆንና ወደአለፈ ታሪክ መመለስ ነው፡፡

“እያንዳንዱ ሰው የፓርቲ አባል የሚሆነው አስተሳሰቡን በሚያራምድለት ፓርቲ ውስጥ ሳይሆን፣ በተወለደበት ጎሣ ነው፡፡ሱዳን፣ ሩዋንዳ፣ ብሩንዲ፣ ኮንጎ፣ ወይም ኬንያ ብትሄድ ሁኔታው ተመሳሳይ ነው፡፡ ዓለም አፍሪካ ውስጥ ከዚህ ቀደም አይቶ የማያውቀውን ጦርነት ወደፊት ያያል፡፡ ጦርነት ሲባልም አስጊ የሆኑ የጎሣ ጦርነቶችን ማለት ነው”

መንግስቱ ድምፃቸውን ጎላ አድርገው ቀጠሉ፣ “ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ አባባል አለን፡፡ ዓለም አዲስ ጫማ ካልተጫማችሁ እያለ ይወተውተናል፡፡ ከእኛ የሚጠበቀው ደግሞ እግራችንን ለዚህ ለአዲሱ ጫማ እንዲስማማ ማድረግ ነው፡፡ ይሁንና አንዳንድ ጊዜ አዲስ ጫማ የሰዎችን እግር ከፉኛ ስለሚልጣቸው አውልቀው ይጥሉታል፡፡ ለመሆኑ ይህን እርስ በርስ የሚቃረን የሚመስል አባባል ተረድተኸዋል? እናንተ ምዕራባውያን የምትሰሩልንን ጫማ ለእግራችን እንዲስማማ አድርጋችሁ በማዘጋጀት ፋንታ የምትጠይቁን በተቃራኒው ነው፡፡ ብቻ ምንም ተባለ፣ ምንም ተሰራ፣ እኔ የሰጠሁት ነጠላ ጫማ እስካሁን ድረስ አልተጣለም” በማለት መልሰዋል፡፡

የቀድሞው ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም ከመኖሪያ ቤታቸው ውጪ በ150ሺ ዶላር በኤመራልድ ኮረብታ የተከበበውን ውብና ድንቅ አካባቢ ላይ የተገነባውን ቤት ከመግዛታቸውም በላይ፣ ዙምባቡዌ እንደገቡም የእርሻ መሬት ገዝተው ከባለሃብቶች ተርታ የሚመደቡ ሆነዋል፡፡ ዘውዳዊ ስርዓቱን ከስሩ መንግለው የጣሉት መንግስቱ የዛሬን አያድርገውና በሺዎች የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ወጣቶችን አንድ ዓይነት ዩኒፎርም አልብሰው በሰልፍ አንጉደዋል፡፡ “ከመንግስቱ ኃይለማርያም ቆራጥ አመራር ጋር ወደፊት!” እያሉ ብዙዎች እጃቸው እስኪዘነጠል አጨብጭበውላቸዋል፡፡ ዛሬ ግን ተነስ! ታጠቅ! ዝመት! እናት አገር ወይም ሞት! ሳታጣ ያጣች አገራችን! የታፈረችና የተከበረች ኢትዮጵያ!... ማለታቸውን አቁመዋል፡፡ የጋለ መፈክራቸው ቀርቷል፡፡ የሚፎክሩበት መድረክም የላቸውም፡፡ ስለዚህ ቀዝቀዝ ብለው ቀሪ ህይወታቸውን ያለፈ ታሪካቸውን በመፃፍና ውስኪ በመጎንጨት ያሳልፉታል፡፡



***     ***     ***

“የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ” በሚል ርዕስ ከኖኅ ጀምሮ እስከዳግማዊ ምኒልክ ድረስ የነበረው ታሪክ በክፍል አንዱ መጽሐፍ በ456 ገጾች ተጠናቅሮ በ2003 ዓ.ም ለሕትመት በቅቶ፣ በተደጋጋሚም ታትሞ ለአንባቢ መድረሱ ይታወቃል፡፡ ከልጅ እያሱ ጀምሮ እስከ ኢህአዴግ ዘመን ድረስ የነበረውን ታሪክ “ካልተዘመረለት እያሡ እስከተዘመረለት ኢህአዴግ” በሚል ርዕስ በቅርቡ ጠብቁት” ብዬ በገባሁት ቃል መሠረት የ“መጽሐፍ አንድ”ን ተከታይ ክፍል “መጽሐፍ ሁለት”ን ባያችሁት መልኩ አቅርቤ ሙሉውን የኢትዮጵያ ታሪክ ፈጽሜያለሁ፡፡

ታዲያ “ካልተዘመረለት እያሡ እስከተዘመረለት ኢህአዴግ” ከተባለ፤እያሱ ለምን እንዳልተዘመረለት የመገለፁን ያህል፣ ኢህአዴግ ለምን እንደተዘመረለትስ እንዴት አልተገለፀም? የሚል አንባቢ ሊኖር እንደሚችል ይሰማኛል፡፡

ሁለት ምላሾችን እሰጣለሁ፡፡ ምላሽ አንድ፤ ስልጣን ላይ ያለ መንግስት ለዜና እንጂ ለታሪክ አይሆንም፤ ዜናውም ልዩ ጥንቃቄ ያሻዋል፡፡

ምላሽ ሁለት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ስልጣን ላይ ያለ መንግስት ምንጊዜም ስለሚዘመርለት ነው እየተዘመረለት ያለው፡፡

..............................ተፈጽሟል...........................

## ዋቢ መጻህፍት


ኀበዜ ጣፈጠ፤ *አባ ጤና ኢያሡ*፤ 1996 ዓ.ም::

ተክለሐዋርያት ተክለማርያም ፤ *የህይወቴ ታሪክ /ኦቶ ባዮግራፊ/*፤ 1999 ዓ.ም::

ጥላሁን ብርሃነስላሴ ቤተ፤ *የ20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ ከ1900 - 1966 1ኛመጽሐፍ*፤ 1996 ዓ.ም::

ከበደ ተሰማ ፤ *የታሪክ ማስታወሻ*፤ 1962 ዓ.ም::

ባህሩ ዘውዴ፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1947 — 1983*፤ 2002 ዓ.ም::

ተክለፃድቅ መኩሪያ፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ አፄ ኃይለስላሴ*፤ 1936 ዓ.ም::

ማሕተመ ስላሴ ወልደመስቀል፤ *ዝክረ ነገር*፤ 1962 ዓ.ም::

ብርሀኑ ድንቄ፤ *አጭር የኢትዮጵያ ታሪክ*፤ 1952 ዓ.ም::

ብርሀኑ ድንቄ፤ *ቄሣርና አብዮት*፤ 1987 ዓ.ም::

ላጺሶ ጌ ድሌቦ፤ *የኢትዮጵያ የገባር ስርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም ከ1900 — 1966*፤ 1983 ዓ.ም::

መርስዔኀዘን ወልደቂርቆስ፤ *የሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ*፤ 1999 ዓ.ም::

ፍቅረማርቆስ ደስታ፤ *ጃገማ ኬሎ (የበጋው መብረቅ)*፤ 2001 ዓ.ም::

ገብረህይወት ባይከዳኝ፤ *መንግስትና የህዝብ አስተዳደር*፤ 1953 ዓ.ም::

ፍትሃዬ ሐጎስ፤ *ጥንታዊና ዘመናዊ የኢትዮጵያና የኤርትራ ታሪክ*፤ 1956 ዓ.ም::

ጳውሎስ ኞኞ፤ *የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት*፤ 1984 ዓ.ም::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፤ *ህይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ*፤ 1965 ዓ.ም ቁጥር 1 እናቁጥር 2 ::

ዘውዴ ረታ፤ *የኤርትራ ጉዳይ*፤ አዲስ አበባ፡፡

መርስዔሃዘን ወልደቂርቆስ፤ *ፍሬ ከናፍር*፤ ቁጥር 5 1952 ዓ.ም::

ዋለልኝ እምሩ፤ *የዓለም ጀግኖች አጫጭር ታሪክ*፤ 1997 ዓ.ም::

ታደሰ ዘወልዴ፤ *ቀሪን ገረመው፤ የአርበኞች ታሪክ*፤1960 ዓ.ም::

ዲሚትሪ የፍሞቭ፤ *ሁለተኛው የዓለም ጦርነትና፤ የእስያና የአፍሪካ ህዝቦች ዕጣ*፤(አማርኛ ትርጉም) 1990 ዓ.ም::

ሁሴን አህመድ፤ *መስዋዕትነትና ፅናት*፤ 1997 ዓ.ም::

ገነት አየለ፤ *የሌ/ኮ/ል መንግስቱ ኃይለማርያም ትዝታዎች*፤ ቁጥር 1 1994 ዓ.ም ቁጥር 2 2002 ዓ.ም::

ተስፋዬ ርስቴ፤ *ምስክርነት*፤ 2001 ዓ.ም::

ዘነበ ፈለቀ፤ *ነበር*፤ ቁጥር1፤ 1996 ዓ.ም፤ ቁጥር 2፤ 2001 ዓ.ም::

ክፍሉ ታደሰ፤ *ያ ትውልድ፤ የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ታሪክ፤* ክፍል 1እና 2 ሲልቨር ስፕሪንግ (ሜሪላንድ) እና ኢትዮጵያ፡፡

ተስፋዬ መኮንን፤ *ይድረስ ለባለታሪኩ*፤1985 ዓ.ም::

ኢዮብ አባተ እንዳለ /ሻምበል/፤ *ጀኔራሎቹ*፤ 2002 ዓ.ም::





ተስፋዬ ሐብተማርያም፤ *የጦር ሜዳ ውሎ*፤ 1997 ዓ.ም::

እፎይታ መጽሔት 8ኛ ዓመት ቁጥር 5 ጥር 1992 ዓ.ም::

አዲስ ዘመን ጋዜጣ 34ኛ ዓመት ቁጥር 231 1983 ዓ.ም::

አዲስ ውበት መጽሔት የካቲት 1997 ዓ.ም::

አዲስ ነገር ጋዜጣ ሐምሌ 18 ቀን 2001 ዓ.ም::

አዲስ ዘመን የካቲት 7 ቀን 1966 ዓ.ም::


## REFERENCES


Aby Demissie. "Lij Iyasu A Perspective study of his short reign" (HSIU History,1964)

Addis Hiwet. *Ethiopia: From Autocracy to Revolution.* London 1975.

Andargachew Tiruneh. *The Ethiopian Revolution 1974 - 1987: A Transformation from an Aristocratic to a Totalitaria autocracy*. Cambridge, 1993

Assefa Tewodros. "History & Telecommunications in Ethiopia up to 1974". (A.A.U. 1973).

Ayele Tarekegn. "The History of the Imperial Highway Authority (IHA), 1951 - 1980". (AAU 1987).

Baharu Zewde (Prof.). "Economic origins of the Absolutist state in Ethiopia, 1916 - 1935". *JES* Vo. 14 1984.

Baharu Zewde. *Pioneers of change in Ethiopia*. 2002.

Badoglio, Pietro. *The war in Abyssinia*. London 1937.

Belete Bizuneh. "Political Power and the Revolution: The Struggle for a 'Provisional People's Government' 1974 - 1976 Graduate Seminar paper (AAU department of History 1997).

Bekure Woldesemaiat. "Industrial development in Addis Ababa". *JES* Vol. 17 1984.

Clapham, Christopher. *Haile Selassie's Government.* New York, 1968 Cohen, J.M. and Wentraub D. *Land and Peasants in Imperial Ethiopia: The Social Backgraund to a Revolution*. Assen, 1975.

*Combat.* A special publication of the Ethiopia Students Union in North America;on the 20th congress of ESUNA. v.1 no.3 1972.

Del Boca, Angelo. *The Ethiopian war 1935 – 1941*. Chicago, 1969.

Duri Mohammed. "Private investment in Ethiopia, 1950 – 1965". *JES* Vol. 7 No 2 1969.

Dunn, John. *Modern Revolutions. An Introduction to the Analysis of Political Phenomenon.* Cambridge 1989.

Gilkes, Patrick. *The Dying Lion. Feudalism and modernization inEthiopia.* London 1975.

Harold Marcus. *The Politics of Ethiopia, Great Brithain and the United States 1941 - 1974: The Politics of Empire.* Berkelay 1983.
Ikeda,Sumihisa(gen). "Nathional defense including defense council,defense policy council and council of commanders"(report to His Majesty).July26, 1957. Mahtheme selassie Wolde Mesqel. "The land system of Ethiopia"(Ethiopian observer vol.1.no9 1957).
Mesfin Woldemariam. *Rural vulnerability of famine in Ethiopia, 1958- 1977.* New Delhi 1984.
Mesay Kbede. *Survival and Modernization.*
Pankhurst,Richard. "The foundations of education, printing, newspapers, book production,libraries and literacy in ethiopia".(Ethiopian Observer v.6 n.3 1962).
Rubenson,Sven. *The survival of Ethiopian independence.*1976.
Riccardo Orizeo. *Talk of the devil.* 2003 (ትርጉም አጥናፍሰገድ ኪዳኔ 1996 ዓ.ም).
*Spark.* A special publication of the Ethiopia Students Union in North America;on the 19th congress of ESUNA. v.1 no 1. December 1971.
Spencer,John. *Ethiopia at bay: a personal account of the Haile Selassie years.* 1984.
Tilahun Takele(pseudonym). The national question (regionalism) in Ethiopia. (Newyork chapter news latter, no3. March 1972.
Yano, Muraji(col). "Draft of central intellignce agency establishment act".
(a study report to the Ethiopian government,october26 1957).
*Challenge.* "Education; challenge to the nation". The world wide federation of Ethiopia students. v.13 no.1. August 1972.